# ኤክሌሽያ



በ ሰለሞን ወልደአምላክ

# ኤክሌሽያ

ከሰለሞን ወ/አምላክ

ሚያዝያ 1985 ዓ. ም.
አዲስ አበባ

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ለማባዛት ፤ መልሶ ለማሳተም እና ለማስተርጐም የደራሲው
መብት የተጠበቀ ነው ።

# ማ ው ጫ

ገጽ

መግቢያ ........................................ 7—9

ምዕራፍ 1 ኤክሌሽያ ማን ናት ? ........................ 11

ክፍል አንድ የኤክሌሽያ ትርጉም ........................ 11

ሀ. ቤተክርስቲያን የሚለው የአማርኛ ቃል
ለ. የቤተክርስቲያን ድርጅታዊ መልክ (ዲኖሚኔሽን)
ሐ. ቤተክርስቲያን - መሪዎች
መ. ቤተክርስቲያን በእንግሊዝኛ - ቸርች

ክፍል ሁለት - የአማኞች ልዩ ልዩ መጠሪያዎች ............ 14—15

ሀ. ደቀመዝሙር
ለ. ቅዱሳን
ሐ. ክርስቲያን
መ. የመንገዱ ሰዎች

ምዕራፍ 2 የኤክሌሽያ ልደት 17—19

ሀ. ከብሉይ ኪዳን የቀጠለች ናት
ለ. በደቀ መዛሙርቱ ጊዜ ተመሥርታለች
ሐ. በበዓለ ሃምሣ ቀን

ምዕራፍ 3 የኤክሌሽያ መሠረትና ገጽታ ................ 21

ክፍል አንድ - የኤክሌሽያ መሠረት ........................ 21

ሀ. የካቶሊክ ቤተክርስቲያን አመለካከት ................ 21

ለ. የሌሎች አብያተክርስቲያናት አመለካከት .............. 21

ሐ. የማቴዎስ 16 ፥ 18 ትርጉም ........................ 21

መ. ስለኤክሊሺያ መሠረት የጴጥሮስ መረዳት ............ 22

ሠ. የጳውሎስ መረዳት ........ 22
ክፍል ሁለት - የኤክሌሽያ ገጽታ ........ 22
ሀ. የማትታየዋ ኤክሌሽያ ........ 22
ለ. የምትታይ አጥቢያ ኤክሌሽያ ........ 23
ምዕራፍ 4 ኤክሌሽያ የምትመሰልባቸውም ምሳሌዎች ...... 25
ክፍል አንድ - የማትታይና የምትታየው ኤክሌሽያ በጋራ የተመሰሉ ባቸው ምሳሌዎች
ሀ. በሙሽራ (በሚስት) ........ 25—28
ለ. በአካል ........ 28—29
ሐ. በሕንጻ ቤት ........ 29
ክፍል ሁለት-የምትታየው ኤክሌሽያ ብቻ የተመሰለችባቸው ምሳሌዎች ፣
ሀ. በዓሣ ማጥመጃ መረብ ........ 30
ለ. በስንዴ አዝመራ ........ 30
ሐ. በእርሻ ........ 31
ምዕራፍ 5 የኤክሌሽያ ድርጅታዊ ገጽታ ........ 33
ሂፍል አንድ - ድርጅት ምን መልክ አለው ? ........ 33
ሀ. ድርጅት ሊኖሩት የሚገቡ ነገሮች ........ 33
ለ. የኤክሌሽያ ድርጅታዊ መልክ ........ 33—34
ሐ. ኤክሌሺያ ከምድራዊ ድርጅት ልዩ የሚያደርጋት 34—35
ክፍል ሁለት-የኤክሌሽያ አስተዳደር ዓይነቶች ........ 35
ሀ. ኤጲስቆጶሳዊ አገዛዝ ........ 35—36
ለ. ፕሪስፒተርስ አገዛዝ ........ 36—37
ሐ. የጉባኤ አስተዳደር ........37—38
መ. የብዙኃን ሽማግሌዎች አስተዳደር ........ 38
ሠ. ግላዊ አስተዳደር ........ 38
ምዕራፍ 6 ለኤክሌሽያ የተሰጡ አገልጋዮች ........ 39
ሀ. ሐዋርያት ........ 39—44
ለ. ነቢያት ........ 44—48
ሐ. ወንጌላውያን 48—49
መ. እረኞች ፣ አስተማሪዎችና ሽማግሌዎች ........ 50—53
ሠ. ዲያቆናት ........ 53—54
ምዕራፍ 7 አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ማደራጀት ........ 55
ክፍል አንድ - የመጀመሪያይቱ ኤክሌሽያ መስፋፋት ...... 55
ሀ. ለመጀመሪያይቱ ኤክሌሽያ ቶሎ ማደግ ምክንያት የሆኑት ነገሮች ........ 55—56
ለ. ሌሎችን አጥቢያ ኤክሌሽያን በየቦታው መመሥረት እና ማስፋፋት ........ 56—57
ክፍል ሁለት-በዚህ ዘመን አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ማደራጀት ... 57
ሀ. የደረጀች ቤተክርስቲያን ሌሎች አጥቢያዎችን ለመመሥረት ስታስብ ልትወስደው የሚገባ እርምጃ ........ 58—59
ለ. አዲስ የተቋረቋረችን ቤተክርስቲያን ራሷን ስለ ማስቻል59—62
ሐ. መሥራች ቤተክርስቲያን አዲስ ለተመሠረተች አጥቢያ ያለ ባት ኃላፊነት ........ 62—66
ምዕራፍ 8 የኤክሌሽያ አገልግሎት ........ 67
ክፍል አንድ - የኤክሌሽያ የውስጥ አገልግሎት ........ 67
ሀ. አምልኮ ........ 67—68
ለ. የመታነጽ አገልግሎት ........ 68—69
ሐ. መንጻት ........ 69—70
መ. ደቀመዛሙርትን ማፍራት ........ 70
ሠ. የኤክሌሽያ ሁለት ሥርዓቶች ........ 70—71
1. የውኃ ጥምቀት ........71—72
2 . የጌታ እራት ........ 72—74
ክፍል ሁለት - የኤክሌሽያ የውጭ አገልግሎት ........ 74
ሀ. ለዚህ አገልግሎት መሠረት የሚሆኑ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ........ 74
ለ. ወንጌል ላልደረሳቸው ማዳረስ ........ 74—75
ሐ. ምሳሌ ሆነው የቀረቡ ሁለት ነገሮች ........ 75—76
መ. ከአማኞች ሌላ በወንጌል ሥራ ማን ድርሻ አለው?... 76—80

# መግቢያ

ኤክሌሽያ በእግዚአብሔር ፈቃድና ኃይል የተዘጋጀች የመንግሥተ ሰማያት ክፍል ናት ።

ኤክሌሽያ መሠረቱ በጸና በከበረ ድንጋይ ላይ የተመሠረተች የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናት ። 1 ጴጥ. 2 ፥ 4—6 ፥ 1 ቆሮ. 3 ፥ 16

ኤክሌሽያ ክርስቶስ በክቡር ደሙ የዋጃት ፥ ስለእርስዋ ራሱን እስኪሰጥ ድረስ የወደዳት አካሉ ናት ። ኤፌ. 5 ፥ 25, 1 ፥ 22

ኤክሌሺያ ሥራዋ አላለቀም ፥ በአንድ በኩል እየተሠራች ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር እየሠራባት ያለች የእግዚአብሔር ምድራዊ ድርጅት ናት ። 2 ቆሮ. 5 ፥ 18—19 ።

ኤክሌሽያ ሥራዋ ሲጠናቀቅ ከዚህ ዓለም ወደተዘጋጀላት ሰማያዊ አገር ትወሰዳለች (ፊል. 3 ፥ 20) ፥ (ዮሐ. 14 ፥ 1—3) እስከዚያው ድረስ በጨለማው ዓለም ላለው ሕዝብ የሕይወትን ቃል እያቀረበች እንደብርሃን ትታያለች ። ማቴ. 5 ፥ 14 ፥ ፊል. 2 ፥ 14—16 እግዚአብሔር የገባላት የተስፋ ቃል ሲፈጸም ግን ከክብር ወደ ክብር ትለወጣለች ፥ ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ አገር ለዘለዓለም ትኖራለች ። 2 ቆሮ. 3 ፥ 18 ፥ 1 ተሰ. 4 ፥ 15—18

ኤክሌሽያ በአንድ መልኳ የሙሽራውን መምጣት የምትጠባበቅ ሙሽራ ስትመስል ፥ በሌላ መልኳ ደግሞ ዓላማ ይዞ የተሰለፈን ሠራዊት ትመስላለች ። መ. መ. 6 ፥ 10 (2 ቆሮ. 11 ፥ 1—2 ፥ ራዕ. 19 ፥ 7) (2 ቆሮ. 10 ፥ 3—6. ኤፌ. 6 ፥ 10—17)

ኤክሌሽያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ምሳሌዎች ተመስላ ተገልጸለች።ታዲያ ስለኤክሌሽያ ለማጥናት የሚፈልግ ሰው ኤክሌሽያ የተመሰለችባቸውን ምሳሌዎች ማወቅ ብቻ ሳይሆን ለምን በእነዚህ ምሳሌዎች እንደተመሰለች ማወቅ አለበት ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለማብራራት የተሞከረው አንዱ ክፍል ይህ ይሆናል ።

ኤክሌሽያ ሁለት ገጽታ አላት ፥ አንደኛዋ ገጽታ የማትታየዋ ኤክሌሽያ ስትሆን ሁለተኛዋ ደግሞ በምድር የምትታይ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምታውጅ ኤክሌሺያ ናት ። የሁለቱን መልክ በማነጻጸር ስለቀረበ ስለኤክሌሺያ የሚያጠና ሰው ሰፊ ግንዛቤ ማግኘት ይችላል ።

በአሁኑ ጊዜ ወንጌል በአገራችን በከተማም ሆነ በገጠር ከምን ጊዜም
በላይ እየተስፋፋ በመሄድ ላይ ነው ። ስለዚህ ወንጌልን ከማስፋፋት ጐን
አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ስለማደራጀት ሁኔታ አብሮ ሊታሰብበት የሚ
ገባ ጉዳይ ነው ።

ብዙ ጊዜ አዳዲስ አጥቢያዎች ሲመሠረቱ በቂ መመሪያ ካለማግኘት
የተነሳ ችግሮች አብረው ይመሠረታሉ ። " ኤክሌሺያ " በዚህ ረገድ ቤተ
ክርስቲያንን ለሚያደራጁም ሆነ ለሚመሠርቱ አዳዲስ አጥቢያ ቤተክርስ
ያናት ትልቅ አስተዋጽኦ ታደርጋለች ብዬ አምናለሁ ።

በሌላ በኩል ደግሞ የደረጀች ቤተክርስቲያን አዲስ የተቆረቆረ አጥ
ቢያዎችን በጊዜው ራሳቸውን ባለማስቻሏ ምክንያት የሚያስከትለ
ውን አዝማሚያ ባለመገንዘብ በሞግዚትነት ይዘው ለረጅም ጊዜ ያቆዩ
አቸዋል ። ይህ ደግሞ ለቤተክርስቲያን መስፋፋት ዕድገት ትልቅ አንቅ
ፋት ሆኖ ይታያል ። ስለዚህ የአዳዲስ አጥቢያ ቤተክርስቲያናት በየሥፍ
ራው መመሥረትና ቶሎ ራሳቸውን የማስቻሉን ዘዴ ማሳየት ያስፈልጋል።
ይህ ደግሞ ለወንጌል መስፋፋትና ለቤተክርስቲያን ዕድገት የሚያስገኘው
ውጤት ከፍ ያለ ይሆናል ።

ብዙ ጊዜ ካለማወቅ ይሁን ከቸልተኝነት የተነሳ አንዳንድ የቤተክር
ስቲያን መሪዎች ቤተክርስቲያን የምታድግበትንና ወንጌል የሚስፋፋበ
ትን መንገድ ከመቀበል ቸል ይላሉ ። ስለዚህ የቤተክርስቲያን መሪዎች
ደግሞ መንፈሣዊ አባቶች ስለሆኑ ሥልጣናቸውን ከመንከባከብ ይልቅ
ቤተክርስቲያን የምታድግበትንና የምትስፋፋበትን መንገድ እንዲቀበሉ
" ኤክሌሽያ " ከጸሎት ጋር ተጠምራ እንድታነሳሳ ተዘጋጅታለች ።

በእርግጥ በዚህ ርዕስ ላይ ለበርካታ ዓመታት ለቤተክርስቲያን መሪ
ዎችና አገልጋዮች ሳስተምር ብዙዎች በመጽሐፍ መልክ አሳትሚ እን
ዳወጣ ያበረታቱኝ ነበር ። መንፈሣዊ መጻሕፍትን ለማዘጋጀት ቀላል
እንዳይደለና ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት " ኤክሌሽያ " ን
ሳዘጋጅ ተረድቻለሁ ።

ይሁን እንጂ " ኤክሌሽያ " ን ሳዘጋጅ ራሴ ብዙ ተባርኬበታለሁ ።
ስለዚህ ለእኔም ለራሴ ለበረከት እንደሆነኝ በቅን ልብ ሆነው በተመስጦ
ለሚመለከቷት ሁሉ " ኤክሌሺያ " ለበረከት እንደምትሆንላቸው እም
ነት አለኝ ።



በተለይ ለቤተክርስቲያን መሪዎች ፣ ለእረኞች ፣ ለወንጌላውያን ፣
ለመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎችና ተማሪዎች ፣ እንዲሁም በቤተክርስቲ
ያን ውስጥ በተለያየ አገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ገብተው ጌታን ለሚያገለ
ግሉ ሁሉ የተትረፈረፈ በረከት እንድታመጣላቸው የዘወትር ጸሎቴ ነው ።

# ምዕራፍ አንድ

## ኤክሌሽያ ማን ናት ?

ኤክሌሽያ ከእግዚአብሔር የተወለደች ፣ ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን የተጠራች ፣ የመንግሥተ ሰማይ ክፍል ናት ። (ዮሐ. 1 ፣ 11—13 ፣ 1 ጴጥ. 2 ፣ 9 ፣ ማቴ. 13—24, 32,44,45)

በዓለማችን ብዙ የተለያዩ ድርጅቶች አሉ ። የፖለቲካ ድርጅቶች ፣ የተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች ፣ የንግድ ድርጅቶችና የመሳሰሉ ድርጅ ቶች አሉ ። ሁሉም በሰዎች ፍላጐት የተገኙና በሰዎች ብልሃት የተፈ ጠሩ ናቸው ።

ኤክሌሽያ ግን በእግዚአብሔር ሐሳብ ብቻ የነበረች በዘመኑ መጨ ረሻ ከእግዚአብሔር የተገኘች የክርስቶስ አካልና የእግዚአብሔር ቤተመ ቅደስ ናት። ኤክሌሽያ የክርስቶስ የሥራ ውጤት ስለሆነች ። ስለ ኤክሌሽያ መወለድና መገኘት ትንቢት ሲናገሩ የነበሩ ነቢያት እንኳ ተግተው ቢመ ረምሯትም ሊደርሱባት አልቻለም ። መላዕክት እንኳን ሊመለከቱ ሲመኙ ቆይተዋል ። (1 ጴጥ. 1 ፣ 10—12) ስለዚህ በዚህ በምዕራፍ አንድ ውስጥ ስለ ልደቷና ስለ ማንነቷ እንመለከታለን ።

### ክፍል 1. የኤክሌሽያ ትርጉም ፣

ኤክሌሽያ ስንል ምን ማለታችን ነው ? ከየት የተገኘ ቃል ነው ? ኤክ ሌሺያ የሚለው ቃል ከግሪክ ቋንቋ የተገኘ ሲሆን ፣ ትርጉሙም “ ተጠር ተው የወጡ ” ማለት ነው ። ይህን ቃል ግሪኮች ቀድሞም ይጠቀሙበት ነበር ። ለተለያየ ዓላማ የሚሰበሰብ ጉባኤ ኤክሌሽያ ይባላል ። ስለዚህ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣን ግዛት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ፣ ከአርኬስት ወደ ቅድስና የወጣው ሕዝብ ኤክሊሺያ ተባለ ። (1ጴጥ. 2 ፣ 9—10) ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ግን በየቋንቋው በተለምዶ ኤክሌሽያ የምት ጠራበት ስም ብዙ ሊሆን ችሏል ።

#### ሀ. ቤተክርስቲያን የሚለው የአማርኛ ቃል ፤

ቤተክርስቲያን የሚለው የአማርኛ ቃል ብንመለከት ኤክሌሽያ የሚለውን በኩረ ቃል ትርጉም የተከተለ አይመስልም ። ቤተክርስቲያን

ማለት እንደ ቃሉ ከሄድን ቀጥተኛ ትርጉሙ የክርስቲያን ቤት ማለት ነው። ሐሳቡ ምናልባት የክርስቲያኖች መሰብሰቢያ ወይም ጸሎት ቤት ለማለት ይሆናል ። ይሁን እንጂ በመሰብሰቢያ ቤትና በሚሰበሰቡ ሰዎች መካከል ብዙ ልዩነት አለ ። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ለንምፋን በቤቱም ላለች ቤተክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ ይላል ። (ቆላ. 4 ፥ 15)

ከዚህ እንደምንረዳው በሐዋርያው ጳውሎስ አእምሮ ውስጥ ያለው የንምፋን ቤት ሳይሆን በንምፋን ቤት ውስጥ በጸሎት የሚሰበሰቡት ወገኖች ናቸው ።

ወደ ቂሳሪያም በደረሰ ጊዜ ወጥቶ ለቤተክርስቲያን ሰላምታ ከሰጠ በኋላ ወደ አንጾኪያ ወረደ ይላል ። (ሥራ 18 ፥ 22) ሐዋርያው ጳውሎስ ሰላምታ የሰጠው ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን ተጠርተው ለወጡ ቅዱሳን ወገኖች ነበር እንጂ ለሕንጻ ቤት አልነበረም ። እንደዚሁም ደግሞ ከአንጾኪያ ቤተክርስቲያን ጳውሎስና በርናባስ ወደ ኢየሩሳሌም በመጡ ጊዜ "ቤተክርስቲያንና ሐዋርያት ፣ ሽማግሌዎችም ተቀበሏቸው " ሲል ምዕመኑ ከመሪዎቻቸው ጋር እንደተቀበሏቸው ያሳያል ። (ሥራ 15 ፥ 5 )

ስለዚህ ቤተክርስቲያን ሲባል በዚያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች በአእምሮአቸው የሚታያቸው ሕዝብ እንጂ ሕንጻ ቤት ወይም መሰብሰቢያ ሥፍራ አልነበረም ።

በአሁኑ ጊዜ ግን ቤተክርስቲያን ሲባል ሕንጻ ቤት ወይም መሰብሰቢያ ሥፍራ ነው በሃሳባችን የሚመጣው ። ስለዚህ መሠብሰቢያ የሆነው

ሕንጻ ጸሎት ቤት ማለት ልምድ ቢደረግ የተሻለ ነው ።

ለ/ የቤተክርስቲያን ድርጅታዊ መልክ (ዲኖሚኔሽን)

ቤተክርስቲያን ሲባል በአሁኑ ጊዜ የሚታሰበው ሌላው ትርጉም ድርጅታዊ መልክ ወይም ዲኖሚኔሽን ነው ።

በዘመናችን የዲኖሚኒሽን ብዛት እንደመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ያህል የበዛ ነው ። በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን በነበሩት ቅዱሳን መሐከል ምንም የዲኖሚኔሽን ልዩነት አልነበረም ።

በእርግጥ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አካባቢያቸው በሚጠራበት ስም ይጠሩ ነበር ። ለምሳሌ ኢየሩሳሌም ያለች ቤተክርስቲያን፣ አንጾኪያ ያለች ቤተክርስቲያን ፣ ተሰሎንቄ ፣ ቆሮንቶስ ወዘተ . . . እየተባሉ ይጠሩሉ ።

በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን ባሉት ቤተክርስቲያናትና በአሁኑ ዘመን ባሉት ቤተክርስቲያናት መካከል ያለው ልዩነት አንዱ የድርጅታዊ መልክ ልዩነት ነው ። በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በመ



ንፈሳዊነታቸው ጠንካራ አቋም ሲኖራቸው ድርጅታዊ አቋማቸው ግን የተጠናከረ አልነበረም ። በአሁኑ ዘመን ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ከጥቂቶች በስተቀር ብዙዎቹ በድርጅታዊ አቋማቸው ጠንካሮች ቢሆኑም በመንፈሳዊነታቸው እስከዚህም አይደሉም ።

ለዲኖሚኔሽን መብዛት ምክንያት የሆኑ ሁለት ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ ። አንደኛ በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ማለትም በመሠረታዊ የክርስትና ትምህርት መለያየት ሲሆን ፣ ሁለተኛው ደግሞ በቤተክርስቲያን አስተዳደር አለመግባባት ምክንያት ሊሆን ይችላል ። ሆኖም ሁሉም " ቤተክርስቲያን " በሚል ስም ይጠራሉ ።

ሐ. ቤተክርስቲያን—መሪዎች ፤

አንዳንድ አጥቢያዎች የቤተክርስቲያን - መሪዎችን " ቤተክርስቲያን " ብለው ይጠሯቸዋል ። ይህም በልማድ የመጣ እንጂ መሠረታ ሐሳቡ እንዲህ አይደለም ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደምንመለከተው ከሆነ ሽማግሌዎችና ቤተክርስቲያን ተለይተው ይጠቀሳሉ ። (ሥራ 15 ፥ 4,22 ፥ ፊል.1 ፥ 1)

በአሁኑ ጊዜ የቤተክርስቲያን መሪዎች " ቤተክርስቲያን" ተብለው መጠራታቸው አጥቢያ ቤተክርስቲያንን ስለሚወክሉ ሊሆን ይችላል ።

ወደ ሌላ ቤተክርስቲያን ወይም ድርጅት መልዕክት ለማስተላለፍ ሲፈለግ ከሆነ ሐሳቡ ልክ ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን መሪዎች ለማኅበረ - ምዕመኑ መግለጫ ሲሰጡ ራሳቸውን " ቤተክርስቲያን " ብለው ከጠሩ ማኅበረ - ምዕመኑን ማን ብለው ሊጠሩ ነው ? ስለዚህ በአግባቡ ራሳቸውን " የቤተክርስቲያን መሪዎች " ብለው ቢጠሩ ተገቢ ይሆናል ።

መ. በእንግሊዝኛ ኤክሌሽያ ቸርች ትባላለች ፥ይህ ቸርች የሚለው ቃል ከየት የተገኘ ቃል ነው ? በብዛት የተለመደው ይህ ቸርች የሚለው የእንግሊዞች ቃል " ኩሪያ ኮዝ " ከሚል ከግሪክ ቋንቋ የተወለደ ነው ። ትርጉሙም " የጌታ " የሚል ነው።ኩሪያኮዝ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ሁለት ቦታ ላይ ብቻ ተጠቅሶ እናገኘዋለን ። አንደኛው በራዕ. 1 ፥ 10 ላይ " የጌታ " ወይም " በጌታ " ቀን የሚለው ሲሆን ሁለተኛው 1 ቆሮ. 11 ፥ 20 ላይ ያለው " የጌታ " እራት የሚለው ነው ። ስለዚህ ቸርች የሚለው ሐሳብ ምናልባት " የጌታ የሆኑ " ለማለት ታስቦ ይሆናል ። መሰረተ ሐሳቡ ትክክል ነው ። ቤተክርስቲያን የጌታ ናት ፣ የማንም አይደለችም ፣ ማንም የእኔ ናት ሊል አይችልምና ። እነዚህ የጌታ የሆኑት ደግሞ ልዩ ልዩ መጠሪያ ስሞች አሏቸው ።

ለረጅም ጊዜ የቆዩ ልምዶችን በአንድ ጊዜ መቀየር በእርግጥ ያስቸግር ይሆናል ። ስለዚህም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንባቢያን ስሜት በሚሠጥ መልኩ ቤተክርስቲያን ኤክሌሽያ የሚለውን ስያሜ በማጣጣም ለመጠቀም ሞክሬአለሁ ።

## ክፍል 2 የአማኞች ልዩ ልዩ መጠሪያ ስሞች ፤

በጥንት ጊዜ አማኞች የሚጠሩባቸው የተለያዩ ስሞች በአሁኑ ጊዜ ግን እምብዛም የማንጠቀምባቸው አሉ ።

### ሀ. ደቀ መዝሙር

ደቀ መዝሙር የሚለው ቃል ተማሪ ወይም ተከታይ ማለት ነው ። ይህ ደግሞ ከጥንት ከአይሁድ ተያይዞ የመጣ ነው ። (ኢሳ. 8 ፥ 16) በዚያን ጊዜ ደቀ መዝሙርት የሚባሉት በአጠቃላይ የጌታን ትምህርት ተቀብለው በጌታ የሚያምኑትን ሁሉ ነበር ። (ሥራ 6 ፥ 1 ፥ 9 ፥ 1 ፥ 15 ፥ 1 ፥0 14 ፥ 21)

ፈሪሳውያንም ደቀመዛሙርት ነበሯቸው ። (ማር. 9 ፥ 14) ስለዚህ አሁን አዲስ መምህር ክርስቶስ በመጣ ጊዜ እርሱን የተቀበሉትና የሚከተሉት ሁሉ ደቀመዛሙርት ተባሉ ። ጌታም ይህን ደቀመዝሙር የማድረጉን ሥራ እንዲቀጥሉ ለሐዋርያት አዟል ። (ማቴ. 28 ፥ 18—20) አሁንም ደቀመዝሙር የማድረጉ ሥራ ቢኖርም የአማኞች " ደቀመዛሙርት " ተብሎ የመጠራት ጉዳይ እምብዛም ነው ።

### ለ. ቅዱሳን (ሥራ 9 ፥ 32)

አማኞች የሚጠሩበት ሌላ ስም " ቅዱሳን " በመባል ነው ። ቅዱሳን ማለት ለእግዚአብሔር የተለዩ ማለት ነው ። ማለትም ከዓለምና ከኃጢአት ተለይተው ለእግዚአብሔር ራሳቸውን ያቀረቡ ማለት ነው ። አማኞች መሠረታዊውን ቅድስና የሚያገኙት በፈሰሰው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ፥ በመንፈስ ቅዱስና በእግዚአብሔር ቃል ነው ። (1ኛ ቆሮ. 1 ፥ 2,30 ፥ ኤፌ.5 ፥ 26 ፥ ያዕ. 1 ፥ 18) ሆኖም በቅድስና የማደጉ ሁኔታ የእያንዳንዱን ክርስቲያን ተሳትፎ ይጠይቃል ። በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የነበሩ አማኞች ከሌላ መጠሪያ ስሞች ይልቅ በይበልጥ የሚጠሩበት ስም "ቅዱሳን " በሚል ነበር ማለት ይቻላል ። በአሁኑ ዘመን ያሉ አማኞች ግን ቅዱሳን ተብለው ለመጠራትም ሆነ ሌሎች አማኞችን ቅዱሳን ብሎ ለመጥራት እምብዛም አይደፍሩም ።

### ሐ. ክርስቲያን (ሥራ 11 ፥ 26)

ይህን ስም አማኞች ለራሳቸው መጠሪያ ያወጡት ሳይሆን በውጪ



ያሉ አሕዛቦች ያወጡላቸው ስም ነበር ። (ሥራ 11—26) ይምህ " ክርስቶሳዊ " ማለትም የክርስቶስ የሆኑ ለማለት ነው ። ክርስቲያን ተብለው ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠሩትም በአንጾኪያ ነበር ። ሆኖም "ክርስቲያን " የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ሶስት ቦታ ብቻ ተጠቅሶ እናገኛለን ። (ሥራ 11 ፥ 26 ፥ 26 ፥ 28 ፥ 1ኛ ጴጥ. 4 ፥ 16) በአሁኑ ዘመን ግን ከየትኛውም መጠሪያ ስም ይልቅ አማኞች " ክርስቲያን " በሚል ስም ይበልጥ ይጠራሉ ።

### መ. የመንገዱ ሰዎች

በዚህ ዘመን ክርስቲያኖች ጨርሶ የማይጠሩበት ስም ፥ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች የሚጠሩበት ሌላ ስም " የመንገዱ ሰዎች " ወይም " የመንገዱ የሆኑ " የሚል ነበር ። (ሥራ 9 ፥ 2 ፥ 19 ፥ 23 ፥ 24 ፥ 14,22) ይህም ስም የተገኘው ጌታ " እኔ መንገድና እውነት ሕይወት ነኝ " ካለው አባባል ሊሆን ይችላል (ዮሐ. 14 ፥ 6)

ይህም ሲባል ክርስቶስ የሚሄድበት መንገድ ሳይሆን ወደ አብ የሚያደርስ ሕይወት እንደሆነ ለማመልከት ነው ። በእርሱ በኩል ወደ አብ መድረስ አለ ። ወደ አንድ ሥፍራ ለመድረስ በተለያዩ መንገዶች መሄድና መድረስ ይቻላል ፥ ወደ አብ ለመድረስ ግን የተለያዩ መንገዶች የሉም ።

ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ሰዎች የሠሯቸው የተለያዩ መንገዶች (ሃይማኖቶች) አሉ ። አንዳቸውም ግን ወደ እግዚአብሔር እንደ ማያደርሱ ጌታ ሲያመለክት " እኔ መንገድ ሕይወት እውነት ነኝ " በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም በማለት ወደ አብ የሚያደርስ እርሱ ብቻ መሆኑን ገለጸ ። ስለዚህ " በእኔ በቀር ወደአብ የሚመጣ የለም " በማለት ሌሎች አማራጮች አለመኖራቸውን የሳያል ። ስለዚህም የመጀመሪያዎቹ አማኞች " የመንገዱ ተከታዮች " ወይም " የመንገዱ ሰዎች " በመባል በክርስቶስ ወደአብ ለመድረስ የሚጓዙ መንገደኞች መሆናቸውን ለመግለጽ ይህን ስም ተጠቅመዋል ።

ዛሬም ቢሆን በክርስቶስ ብቻ ታምነው የሚጓዙ ሰማያውያን ወደ አብ ይደርሳሉ ፥ ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ የተለያዩ መንገዶች የሉም ፥ መንገዱ አንድ ብቻ ነው ። እርሱም ክርስቶስ ነው ።

# ምዕራፍ ሁለት

# የኤክሌሽያ ልደት

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ፈቃድ የተወለደች እንጂ በሰው አሠራር የተገኘች አይደለችም ። በዓለም ላይ ብዙ ታላላቅ ሃይማኖቶች አሉ ። ጅማሪያቸውን ስናጠና ሁሉም በሰው የተመሠረቱ ናቸው ። ቤተክርስቲያን ግን በሰው ሐሳብና እቅድ የተመሠረተች አይደለችም ። እግዚአብሔር እቅዶ ያስገኛት ናት ። የማንም ሰው የሥራ ውጤት አይደለችም ።

ኤክሌሽያ የእኔ ወይም የእኛ የምትባል አይደለችም ። ኤክሌሽያ የእግዚአብሔር ናት ። (1 ቆሮ. 1፥2፥2 ቆሮ. 1፥1) በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ሥፍራ "የእኔ ቤተክርስቲያን" ወይም "የእኛ ቤተክርስቲያን" ተብላ ተጠቅሳ አታውቅም ። ስለሆነም በዚህ ክፍል ውስጥ የልደት ጊዜዋን በሚመለከት ሶስት የተለያዩ አመለካከቶችን እናያለን ።

ሀ. <u>ከብሉይ ኪዳን የቀጠለች ናት ፤</u>

ይህን ሐሳብ የሚደግፉ የሚያቀርቡት ነጥብ ቢኖር የእሥራኤል ሕዝብ ከአሕዛብ ተለይተው የተጠሩ ስለሆነ ኤክሊሺያ ልንላቸው እንችላለን የሚል ነው ።

በእርግጥ የእሥራኤል ሕዝብ ከአሕዛብ ተለይተው ለልዩ ዓላማ የተጠሩ ስለሆነ "ኤክሊሺያ" ልንላቸው እንችል ይሆናል ። ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ኤክሊሺያና የአዲስ ኪዳን ኤክሊሺያ ልዩነት አላቸው ። ምክንያቱም ጌታ ከሰጠው ምሳሌ እንደምንረዳው የአዲስ ኪዳን ኤክሊሺያ በአዲስ አቁማዳ የተጠመቀች አዲሱን የወይን ጠጅ ትመስላለች ። ማቴ. 9፥17 ያረጀው አቁማዳ የያዘው ያረጀውን ወይን ጠጅ ነው ። ያረጀው አቁማዳ የተመሰለው በብሉይ ኪዳን ማለትም በአሮጌው ኪዳን ሲሆን እንዲሁም አዲሱ አቁማዳ ደግሞ አዲሱን ኪዳን ያመለክታል ።

ስለዚህ ጌታ ለመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርት የሰጠው መልስ ይህን ይመስላል ። አቀራረባቸው "እኛና ፈሪሳውያን" ብለው "ደቀመዛሙርትህ" ሲሉ የጌታን ደቀመዛሙርት ከእርነሱ ልዩ እንደሆኑ አመል

ተዋል ። ጌታም በጥያቄያቸው ተመሥርቶ እናንተና ፈሪሳውያን በአረጀ አቁማዳ ያላችሁ ናችሁ ። ስለዚህ አዲሱን የወይን ጠጅ ባረጀ አቁማዳ የሚያኖር የለም ፤ በማለት የእርሱ ደቀመዛሙርት የሆኑትን በአዲስ አቁማዳ የተጠመቀ የወይን ጠጅ መስሉአቸዋል ። ማቴ 9.14—17

በተጨማሪም ኤፌ. 2 ፥15 ላይ እንደምንረዳው የክርስቶስ አካል የሆነች ቤተክርስቲያን ከአሕዛብና ከአይሁድ የተፈጠረች “ በአዲስ ሰው ” ትመስላለች ። ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ኤክሊሺያ የብሉይ ኪዳን ኤክሊሺያን ቅጥያ አይደለችም ማለት ነው ። ኪዳኑም ልዩ ነው ። ሕዝቡም ልዩ ነው ። (ዕብ. 8 ፥ 6—7) ጊዜው ልዩ ነው ። (ገላ. 4 ፥ 4)

ለ. በደቀመዛመርቱ ጊዜ

ሁለተኛው አቋም ኤክሌሽያ በደቀመዛሙርቱ ጊዜ ተመሥርታለች የሚል ነው ። ምክንያቱም ደቀመዛሙርቱ ክርስቶስነቱን አውቀውና አምነው ተቀብለው ከአለም ተለይተዋል የሚል ሐሳብ ያቀርባሉ ።

ነገር ግን በማቴ. 16 ፥18 ላይ የጌታን አባባል እንደምናየው ከሆነ በዚያን ጊዜ ኤክሌሽያ እንዳልተመሠረተች እንረዳለን ። ምክንያቱም “ በዚችም ዐለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እመሠርታለሁ ” ሲል ገና ወደፊት እንደሚሠራት ያመለክታል ። ይህ አባባል ” ቤተክርስቲያን ከአይሁድ የቀጠለች አለ መሆኗን ተጨማሪ መልስ ሊሆን የሚችል ነው ።

ሐ. በበአለሃምሳ ቀን

ሶስተኛው አቋም ኤክሌሺያ የተመሠረተችው በበዓለ-ሃምሣ ቀን ነው የሚል ነው ።

ቤተክርስቲያን በአካልና በሕንጻ ቤት ተመስላለች ። አንድ አካል ለመሆን በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ አስፈልጓታል ።(1 ቆሮ. 12 ፥ 13 ) መንፈስ ቅዱስ የወረደው ደግሞ በበዓለ—ሃምሣ ቀን ስለሆነ ቤተክርስቲያን የተገኘችው ወይም የተመሠረተችው በዚህ ቀን ነው ማለት ይቻላል ።

እነዚህ ደቀመዛሙርት መንፈስ ቅዱስ እስከወረደበት ቀን ድረስ ለየራስ ያሉ ብልቶችና ለየራስ ያሉ ድንጋዮች ነበሩ ። መንፈስ ቅዱስ በሠረጸ ጊዜ ግን አንድ አካል ፥ አንድ ቤተመቅደስ (ኤክሌሽያ) ለመሆን መታነጽ ተጀመረ ማለት ነው ።(1 ጴጥ. 2 ፥4 ፥ ኤፌ. 2 ፥21—22 ፥1 ቆሮ. 12 ፥ 13)

ብዙዎች የሚስማሙበት ነጥብ ይህ ነው ። በእርግጥም መንፈስ ቅዱስ የወረደው ለአገልጋዮች የአገልግሎት ኃይል ለመስጠት ብቻ አይደለም ። የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተክርስቲያንን ለማነጽና ለመገንባት ጭምር ነው ። ቤተክርስቲያን ብዙ ብልቶች ባሉት አካል ትመስላ



ለች ። ብልቶችን የሚያገጣጥም ጅማትና ሥጋ እንደሆነ ሁሉ ልዩነትን በማጥፋት በክርስቶስ አንድ አካል እንዲሆኑ ማድረግ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ። (ኤፌ. 2 ፥ 22)

የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ሊተካ የሚችል ምንም ዓይነት ሥርዓት በቤተክርስቲያን ውስጥ ሊኖር አይችልም ።

ቤተክርስቲያን በሕንጻ ቤት ትመሰላለች ። የአማኞችን ውስጣዊ ሰውነት በማገጣጠም ለእግዚአብሔር ቤተመቅደስ አድርጎ የመሥራት ድርሻ የተሰጠው ለመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ። (1 ጴጥ. 2 ፥4 ፥ ኤፌ.2 ፥22) ብልቶች በጅማት ተያይዘው አካል እንደሚሆኑ ሁሉ ፥ መንፈስ ቅዱስ አማኞችን ውስጣዊ ሕይወታቸውን በማያያዝና በማገጣጠም የክርስቶስ አካል በማድረግ ይሠራል ማለት ነው ። (1 ቆሮ. 12 ፥ 13)

# ምዕራፍ ሦስት
# የኤክሌሽያ መሠረት ገፅታ

## ክፍል 1 የኤክሌሽያ መሠረት

ስለቤተክርስቲያን መሠረት ማንነት ስናነሳ የተለያዩ አቋሞችን እናያለን።

**ሀ. የካቶሊክ ቤተክርስቲያን አመለካከት ፤**

የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን የመሠረተው በጴጥሮስ ላይ ነው የሚል እምነት አላት ። ይህም በማቴዎስ 16 ፥ 18 ላይ “ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህ አለት ላይ ቤተክርስቲያን እሠራለሁ ” የሚለውን ሐሳብ በመውሰድ ነው ። ጴጥሮስ ማለት አለት ማለት ነው ። ስለዚህ አንተ ጴጥሮስ ነህ ፥ በአንተ ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ ማለት ነው ብለው ይተረጉማሉ ።

**ለ. የሌሎች አብያተ ክርስቲያናት አመለካከት ፤**

ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን በስተቀር ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የሚቀበሉትና የሚስማሙት የቤተክርስቲያን መሠረት ክርስቶስ እንደሆነ ነው ።

**ሐ. የማቴ. 16 ፥ 18 ትርጉም ፥**

“ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚችም አለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ ” የሚለው አባባል በማስተዋል ካልተመለከትነው በስተቀር አስቸጋሪ ይመስላል ። በዚህ ሥፍራ ጌታ “ ጴጥሮስ ” የሚለው ቃልና “ አለት ” የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ የተለያዩ ቃላትን ነው የተጠቀመው ። ስለዚህ ጴጥሮስና አለት የሚለውን ቃል በግሪኩ እንደ ተጻፈ አድርገን ብናነብ እንዲህ ሆኖ እናገኘዋለን ።

“ አንተ ፔትሮስ ነህ ” በዚችም “ ፔትራ ” ላይ ቤተክርስቲያኔን አመሠርታለሁ ” የሚል ነው ። ትርጉሙም ፔትሮስ ድንጋይ ማለት ሲሆን ፔትራ ማለት ደግሞ አለት ማለት ነው ።

በአማርኛችንም እንደምንረዳው አለቱን ድንጋይ እንል ይሆናል ። ድንጋዩን ግን አለት አንልም ። ድንጋይ በእጅ ሊነሳ የሚችል

ዓይነት ሲሆን ፣ አለት ግን ትልቅ ቋጥኝ ነው ። ስለዚህ ጌታ “ አንተ ፔትሮስ ነህ ” በዚህ “ አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ” ባልከው ፔትራ ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ ማለት እንደ ሆነ ግልጽ ነው ።

መ. <u>ስለ ኤክሌሽያ መሠረት የጴጥሮስ መረዳት ፣</u>

ጴጥሮስ ራሱ በግልጽ የቤተክርስቲያን መሠረት ክርስቶስ መሆኑን አስረድቷል ። (1 ጴጥ. 2 ፣ 4) አንድ ጊዜም እንኳን የቤተክርስቲያን መሠረት እርሱ እንደሆነ ጠቅሶ አያውቅም ።

ሠ. <u>የጳውሎስ መረዳት ፤</u>

ሐዋርያው ጳውሎስ “ ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልም ፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ” ይላል (1 ቆሮ. 3 ፣ 11) “ ከተመሠረተው በቀር ” ሲል ሌላ ሊመሠረት እንደማይችል እያረጋገጠ ይህም የተመሠረተው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ይገልጻል ።

የገሃነም ደጆች አይችሏትም የተባለችው ቤተክርስቲያን መሠረቷ ክርስቶስ ስለሆነ ነው ። እርሱ ደግሞ የተፈተነ ፣ የከበረ ፣ የጸና የማዕዘን ድንጋይ ነው ። (ኢሳ. 28 ፣ 16) ስለዚህ በእርሱ የሚያምን አያፍርም ፣ አይ ናወጥም ፣ አይሰጥምም ። ጴጥሮስ ከአንዴም ሁለቴ ተረትቷል ። ጌታውን የካደ ጴጥሮስ በሌላ ጊዜ ደግሞ አይሁዶችን ፈርቶ ሲያፈገፍግ ጳውሎስ ዓይቶ በተግሣጽ ወደ እውነት እንደመለሰው እናያለን ። (ገላ. 2 ፣ 11—14) ጴጥሮስ ራሱ የጸናው በራሱ ብርታት ሳይሆን በጌታ ምልጃና ጸሎት ነው ። ሉቃ. 22 ፣ 31—32 ታዲያ የክርስቶስ አካል የሆነች ቤተክርስቲያን ሟች በሆነ ሰው ላይ እንዴት ትመሠረታለች ? ።

## <u>ክፍል 2 የኤክሌሽያ ገጽታ</u>

ስለ ኤክሊሺያ ስናጠና ሁለት መልክ እንዳላት ማሰባችንን እንተው ። አንደኛው መልኳ የማትታየዋ ኤክሊሽያ ስትሆን ፣ ሁለተኛዋ መልክ ደግ ሞ የምትታየዋ አጥቢያ ኤክሌሽያ የምንላት ናት ። ስለዚህ ሁለቱንም በማ ነጻጸር እናያለን ።

ሀ. <u>የማትታየዋ ኤክሌሽያ ፣</u>

1. በጌታ የተደራጀች ናት ። (ማቴ. 16 ፣ 18) ድርጅታዊ መዋቅር የላትም ። መሪዋ አንድ ክርስቶስ ነው ።



2. በዘመናት ውስጥ በክርስቶስ ደም የተዋጁትን ሁሉ ታጠቃልላ ለች ። ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍት የተጻፉትን ብቻ የያ ዘች ናት ።
3. <u>በጊዜና በቦታ አትወሰንም</u> ፣ በጊዜ አትወሰንም ፣ ምክንያቱም በሐዋርያት ዘመን የነበረች በመካከለኛው ዘመን ያለች አትባ ልም ፣ ዘለዓለማዊ ናትና ።

   በቦታ አትወሰንም ፣ ምክንያቱም በኢየሩሳሌም ያለች ፣ በአንጾ ኪያ ያለች ፣ በኢትዮጵያ ያለች አትባልም ። ዓለም አቀፋ ዊም አንላትም ። ምክንያቱም በዚህች ዓለም አትወሰንምና ። ነገር ግን ሰማያዊና ዘለዓለማዊ ናት ። (ዕብ. 12 ፣ 12 ፣ ራዕ. 19 ፣ 17)
4. የአባላቷ ቁጥር አይታወቅም ፣

   የዚህችን የማትታይ ቤተክርስቲያን አባላት ቁጥር ከጌታ በስ ተቀር የሚያውቅ ማንም የለም ። ከየአጥቢያዎች ያሉትን ብቻ ሳይሆን በግልም ጌታን አውቀው የዳኑትን ሁሉ ታጠቃልላ ለች ። ያልዳነ የዚህች ቤተክርስቲያን አካል ሊሆን አይችልም።
5. አንድ ብቻ ናት (ኤፌ. 4 ፣ 4)

   በቦታም ሆነ በስም ወይም በድርጅት የተከፋፈለች አይደለችም። ልዩነት በአባሎቿ መካከል የለም ። የሐሳብ ግጭት መለያየት የለም ። አምባገነኖች የሆኑ መሪዎች የሉም ፣ ሁሉም ለአንዱ ጌታ የሚገዙ ናቸው ። ስለዚህ በአስተዳደር መለያየትና መጋ ጨት የለም ። በአገልግሎት ምክንያት መለያየት አይኖርም ።

ለ. የምትታይ አጥቢያ ኤክሌሽያ ፣

1. በአገልጋይ የምትደራጅ ናት ። (ቲቶ 1 ፣ 5) ይህ ማለት የሰው የሥራ ውጤት ናት ማለት አይደለም ። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የጌታ አገልጋዮች ያደራጇዋታል ማለት ነው ። ስለዚህም አደረ ጃጀትዋ እንደየቦታውና እንደየአገሩ የተለያየ ሊሆን ይችላል ።
2. ያልተዋጁ ማለትም ያልዳኑ አባላት ሊኖሯት ይችላሉ ። (ፊል. 3 ፣ 2 2 ቆሮ. 11 ፣ 26 ፣ ገላ. 2 ፣ 4) በሐዋርያትም ጊዜ እንኳን እያስመሰሉ ሾልከው ወደ የአጥቢያዎች ይገቡ እንደነበረ ሐሰ ተኞች ወንድ ሞች ዛሬም ቢሆን ሾልከው ይገባሉ ። ይህ እስከ መከር ድረስ እስከ ጌታ ዳግም ምጽአት የሚቀጥል ነው ። ለይ ተን እናውጣቸው ብንል አዳጋች ይሆንብናል ። (ማቴ. 13 ፣ 24 30:47—49)

3. በጊዜና በሥፍራ የተወሰነች ናት ፤

በጊዜ የተወሰነች ናት ፤ ምክንያቱም የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ስንል የጌታን ስም በመጥራትና በማመን በአንድ አካባቢ ለአምልኮ እና ለአገልግሎት የሚሰበሰቡ ምዕመናን ነው ። የተሰሎንቄ ፤ የቆሮንቶስ ፤የገላትያ ፤ ወዘተርፈ አብያተክርስቲያናት የተባሉት በሥፍራ መወሰናቸውን ያመለክታል ። ዛሬም የአዲስ አበባ ፤ የደብረዘይት ፤ የናዝሬት ወዘተርፈ . . አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የምንላቸው በሥፍራ የተወሰኑ እንደሆነ ለማመመልከት ነው ።

4. የአባሎች ቁጥር ይታወቃል ፤

ሁሌም አጥቢያዎች የየራሳቸው የአባላት ስም የያዘ መዝገብ ሊኖራቸው ይችላል ። የማይኖራቸውም ሊኖሩ ይችላሉ ። ሆኖም በአንድ አጥቢያ ያሉትን አባላት ምን ያህል እንደሆኑ ቆጥሮ መድረስ ይቻላል ።

5. ብዙ አጥቢያዎች አሉ ፤

በአሁኑ ዘመን የአጥቢያዎች ብዛት በዓለም ውስጥ ቁጥራቸው እጅግ በጣም የበዙ ናቸው ። አጥቢያ ቤተክርስቲያን የሌለባቸው አገሮች ካሉም ምን አልባት እጅግ በጣም ጥቂት አገሮች ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ ።



# ምዕራፍ አራት

# ኤክሌሽያ የምትመሰልባቸው ምሳሌዎች

የቤተክርስቲያንን ሁኔታ ለመግለጽ ብዙ የተለያዩ ነገሮች በምሳሌነት ተጠቅሰዋል ። እነዚህም በምሳሌነት የተጠቀሱትን ነገሮች ለይቶ ማወቅ ይጠቅማል ።

ለምሳሌ ጌታ በእርሱ ያመኑትን ቅዱሳንን ለመግለጽ በበጐች ሲመስላቸው አመጸኞችን ደግሞ በፍየሎች ይመስላቸዋል ። ራሱን በበጐች በር በመንገድ ፤ በወይን ግንድ መስሏል ። እነዚህን ነገሮች ቃል በቃል የምንወስዳቸው ሳይሆን ምሳሌነት ያላቸው አባባሎች ስለሆኑ ልንተረጉማቸው ያስፈልጋል ።

## ክፍል 1 <u>የማትታየውና የምትታየው ኤክሌሽያ በጋራ የተመሰሉባቸው ምሳሌዎች</u>

የማትታየው ቤተክርስቲያንና አጥቢያ ቤተክርስቲያን በጋራ የተመሰሉባቸው ሶስት ምሳሌዎች ሲኖሩ አጥቢያ ቤተክርስቲያንን ብቻ ለማመልከት የተሰጡ ምሳሌዎች አሉ ። እነዚህን በተናጠል እናያለን ።

ሀ. በሙሽራ (በሚስት) ራዕ. 19 ፥ 7 ፤ ኤፌ. 5 ፥ 21—33)

በክርስቶስና በቤተክርስቲያን መሐከል ያለውን መንፈሳዊ ሁኔታ ለማስረዳት ክርስቶስ በባል ሲመሰል ቤተክርስቲያን ደግሞ በሚስት ተመስላለች ። ይህን ሁኔታ ቃል በቃል የምንወስደው ነገር አይደለም ። ሆኖም ጥልቅ መንፈሳዊ ምሳሌነት እንዳለው እናያለን ።

ጥንትም በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ ተብለው የተጠሩት እሥራኤላውያን በሚስትነት ሲመስሉ እግዚአብሔር ደግሞ በባል ተመስሏል ። (ኢሳ. 54 ፥ 4—5 ፤ ኤር. 3 ፥ 14) ሕዝቡ እግዚአብሔርን ትተው ጣኦትን ሲከተሉና ሲያመልኩ ደግሞ በአመንዝራ ሴት ተመስለው እናያለን ። (ሆሴ. 2 ፥ 4 ፤ ኤር. 3 ፥ 1—5) ስለዚህ ይህ ጽንሰ—ሐሳብ በብሉይ ኪዳንም የነበረ ነው ማለት ይቻላል ።

ዋናው ቁም ነገር የእሥራኤል ሕዝብም ሆኑ ቤተክርስቲያን በሚስት የተመሰሉበትን ምስጢር ማወቅ ነው ። ለዚህ ደግሞ በባልና በሚስት መካከል ያለውን ዝምድና ማወቅና መረዳት በክርስቶስና በቤተክርስቲያን መካከል ያለውን ምስጢር ለመረዳት ያስችለናል ።

በኤፍ. 5 ፥ 21—33 ያለውን ክፍል ወስደን ብናይ በሁለቱም አቅጣጫ ሰፊ ግንዛቤ ለማግኘት እንችላለን ። በዚህ ሥፍራ ባል እንደራሱ ሥጋ አድርጎ ሚስቱን ይወዳል ይላል ። በእርግጥም ሰው ለሰው ያለው ፍቅር መለካት ቢቻል ባል ለሚስቱ ያለው ፍቅር ለሌላ ሊኖረው እንደ ማይችል የተረጋገጠ ነው ። ሰው የሚወደውን ነገር ማንም እንዲጋራበት አይፈልግም ። ማንም ሰው ሚስቱ ከእርሱ ሌላ ወዳጅ እንዲኖራት አይፈቅድም ። ባል በሚስቱ ነገር ሕይወቱን ይሰጣል ። ይህም የሚያሳየው ባል ለሚስቱ ያለውን የፍቅር ብርታት ነው ።

ይህንን ባህርይ በሰው ሕይወት ውስጥ የፈጠረ እግዚአብሔር ነው ። ሆኖም ሰው በኃጢአት የተበከለና በአመጽ የተሞላ ስለሆነ ይህን ጥልቅ ሚስጢር ማወቅ ተስኖታል ። ቢሆንም ቤተክርስቲያን ምን ያህል በጌታ የተወደደች እንደሆነ ለማመልከት በሚስት ተመስላለች ።

ክርስቶስ ነፍሱን ስለ እርስዋ በመስጠት ፍቅርን ገልጾአል ። (ዮሐ. 15 ፥ 13 ፥ ኤፌ. 5 ፥ 26) ፍቅሩን መግለጽ ብቻ አይደለ ፍቅሩን ሠጥቷል ሰውም ስለሚወዳት ሚስት ራሱን በመስጠት ፍቅሩን መግለፅ ይችል ይሆናል ። ፍቅሩን ግን ለመስጠት የሚችል ማንም የለም ። ክርስቶስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በሚያምኑት ሰዎች ልብ ውስጥ አፍስሶ ያሳያል ። (ሮሜ5 ፥ 5 ፥ 1 ዮሐ. 3 ፥ 1)

ቤተክርስቲያን በሚስት የተመሰለችበት ሁለተኛው ነጥብ ያለነውርና ያለነቀፋ መሆኗን ለመግለጽ ነው ። በአይሁድ ሕግ ሴት ባሏን ፈትታ ሌላ ባል ካገባች አመንዝራ ሴት እንጂ " ሚስት " የሚያሰኛትን የከበሬታ ስም ታጣለች ። (ዮሐ 4 ፥ 16—18) ድንግልናዋንም ካጣች እንደነውረኛ ተቆጥራ በድንጋይ ተወግራ ትሞታለች ። (ዘዳ. 22 ፥ 20—21) ለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተክርስቲያን እንደ ንጽሕት ድንግል ልጃገረድ ተመስላ ለክርስቶስ ያላትን ንጽህናና ቅድስና ሳይረክስ ተጠብቃ እንድትቀርብ አስጠንቅቋል።(2 ቆሮ. 11 ፥ 1—2) ይህ ማስጠንቀቂያ ደግሞ በጌታ የሚያምኑን ሁሉ እንጂ በቆሮንቶስ ያሉትን አማኞች ብቻ የሚመለከት አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። ስለዚህ በየትም ያለች ቤተክርስቲያን ክርስቶስን ብቻ ስትከተልና ለእርሱ ብቻ ስትገዛ በሚስት ፥ በ ሙሽራ ፥ በንጽሕና ድንግል ልጃገረድ ትመሰላለች ። አለበለዚያ ግን በብሉይ ኪዳን እንዳየነው ሁሉ በአዲስ ኪዳንም በአመንዝራ ሴት ልትመሰል ትችላለች ።



በአዲስ ኪዳን የምናገኛት በአመንዝራ ሴት የተመሰለች አለች ፥ ማናት ? (ራዕ. 17 ፥ 1—18) ይህቺ ሴት በብዙ ሁኔታ ተመስላ ተጠቅሳለች ።

1. በብዙ ውሃዎች ላይ የተቀመጠችን ሴት (17 ፥ 1) ይኸውም በብዙ ሕዝብ ላይ የተቀመጠች መሆኗን ሲገልጽ ነው ። (17 ፥ 15)

2. ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ባሉት አውሬ ላይ የተቀመጠች ሴት ፥ የተቀመጠችባቸው ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉት አውሬና ሰባት ተራራዎች በነገሥታት ተመስለዋል ። (17 ፥ 3,9—12)
   የእሥራኤል ሕዝብ በዛፎች ሥርና በኮረብታዎች ላይ በመሰዋታቸው ከዛፍና ከኮረብታዎች ጋር እንዳመነዘሩ እንደተቆጠረ ሁሉ ይህች ሴት ከምድር ነገሥታት ጋር በመወዳጀቷ ከምድር ነገሥታት ጋር እንዳመነዘረች ተቆጥራለች ። (17 ፥ 2)

3. ሴቲቱ ጋለሞታ ሆና የብዙ ጋለሞታዎችና የምድር ርኩሰት እናት ተብላለች ። (17 ፥ 5)

   ይህም ጋለሞታ ማለትም በአመንዝራ ሴት የተመሰሉ በሥራ እሷን የመሰሉ ብዙዎች እንዳሉ ሲያመለክት ነው ።

4. የዚህች ሴት ሌላ መጠሪያ ስም ባቢሎን ነው ። (17 ፥ 5)
   ባቢሎን ማን ናት ? ብንል ባቢሎን ለእግዚአብሔር መገዛት እንቢ ያለች አመጸኛ የጥንት ከተማ ናት ። የስሟም ትርጉም " ግራ መጋባት " ወይም " የተደበላለቀ " ማለት ነው ። ይህች ሴት በባቢሎን መመስሏ ለእግዚአብሔር ለመገዛት እምቢ ያለች ድብልቅልቁ የወጣ አመጸኛ መሆኗን ለማመልከት ነው ።

5. ይህቺ በአመንዝራ ሴት የተመሰለች በክርስቶስ ምስክሮች ደም ሰክራ መገኘቷ ሌላ መለያዋ ነው ። (ራዕ. 17 ፥ 6) ማለትም የቅዱሳንን ደም አፍስሳለች ። (ራዕ. 18 ፥ 24)

6. ይህቺ ሴት እራስዋን እጅግ ያከበረች ናት ። በብሉይ ኪዳን በሚስትም ሆነ በአመንዝራ ሴት የተመሰለ የእሥራኤል ሕዝብ ነበር ። አሁንም በአዲስ ኪዳን በሚስትም ሆነ በአመንዝራ ሴት የተመሰለች ቤተክርስቲያን ናት ለማለት አያዳግትም ። እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን በሚስት ስትመስል " ቤተክርስቲያን " የሚል ስም ይዛ ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱትን ስትፈጽም የቆየች አመንዝራ ቤተክርስቲያን አለች ማለት ነው ። የትኛዋ ቤተክርስቲያን እንደሆነች ለማወቅ ታሪክን መመርመር ያስፈልጋል ። አንዳንድ አስተማሪዎች ይህች በአመንዝራ የተመሰለች ዓለም ናት ይላሉ ። ነገር ግን የዚችን

አመንዝራ ሴት ሁኔታ ስናይ በብዙ ውኃዎች ላይ ተቀምጣ እናያ ለን ። ይህ ደግሞ የሚያሳየው በምድር አህዛብ ላይ መሰልጠኗ እንደ ሆነ ቀደም ሲል ዓይተናል ። (ራዕ. 17 ፡ 1 15 ) ስለዚህ ዓለም ራሷ በራሷ ላይ ተቀምጣለች ብንል ትርጉም አይሰጠንም ። ከዚህ ጋር ደግሞ ይህቺ ሴት በነገሥታት ላይ ተቀምጣ ዓይተናል (ራዕ. 17 ፡ 3.12) ስለዚህ ነገሥታት በዓለም ላይ ይነግሣሉ ፣ ይሠለጥናሉ እንጂ ዓለም በነገሥታት ላይ እንደማትሠለጥን ግልጽ ነው ።

## ለ. በአካል ትመሰላለች (ኤፌ. 4 ፡4) ፣

ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን ብዙ ቦታ በአካል እየመሰል ጠቅሷል ። አብሮም በማያያዝ የሚገልጻቸው ነገሮች ኣሉ ። ቤተክ ርስቲያን ለምን በሰው አካል ትመሰላለች ?

1. ክርስቶስ ብቻ የበላይ መሪ መሆኑን ለመጥቀስ ነው ።

ቤተክርስቲያን በአካል ምሳሌነት አድርጐ ሲያቀርብ አብሮ አያይዞ ክርስቶስ የአካል ማለት የቤተክርስቲያን “ራስ ” እንደሆነ ይጠቅሳል ። (ኤፌ. 1 ፡22 . 4 ፡14—16, 5 ፡23 ፣ ቆላ. 1 ፡ 18) በአንድ አካል ላይ ብዙ ብልቶች ሲኖሩ ለብልቶች ሁሉ የበላይ የሚሆን “ ራስ ” ግን አንድ ብቻ ነው ። በተመሳሳይ ሁኔታ ማኅበረ - ምዕመናን በቁጥር ብዙዎች ሲሆኑ የሁላቸውም የበላይ ገዢና አጻኸ አንዱ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ያመለክታል ። በተጨማሪም ብልቶች ያለ ራስ ምንም ማድረግ እንደ ማይችሉ ሁሉ አማኞች ያለ ክርስቶስ ምንም ማድረግ እንደማይችል ለማስገኘዘብም ነው ።

የወይን ቅርንጫፍ ያለ ግንድ ሊያፈራና ሕይወት ሊኖረው አይ ችልም ። (ዮሐ. 15 ፡ 5) ብልቶችም ያለ ራስ ሊሠሩና ሊንቀሳቀሱ አይችሉም ። የቅርንጫፎች ሕይወት ከግንዱ ጋር የተያያዘ ነው ። የብልቶችም ሕልውና ከራስ ጋር የተያያዘ ነው ። ስለዚህ ቅርንጫ ፎች ያለ ግንድ ፣ ብልቶችም ያለ ራስ መኖር እንደማይችሉ ሁሉ ክር ስቲያኖች ያለ ክርስቶስ ሕይወት ሊኖራቸው አይችልም ። ይህን ለማ መልከት በእርሱ የሚያምኑ በአካል ሲመሰሉ ፣ ክርስቶስ ደግሞ በራስ ተመስሏል ።

2. የማኅበረ ምዕመናንን መደጋገፍና መቀራረብ ለማመልከት ነው ። ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን በአካል መስሉ የሚጠቅሳቸ ውን ጥቅሶች በጥንቃቄ ስንመረምር አብሮ አያይዞ መግለጽ የሚፈ



ልገው ሌላ ነገር የአማኞች ኀብረትና መደጋገፍ ምን እንደሚመስልና ምን መምሰል እንዳለበት ለማስገንዘብ እንደሆነ እንረዳለን። ( ሮሜ 12 ፡ 4—6 ፣ 1 ቆሮ. 12 ፡ 14—26)

በሮሜ 12 ፡4—6 ላይ ብልቶች ብዙዎች ሆነው ሳለ የእያንዳንዳቸው ተግባር የተለያየ እንጂ አንድ አለመሆኑን ይገልጻል ። በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዳቸው እንደሚደጋገፉ ያሳያል ። (ሮሜ 12 ፡5) በተመሳሳይ ሁኔታ አማኞች ብዙዎች ሆነው ሳለ ለእያንዳንዳቸው በመንፈስ ቅዱስ የተሰጣ ቸው የተለያየ አገልግሎት እንጂ አንድ ዓይነት ብቻ አለመሆኑን ያሳያል ። በተሰጣቸው የጸጋ ስጦታ ደግሞ እያንዳንዳቸው በትጋት እንዲያገለግሉ ያስገነዝባል ። ስለዚህ አንዱ ለሌላው እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እናያለን ። በ1ኛ ቆሮ. 12 ፡ 14—26 ላይ የምንረዳው ነገር ቢኖር አንድ ብልት የበታችነት ስሜት ተሰምቶት ወይም በሌላ ምክንያት የአካል ክፍል አይደለሁም ማለት እንደማይችልና (12 ፡ 14—16) በሌላ በኩል ደግሞ ሌላው ብልት የበላይነት ተሰማቶት በመናቅ ሌላውን “ አታስፈልግም ” ማለት እንደማይችል ያስረዳል (12 ፡21—26) ። ስለዚህ ብልቶች እርስ በእርሳቸው በትክክል እንደሚተሳሰቡ እንጂ በመካከል መለያየት እንደሌለ ሁሉ ፣ አማኞችም እንዲሁም እርስ በእርሳቸው እንደብልቶች ሆነው በእኩልነት መደጋገፍና መተሳ ሰብ እንዳለባቸው ያስገነዝባል ።

## ሐ. በሕንጻ ቤት ትመሰላለች (1 ቆሮ. 3 ፡9) ፣

ቤተክርስቲያን በሕንጻ ቤት የተመሰለችው የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት እንደ ሆነች ለማመልከት ነው ። ( ኤፌ. 2:22) ፡6 ፣ 1 ቆሮ . 6፡ 19 ) በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ቤተክርስቲያን ነች ። (1 ቆሮ. 3 ፡16 )

በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ቤተመቅደስ መካከል ልዩነት አለ ። ያለውንም ልዩነት በማነጻጸር ብናይ ፡—

1. የብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ ከግዑዝ ድንጋይና እንጨት የተሠራ ሲሆ ን ፣ የአዲስ ኪዳን ቤተመቅደስ ግን ከሕያዋን ድንጋዮች በተመሰሉ አማኞች የተሠራ ነው ። (1 ጴጥ. 2 ፡4—5)
2. የብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ በሰዎች የተሠራ ሲሆን ፣ የአዲስ ኪዳን ቤተመቅደስ በመንፈስ ቅዱስ የተሠራ ነው ። (ኤፌ. 2 ፡22)
3. የብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ መሠረት ግዑዝ ድንጋይ ሲሆንየአ ዲስ ኪዳን ቤተመቅደስ ግን ክርስቶስ ነው ። (ማቴ. 16 ፡8 ፡1ኛ ቆሮ. 3 ፡ 11)

4 በብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ የሚቀርበው መስዋዕት ሥጋዊ ሲሆን ፣ በአዲስ ኪዳን ቤተመቅደስ ግን መንፈሳዊ ። (1ኛ ጴጥ. 2 ፡ 4—5)

5 የብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ ፈርሶ የቀረ ሲሆን ፣ የአዲስ ኪዳን ቤተ መቅደስ ግን ለዘለዓለም ጸንቶ የሚቆይ ነው ። (ማቴ. 16 ፡ 18 ፡ 1ኛ ቆሮ. 3 ፡ 17)

## ክፍል 2 የምትታየው ኤክሌሽያ ብቻ የተመሰለችባቸው ምሳሌዎች ፣

አጥቢያ ቤተክርስቲያን (አማኞች) በብዙ ነገር ተመሥላለች ከእነ ዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን ወስደን እናያለን ።

### ሀ. በዓሣ ማጥመጃ መረብ ትመስላለች ።

ብዙውን ጊዜ ጌታ ለሕዝቡ በተፈጥሮአዊ ነገርና ዕለት በሚያዩትና በሚያደርጉት ነገር በምሳሌነት በመጥቀስ ጥልቅ መንፈሳዊ ምስ ጢር ያስተምራቸው ነበር ።

ስለዚህ በማቴ. 13 ፡ 47 ላይ ያለውን ምሳሌ የመሰለው በባህር አጠ ገብ ተቀምጦ ነበር ። በዚህ ሥፍራ ቤተክርስቲያንን በምድር ላይ ያለ የመንግሥተ ሰማያት መጠቀሚያ ዕቃ ወይም በመረብ መስሎ ያቀርባ ታል ። ባህር ደግሞ ብዙውን ጊዜ ሕዝብን ይወክላል ። (ራዕ. 17 ፡ 15)

ይህች ወደ ባህር የተጣለች መረብ ከሁሉ ዓይነት ነፍሳትን ሰብስባ የያዘች እንደሆነች ሁሉ እንደዚሁም በምድር ላይ ያለች ቤተክርስቲያን የዳኑትንም ያልዳኑትንም ነፍሳት የያዘች መሆኗን ያሳያል ።

ምክንያቱም የዳኑትንና ያልዳኑትን መለየት በምድር ያለች ቤተክር ስቲያን ኃላፊነትና ችሎታም የላትም ። የዚህ መብት ባለቤት ጌታ ብቻ ነው ። (ያዕ.4 ፡ 12 ፣ ማቴ. 7 ፡ 1—5) እስከ ዳግም ምጽዓት ሁሉም አብሮ ተደባልቆ እንዲቆይ ፈቅዷል ። ( ማቴ. 13 ፡ 30)

### ለ. በስንዴ አዝመራ ትመስላለች ።

በማቴ. 13 ፡ 24—30 ፡ 36—43 እንደምንመለከተው ደቀመዛሙር ቱን በዕለታዊ ኑሮአቸው ከሚያዩት የስንዴ አዝመራን በምሳሌነት በመጥ ቀስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር ያስተምራቸዋል ።

• በዚህ ምሳሌ ውስጥ የምናያቸው ነገሮች አሉ ፡—

(1) ሰፊ ማሣ ፣
(2) የስንዴ አዝመራ ፣
(3) በስንዴው ውስጥ ተደባልቆ የተዘራ የእንክርዳድ ዘር ፣



(4) ስንዴውን የዘራ ሰው ፣
(5) እንክርዳዱን የዘራ ጠላት ፣

ጌታ ከሰጠው ምሳሌ ትርጉም እንደምንረዳው ፦

(1) ማሣው ዓለም ነው ፣
(2) መልካም ዘር ማለትም የስንዴ አዝመራ አማኞች ናቸው ፣
(3) እንክርዳዱ ውሸተኞች ፣ ሾልከው የገቡ ክፉዎች ናቸው (ገላ. 2 ፡ 4)
(4) መልካም ዘር የዘራው ራሱ ጌታ ነው ፣
(5) እንክርዳዱን የዘራው ዲያብሎስ ነው ።

ከዚህ ምሳሌ እንደምንረዳው ጠላት ዲያብሎስ የራሱ የሆኑትን መል ዕክቶች በእግዚአብሔር ልጆች መሐል መልካም አስመስሎ እንደሚያስ ቀምጥ ነው ። (2ኛ ቆሮ. 11 ፡ 14) ከዚህ የተነሳ ሁለቱን ወዲያው ለመለ የት ለሰው አስቸጋሪ ነው ። እንዚህን ሰው ለመለየት ቢፈልግ እውነተኞ ችን ጨምሮ ሊጐዳ ስለሚችል የፍርድ ቀን እስኪመጣ ድረስ በትዕግሥት መጠበቅ እንዳለብን ያሳስባል ። (ማቴ. 13 ፡ 29—30)

### ሐ. በእርሻ ትመስላለች ።

ሐዋርያው ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን " የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ " ይላል ። (1 ቆሮ. 3 ፡ 6,9) በማቴ. 13 ፡ 3—9, 18—23 እን ደምናየው ደግሞ ቃሌን የሚሰሙት ሰዎች በአራት የተለያዩ ቦታዎች ተመስለዋል ። በዘር የተመሰለው ቃሉ ነው ። ከአራቱ ሥፍራዎች ዘሩን ያበቀለውና ፍሬ ያፈራው አራተኛው ሥፍራ ብቻ ነው ። ይህም ፍሬ ማፍ ራት ደግሞ ቃሉን ሰምቶ በቃሉ መኖር ሲያመለክት ነው ። (ማቴ. 13 ፡ 23, ዮሐ. 15 ፡ 7—8) ቃሉ በዘር ተመስሏልና ።

እንግዲህ ማሣ ዘር እንደሚያስፈልገው እንዲሁም አማኞች የእግዚ አብሔር ቃል ያስፈልጋቸዋል ። ቃሉን ሰምቶ ማስተዋል ከሌለ ደግሞ ፍሬ ሊያፈራ የሚችል የለም ።

ማሣ ዘር ካልተዘራበት ዝናብ ብቻ ቢዘንብበት አይጠቅምም ። አረም ሊያበቅል ይችል ይሆናል ። እንዲሁም አማኞች የቱን ያህል በሰማያዊ በረከት ቢረሰርሱ የእግዚአብሔር ቃል ከሌላቸው በሕይወታቸው ፍሬ ሊኖራቸው አይችልም ። ወደ ተሳሳተ ትምህርት በቀላሉ ሊወሰዱ ይች ላሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ በሕይወታቸው የእግዚአብሔር በረከት ካልዘ ነበ ቃሉ ቢዘራ ቃሉ በሕይወታቸው ሊያድግና ፍሬ ሊኖረው አይችልም፣ ማለትም እንደ ቃሉ ሊኖሩ አይችሉም ። የመንፈስ ቅዱስ በረከት ያስፈል ጋቸዋል።ስለዚህ ለእርሻ ዘርና ዝናብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ (ዘካ.10፡1) ለአማኞችም የእግዚአብሔር ቃልና የመንፈስ ቅዱስ በረከት እንደሚያስ ፈልጋቸው ለማስገንዘብ አማኞች በማሣ ተመስለዋል ።

# ምዕራፍ አምስት

## የኤክሌሽያ ድርጅታዊ ገፅታ

ኤክሌሽያ ድርጅት ናት ማለት እንችላለን ? ይህንን ለመመለስ በመጀመሪያ ድርጅት ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል፣ ወይም ድርጅት ሊኖረውና ሊይዝ የሚገባውን ነገሮች ማለየት አለብን ።

### ክፍል 1 ፣ ድርጅት ምን መልክ አለው ?

ድርጅት የምንለው አንድን ዓላማ ወይም ሥራን ለማከናወን የተመሠረተ ተቋም ነው ።

ሀ. ድርጅት ሊኖሩት የሚገቡ ነገሮች ፣

(1.) ግልፅ የሆነ ዓላማ ፣

(2 ) ወደ ዓላማ የሚያደርሱ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች ፣

(3) የተለያየ የሥራ እውቀትና ልምድ ያላቸው ሰዎች ፣

(4) ሥራውን የሚያንቀሳቅሱበት ገንዘብና ቁሳቁስ ፣

(5) የአስተዳደር መዋቅር ሊኖረው ይገባል ።

እነዚህን ያላሟላ ከሆነ ድርጅት ሆኖ ሊንቀሳቅስ አይችልም ። እንግዲህ ከዚያ አኳያ ቤተክርስቲያን ስንመለከት ድርጅታዊ መልክ አላት ማለት እንችላለን ።

ለ. የኤክሌሽያ ድርጅታዊ መልክ ፦

1. ኤክሌሽያ ዓላማ ወይም ተልእኮ አላት ። ( ኤፌ. 4 ፣ 13 ) ዓላማዋም ከኤፌ.

4፡13 እንደምንረዳው ፦

1.1 በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ወደ ሚገኘው አንድነት መድረስ ፣

1.2 ቅዱሳንን ሁሉ ለአገልግሎት ማዘጋጀት ፣
1.3 ወደ ክርስቶስ ሙላት ልክ መድረስ ነው ።

2. ይህን ዓላማ ለማስፈጸም የተለያዩ አገልጋዮች አሏት ። እነዚህም በኤፌ. 4፡11 - 12 ላይ እንደምንመለከተው ፡—

   2.1 ሐዋርያ ፣
   2.2 ነቢያት ፣
   2.3 ወንጌል ሰባኪዎች ፣
   2.4 አስተማሪዎችና እረኞች ናቸው ።

   እነዚህ የቤተክርስቲያን ዋና ዋና አገልጋዮች እንደ ሆኑ ለመጥቀስ እንጂ በመሠረቱ አማኞች ሁሉ በተሰጣቸው ፀጋ ልዩ ልዩ አገልግሎት አሏቸው ። ( ሮሜ 12፡4-8 ) ቆሮ12 ፡ 4 - 11

3. ኤክሌሽያ ወደሚጠበቅባት ግብ ለመድረስ የተለያየ አገልግሎት አላት ። እነዚህም ወንጌል መስበክ ፣ ማስተማር ፣ መምከር፣ ማስተዳደር የመሳሰሉት ናቸው።( ሮሜ 12 ፡ 4-8 )

4. ኤክሌሽያ እነዚህን አገልግሎት ለመፈጸም ገንዘብ ያስፈልጋታል ። ምዕመናን እሥራትና ምፅዋት የሚሰጡትም ለዚሁ ነው ።

5. ኤክሌሽያ ድርጅታዊ መዋቅር አላት ። ሆኖም የየአብያተ ክርስቲያኑ ድርጅታዊ መዋቅር የተለያየ ሊሆን ይችላል ። አንዳንዶች ለቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር ሥጋዊ አሠራር ስለሆነ አያስፈልጋትም ይላሉ ። ምክንያቱም ድርጅታዊ መዋቅር ለመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እንቅፋት ሊሆን ይችላል ብለው ስለሚሰጉ ነው ። ሆኖም ድርጅታዊ አሠራር መኖሩ የመንፈስ ቅዱስን ድርሻ ለመተካት አይደለም ። ሥርዓት ባለው ሁኔታ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ነው። አለበለዚያ ፕሮግራም ማካሄድ ፤ ወንጌል ማዳረስ ፣ ሌሎችንም ተግባሮች በአግባቡ ማከናወን አስቸጋሪ ነው ። በምድር እስካለን ድረስ ሥርዓት ያስፈልገናል ።

ሐ. ኤክሌሽያ ከምድራዊ ድርጅት ልዩ የሚያደርጋት ፡—

1. ዓላማዋ መንፈሳዊ ነው ። በምድራዊ መለኪያ የሚሠፈርና የሚለካ አይደለም ።

2. የበላይ መሪዋ ክርስቶስ ነው ። ማቴ 23፡ 8 - 12 ቆላ 1፡18 ለምድራዊ ድርጅት ግን የበላይ መሪ ሰዎች ናቸው ። ይህ ሲባል



በቤተክርስቲያን መሪዎች የሏትም ማለት አይደለም ።የቤተክርስቲያን መሪዎች እንደዚህ አለም መሪዎች አሠሪዎች ሳይሆኑ የማህበር ምእመናን አገልጋዮች ናቸው ።ማቴ.20 ፡25 - 27

3. አገልጋዮች አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙት መንፈስ ቅዱስ በሚሰጣቸው ኃይል እንጂ በራሳቸው ጥበብና ችሎታ አይደለም ። 1 ቆሮ 12 ፡ 4 - 12

4. በመንፈስ ቅዱስ አንድነት ትመራለች ። ስለዚህ ሕይወት ያላት ድርጅት ነች ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ቦታ ካጣ ቤተክርስቲያን ሕያው ድርጅት መሆኗ ይቀርና ድርጅት ብቻ ሆና ትቀራለች ። ስምና መዋቅር ሊኖራት ይችላል ። ሆኖም ሕያው ድርጅት መሆኗ ይቀራል ።

## ክፍል 2. የኤክሌሽያ አስተዳደር ዓይነቶች ፣

በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የነበረች ቤተክርስቲያን የተለያዩ አስተዳደርና አገዛዝ አልነበራትም ። ብዙውን ጊዜ ምዕመናን የሚሰበሰቡት ለአምልኮና ለትምህርት ነበር ። ( ሥራ.2፡42 ) ቤተክርስቲያንን ከበላይ ሆነው የሚመሩና የሚያስተዳድሩ ሐዋርያት ነበሩ ። የእግዚአብሔር ሥራ እየሰፋ ሲሔድ በየአገሩ አጥቢያዎች እየተቋቋሙ ሲሔዱ ሐዋርያት ሽማግሌዎችን ይሾሙላቸው ነበር ። ( ሥራ 14 ፡ 23 )

ይሁን እንጂ አንዳንድ ችግሮች ሲነሱ ሐዋርያት ብቻቸውን ሳይሆን ሽማግሌዎችና ከቤተክርስቲያን ጋር በመሆን አብረው በመወያየት ችግሮችን ይፈቱ ነበር ። ( ሥራ 15 ፡ 22 )

ዘመን እየጨመረ ሲሔድ የቀደሙት ሐዋርያትና ከእነርሱም የተረከቡ አገልጋዮች አገልግሎታቸውን ጨርሰው ሔዱ ።

አብያተ ክርስቲያናትም የመጀመሪያዋን ቤተክርስቲያን መልክ እንዳለ መከተል አልቻሉም ። ። ስለዚህም በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ የአስተዳደር ዓይነቶች ተፈጠሩ ።

### ሀ. ኤጲስ ቆጶሳዊ አገዛዝ ፣

ይህን አገዛዝ የምትከተለል ቤተክርስቲያን ከበላይ ሆነው ሲያስተዳድሩና ሲመሩ የነበሩ ሐዋርያት ወይም በሐዋርያት የተወከሉ ስለ ሆኑ ሽማግሌዎች የሚሾሙትና ለሽማግሌዎችም መመሪያን የሚሰጡ ሐዋርያት ነበሩ ። ሥራ 14፡23 ፡ 20፡28

፥ ቲቶ 1፥5) በማለት በአሁኑ ጊዜ ቤተክርስቲያንን ከበላይ ሆነው መምራት ያለባቸው በሐዋርያት ሥልጣን ላይ ያሉ ጳጳሳት ናቸው ብለው ያምናሉ ። ስለዚህ ይህ አስተዳደር የተፈጠረው በቤተክርስቲያን ውስጥ ሐዋርያዊ ሥልጣንን ለመተካት ታስቦ ነው ። አመራሩ የሚሰጠው በሰው ሹመት ነው ። ነገር ግን ሐዋርያትን ቢሆን ወይም ሌሎች አገልጋዮችን የሚሾማቸው ጌታ ነው እንጂ ሰው አለ መሆኑን እንረዳለን ። ( ኤፌ. 4፥11-13 )

በዚህ በኤጲስ ቆጳሳዊ አገዛዝ የምትመራ ቤተክርስቲያን ሶስት የአገልግሎት ደረጃ አላት ።

1ኛ- ጳጳስ ፥
2ኛ. ካህን ( ቄስ )
3ኛ. ዲያቆን በማለት ደረጃው ይለያል ።

ዲያቆን የካህኑ ፥ ካህኑን የጳጳሱን ሥፍራ ተክቶ ሊቆም አይችልም ። ዲያቆኑ በሌለበት ቄሱ ማለት ካህኑ የዲያቆኑን ቦታ ተክቶ አገልግሎት መስጠት ይቻላል ።

ለ. ፕሪስፒተሮስ አገዛዝ ፥

ፕሪስፒተሮስ በግሪክ ቋንቋ ሽማግሌ ማለት ነው ። በፕሪስፒተሮስ አገዛዝ የምትመራ ቤተክርስቲያን በሽማግሌዎች የምትዳደር መሆኗ ነው ። ቤተክርስቲያንን ከበላይ ሆነው የሚመሩ ፥ የሚያስተዳድሩና ቤተክርስቲያንን በመወከል በከፍተኛ ስብሰባዎች ላይ የሚገኙ ሽማግሌዎች ናቸው ።

የፕሪስፒተሮስያን አገዛዝ የሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናት የሚያቀርቡት ሃሣብ ፥ በኢየሩሳሌም ስብሰባ ጊዜ የተሰበሰቡና ውሣኔ የሰጡት ሽማግሌዎች ከሐዋርያት ጋር በመሆን ነው እንጂ ከምዕመናን ጋር በመሆን አይደለም ይላሉ ። ( ሥራ 15፥6) እንደገናም ጢሞቲዎስን የሾሙት እጅ በመጫን ሽማግሌዎች ናቸው ብለው ያስባሉ ። ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን እንዲያሠማሩ ኃላፊነት የሰጣቸው ለሽማግሌዎች ነበር ይላሉ ። ( ሥራ 20 ፥ 28 ) ስለዚህ የመጀመሪያ ቤተክርስቲያን የምትተዳደረው በፕሪስፒተሮሳዊ አስተዳደር ስለሆነ አሁንም ቤተክርስቲያን ልትከተል የሚገባት የመጀመሪያይቷን ቤተ ክርስቲያን አመራር መሆን አለበት ብለው ያምናሉ ።

ለነገሩ በኢየሩሳሌም ስብሰባ ጊዜ ቤተክርስቲያን ከሐዋርያትና ከሽማግሌዎች ጋር እንደነበረች በግልፅ እንረዳለን ። ( ሥራ 15 ፥ 4፤ 12.22 )



ጢሞቴዎስም ቢሆን በሐዋርያው ጳውሎስ የተሾመ መሆኑ የታወቀ ነው ። ሆኖም ሽማግሌዎች እጅ ጭነው እንደጸለዩለት እንጂ እንደ ሾሙት አናይም ። (1ኛ ጢሞ. 4፥14 )

በእርግጥ በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በሽማግሌዎች የሚተዳደሩ መሆናቸው ግልጽ ነው ። ( ሥራ 14፥23.20 ፥ 17. 28፥ ፊልጵ. 1፥1) ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ ካለው ፕሪስፒተሮሳዊ አገዛዝ በመጠኑም ቢሆን ልዩነት አለ ።

በፕሪስፒተሮሳዊ አገዛዝ የምትመራ ቤተክርስቲያን አራት መደበኛ የስብሰባ ደረጃዎች አሏት ።

1. የአባላት ስብሰባ ፥
2. የሽማግሌዎች ስብሰባ ፥
3. የክልል ( የሲኖዶስ ) ስብሰባ ፥
4. አጠቃላይ ጉባኤ የሚባሉ ናቸው ።

ፖሊሲ ነክ በሆነና ከፍተኛ ውሣኔ አሰጣጥን በሚመለከት የሚመለከተው አጠቃላይ ጉባኤው ነው ።

ሐ. <u>የጉባኤ አስተዳደር</u> ፥

ይህን በጉባኤ አስተዳደር የሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናት ፍላጐታቸውን ድምፅ በመስጠት ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሥርዓት ይመራሉ ። የበላይ ወሣኝ አካል አይኖራቸውም ።

ከመሰል አብያተክርስቲያናት ጋር የክልል ስብሰባና አጠቃላይ ስብሰባ ያደርጋሉ ። ሆኖም ለመንፈሳዊ መነቃቃትና ለወንጌል አገልግሎት በሆነ ጉዳይ እንጂ አስተዳደር ነክ በሆነ ነገር አይሰበሰቡም ።
ይህን አገዛዝ የሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናት ስለ ጉባኤ አስተዳደር የሚያቀርቡት ሐሳብ አላቸው ፥—

1. የመጀመሪያዎቹ ምዕመናን አገልጋዮቻቸውን ራሳቸው መርጠዋል ። ( ሥራ 6፥1-6 ) የሚል ነው ።

2. ከመሪዎች ጋር በመሆን ምዕመናን በአንዳንድ ነገሮች ላይ ይወያዩና ይወስኑ ነበር ። ( ሥራ 15፥22 )

3. ከሌላ ቤተክርስቲያን ተወክለው የሚመጡትን ይቀበላሉ ፥ ይልካሉም ። ( ሥራ 15፥4. 18፥27. 13፥13 )

4. ያጠፉትን የሚቀጡ ምዕመናን ናቸው ። ( ማቴ.18፥17፥ 1ኛ ቆሮ. 5፥13፥ 2ኛ ቆሮ. 2፥6፥ 2ኛ ፥ ተሰ. 3፥6.14)

ስለዚህ በቤተክርስቲያን ውስጥ በበላይነት ሰዎችን ማስቀመጥ የክርስቶስን ቦታ መስጠት ይሆናል ብለው ያስባሉ ።

በእርግጥ ይህ የአገዛዝ ሁኔታ በጥንቷ ቤተክርስቲያን የሚሠራበት ይመስላል ። ይሁን እንጂ ምዕመናኑ በተለያዩ ስብሰባዎች ቢገኙም ሐሳብ መስጠት አለመስጠታቸውን በግልጽ አናይም ።ደግሞም ቤተክርስቲያንን የሚመሩ ሐዋርያት እንደነበሩና ከዚያም ሽማግሌዎች መሆናቸውን መረዳት አያዳግትም ።

መ. <u>የብዙኃን ሽማግሌዎች አስተዳደር ፥</u>

በዚህ መስተዳደር የሚመሩ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎቻቸው ሽማግሌዎች   መጋቢዎች ፥ እረኞችና ጳጳሳት ተብለው ይጠራሉ ። እነዚህ እንደ ፕሪስፒተሮስ ለአጥቢያዎቻቸው ተጠሪና ተወካይ ናቸው ። አጥቢያ ቤተክርስቲያንን በኃላፊነት ይመራሉ ፥ ያስተዳድራሉ ያስተዳድራሉ ። ከፕሪስፒተሮስ የሚለዩበት ነገር ቢኖር አንድ ነገር ነው ። ይኸውም ፕሪስፒተሮስ ሽማግሌዎች ሁሉም በእኩልነት ይሰየማሉ ። በብዙኃን የሽማግሌዎች አስተዳደር ግን አንዱ በእግዚአብሔር እንደተቀባ በመቀበል ዋና ተናጋሪና የሽማግሌዎች ተወካይ ይሆናል ።

ሠ. <u>ግላዊ አስተዳደር ፥</u>

ይህን መስተዳደር ተቀብለው ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ለየግላቸው በመቆም ለማንም ድርጅት ተጠሪ አይሆኑም። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጋቢው የበላይ መሪ ነው ። አልፎ አልፎ በአንዳንዶች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ይኖራሉ ። ቢሆንም ፓስተሩ ማለትም መጋቢው ድምጽ ፖሊሲ ነክ በሆኑ   ነገሮች ላይ ወሳኝነት ይኖረዋል ።

ለቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ዕድገትና መንቃቃት የትኛው የአስተዳደር ዓይነት ይበልጥ አመቺ ይሆን ? የሚል ጥያቄ አለ ።

እምስቱም የመስተዳደር ዓይነቶች ከመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ቅጂ እንደሆነ ይገምታሉ ።

ስለዚህ የትኛው የአስተዳደር ዓይነት ይሻላል ቢባል መንፈስ ቅዱስ ያልገባበትና የማይቆጣጠረው ከሆነ ሁሉም ዓይነት አይጠቅምም ። ሰው ሠራሽ ብቻ ሆኖ ይቀራል ። ቤተክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ አንድነት የምትመራ ከሆነች የትኛውም ዓይነት አስተዳደር እንቅፋት ሊሆን አይችልም ።



# ምዕራፍ ስድስት

# ለኤክሌሽያ የተሰጠ አገልጋዮች

በኤፍ. 4፥7 - 13 ላይ እንደምናየው ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ከሰጣቸው ታላላቅ ስጦታዎች ውስጥ አንዱ አገልጋዮችን ነው።በዚህ ክፍል ውስጥ እንደምናየው በመጀመሪያ ስጦታን ለሰዎች ሰጠ ። እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያ እንዲሆኑ የሐዋርያትን ስጦታ ሰጠ ። ሌሎቹም ነቢያት ፥ ሌሎችም ወንጌል ሰባኪዎች ፥ ሌሎችም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ ። ይህንንም ስጦታ የሰጣቸው ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለእካሉ ማለትም ለቤተክርስቲያን ጥቅም ነው ።

ይህንንም ያደረገበት ምክንያት በተለያዩ ርዕሶች እንደተገለጸው አንደኛ ቅዱሳንን ሁሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለማዘጋጀት ፥ ሁለተኛ ማኅበረ ምዕመናን በክርስቶስ እምነት ወደሚገኘው አንድነት እንዲደርሱ ለመርዳት ፥ ሶስተኛ ቤተክርስቲያን ወደ ክርስቶስ ሙላት ለመድረስ እንድትችል ለማገዝ እንደሆነ ቀደም ሲል ዓይተናል ።

አንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን እነዚህን አገልጋዮች ሁሉ ከአገልግሎታቸው ባህርይ የተነሳ ላይኖራት ይችላል ። ሆኖም የእነዚህን አገልጋዮች የፀጋ አገልግሎት በየወቅቱም ቢሆን መካፈል አለባት ። አለበለዚያ ወደ ታቀደላት ግብ መድረስ አትችልም ። ስለዚህ የእያንዳንዳቸውን የአገልግሎት ባህርይ በተናጠል ለማየት እንሞክራለን ።

ሀ/ <u>ሐዋርያት ፥</u>

ሐዋርያት ማለት በግሪክ ቋንቋ “ አፖስቶሌስ ” ይባላል ። ትርጉሙም “ የተላከ ” ማለት ነው ። በአዲስ ኪዳን በዕብ. 3፥1 ላይ እንደምናነበረው ክርስቶስ “ አፖስቶሌስ ” ተብሏል ። እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደዚህ ዓለም ተልኳልና ። ( ዮሐ.17፥18.20፥21 ) ስለ ሐዋርያት ስናይ በሁለት ክፍለን ማየት ይኖርብናል ።

1. <u>የበጉ ሐዋርያት ራዕ. 21፥14፥</u>

   1.1 የበጉ ሐዋርያት የምንላቸው በስም የተጠቀሱ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ናቸው ። ( ሉቃ.6፥12-16 ) እነዚህን

አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ከጌታ ጋር አብረው የበሉና የጠጡ ከዮሐንስ ጥምቀት ጀምሮ እስከ ዕርገቱ ድረስ አብረውት የነበሩ ናቸው ።

ስለ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም ሲነሳ የአስቆሮቱ ይሁዳን ሹመት የወሰደ ማን እንደሆነ ብዙ ክር ክር ተደርጓል።አንዳንዶቹ ጴጥሮስ ባወጣው ክራይቴሪያ ዕጣ የወጣለት ማትያስ ነው ሲሉ(ሥራ 1፡15-2)6ሌሎች ደግሞ ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ የተመረጠው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው ይላሉ ። ( ሥራ 22፥ 14፥ ገላ.1፡15) ስለዚህ ነገር እርግጡን ለማወቅ የእግዚአብሔር ክብር የሞላባት አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ቅጥር ውስጥ የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስሞች የተጻፉ ስለሆነ እዚያ ቀድሞ የደረሰ ያንብብና ይወቅ ፥ ( ራዕ. 21፡14 ) ።

## 1.2 አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ልዩ የሚያደርጋቸው ምንድነው ?

እነዚህ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ከሌሎች ሐዋርያት ልዩ የሚያደርጋቸው አገልግሎታቸው ሳይሆን የተሰጣቸው ሥልጣንና ክብር ነው ። ማቴ. 19፡28 ፥ ሉቃ. 22፡28፥ ራዕ. 21፥ 14 ) ስለ አገልግሎታቸው ከሆነ ጌታም እንኳን “ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል ”(ዮሐ.14፡12) ብሏል ። ሆኖም ክርስቶስ የሚያደርገውን ሥራ ቢሠራም ማንም የእርሱን ክብርና ሥልጣን ሊኖረው አይችልም ።

## 1.3 የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጥሪ እንዴት ነበር ?

ሌላው ልዩ ነገር ጥሪያቸው ነው ። እነዚህን ጌታ በዚህ ዓለም በነበረ ጊዜ በቀጥታ የጠራቸው ናቸው። ሲመርጣቸው ምን መለኪያ ወይም መመዘኛ እንደተጠቀመ አናውቅም ። ሁሉም ግን እንደ እኛ ደካሞች እንደ ነበሩ እናያለን ። ሕይወታቸው የተለወጠው እንኳን መንፈስ ቅዱስን ከተሞሉ በኋላ ነበር ። አስቀድሞ ግን እርስ በእርሳቸው ዘወትር የሚከራከሩ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ተባብለው ለሥልጣን የሚጣሉ ፥ ( ሉቃ.9፡46 ፥ ሉቃ. 22፡24፥ ) ፈሪዎች ፥ ( ማር.14፡50 ፥ ዮሐ. 20፡19 ) እምነት የሌላቸው ፥ ( ማር.8፡17-21. 16፡14 ) ነገር የማይገባቸው ፥ ማቴ.16፡5-12 ) እንደ ነበሩ እንረዳለን ። አስቀድሞ ግን ሌሊቱን ሁሉ ሲፀልይ እንደነበር ተጽፏል። ( ሉቃ.6፡13-14 )



ይሁን እንጂ ጌታ ሲመርጣቸው በውስጣቸው ያየው ነገር ይኖራል ። ስለዚህ ቢክዱትም ፥ ጥለውት ቢሸሹም ፥ ሲጠራጠሩ ትም እርሱ ግን ሰበሰባቸው ። ወንጌልን ለዓለም ሁሉ እንዲያደርሱ አደራ ሰጣቸው ( ማር16፡8 )። መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ደፋሮች ፥ ለሰይፍ የማይበገሩ ፥ የእምነት ሰዎች ሆኑ ።

# 2. ለሎች ሐዋርያት ፥

## 2.1 አዲስ ኪዳናችንን ስናነብ ከአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ሌሎችም እንዳሉ እናያለን ።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች እነዚህን ከአሥራ ሁለቱ የበጐ ሐዋርያት ለመለየት “የቤ ክርስቲያን ሐዋርያት ” ብለው ይጠቅሷቸዋል ። በ2 ቆሮ. 9፡23 ላይ “ ስለ ወንድሞች የሚጠይቅ ቢኖር የአብያተክርስቲያናት መልዕክተኞች ናቸው” የሚለውን ቃል ወስደው “ መልዕክተኛ” ማለት ሐዋርያ ማለት ስለሆነ እነዚህ“ የአብያተክርስቲያናት ” መልዕክተኞች መባላቸው “ የአብያተክርስቲያናት ሐዋርያት ” ለማለት ነው ብለው ያስባሉ ።

በእርግጥ በዚህ ሥፍራ የተጠቀሱ ወንድሞች በአብያተክርስቲያናት የተመረጡና የተላኩ ናቸው (2ቆሮ 8፡18 ) ። የተላኩት ግን ለወንጌል አገልግሎት ሳይሆን ለችግረኛ ክርስቲያኖች ከየአብያተክርስቲያናት መዋጮ እንዲሰበስቡ ከአብያተክርስቲያናት ተወክለው የተላኩ ናቸው ። ደግሞም ቤተክርስቲያን ሐዋርያ አድርጋ ማንንም መሾም አትችልም ። በኤፌ. 4፡11 ላይ እንዳየነው ለቤተክርስቲያን የተሰጡት ሰዎች ናቸው እንጂ ስጦታው አይደለም ። ስለዚህ እነዚህን ሐዋርያት ከአሥራ ሁለቱ የበጐ ሐዋርያት ለይቶ ለማየት “ ሌሎች ሐዋርያት ” ብንል የተሻለ ነው ።

## 2.2 በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ከአሥራ ሁለቱ የበጐ ሐዋርያት ሌላ በስም ተጠቅሰው ያሉ ሌሎች ሐዋርያት

እንዳሉ እናያለን ።

<u>ለምሳሌ</u> ፦በርናባስ ሐዋርያ ተብሏል ፤ ( ሥራ 14፡4.14 )

የጌታ ወንድም ያዕቆብ ፤ ( ገላ.1፡19)

ሲላስና ጢሞቴዎስ ፤ (1ተሰ.1፡1.2 ፡6 )

በሌላ በኩል ብናይ ራዕ. 2፡2 ላይ በኤፌሶን ቤተክርስቲያን
ሐዋርያት ነን ብለው የተነሱ ፤ በኋላ መጋቢው መርምሮ ሐዋ
ርያ እንዳልሆኑ እንደደረሰባቸው እናያለን ። በ2 ቆሮ.11፡13
ላይ እንደምናነበው ደግሞ በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያንም ሐዋ
ርያትን ለመምሰል እራሳቸውን ለውጠው የተቀመጡ እንደ
ነበሩ እናገኛለን ። እንግዲህ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ለሌሎች
አገልጋዮች ሐዋርያት መባል ሳይችሉ ሐሰተኞች ለመሆናቸው
መመርመር አያስፈልግም ። ገና ሐዋርያ ነን ሲሉ “ ከአሥራ
ሁለቱ ሌላ ሐዋርያ ሊባል አይችልም ” ተብለው በተባረሩ
ነበር ።

## 2.3 <u>ለሐዋርያነት የሚያበቃ ምንድነው ?</u>

ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆኑ የተለያዩ አቋሞች አሉ ።

2.3.1. አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ጌታን
ማየት ነው ብለው እነዚህን ጥቅሶች ይጠቅሳሉ ( ሥራ
1፡21-22 ፤ 1ቆሮ.9፡1) ። እነዚህን ጥቅሶች ወስደን በጥ
ንቃቄ ብናያቸው ለሐዋርያት የሚያበቁ መስፈርቶች
አለመሆናቸውን እናያለን ። በሥራ 1፡21-22 ላይ የም
ንረዳው ጴጥሮስ በይሁዳ ቦታ ሐዋርያ ለመተካት ሰዎ
ችን በዕጣ ለማቅረብ የተጠቀመበትን ዘዴ እንደታ
ሪክ ተመዝግቦ እናገኛለን እንጂ እንደመመሪያ ሆኖ
የቀረበ አይደለም ። በ1ቆሮ 9፡1-4 ላይ የምናየው ደግሞ
ሐዋርያው ጳውሎስ እኔ ሐዋርያስ አይደለሁም ? ጌታ
ችንን ኢየሱስ ክርስቶስ አላየሁትም ? ሲል ከበስተ
ኋላ ስለሚሉት ነገር መልስ ለመመለስ እንጂ መስፈ
ርት አድርጐ ማቅረቡ አይደለም ።

ጌታን ማየት እንደብቃት አድርገን ካየን ከአሥራ
ሁለቱ ሌሎች ሐዋርያት ይሾማሉ ወይም ይኖራሉ የሚ
ለውን ሐሳብ መተው አለብን። እነጢሞቴዎስና እነሲላ
ስና በርናባስ መቼ ጌታን አዩ ? ሆኖም እነዚህ ወንድ
ሞች ሐዋርያት ተብለው መጠራታቸውን በግልጽ ዓይ



ተናል ። አለበለዚያማ በዘመናችን ሐዋርያት ሊኖሩ
አይችሉም ማለት ነው !

2.3.2 ሌሎች ደግሞ ለሐዋርያነት የሚያበቃ ድንቅ ተአም
ራት ማድረግ ነው ብለው 2ቆሮ.12 ፡12 ላይ ያለውን
ቃል ይጠቅሳሉ ። በዚህም ሥፍራ ሐዋርያው ለሚሞ
ግቱት መልስ ለመስጠት ነው ። “ በእርግጥ የሐዋር
ያነት ምልክት በመካከላችሁ ተደረገ ” ይላል ።
ሐዋርያው ጳውሎስን የሚሉት ብዙ ነገሮች አሉ፣
ያንን የሚሉትን ሁሉ አልጠቀሰልንም ። ሆኖም
ለሚሉት ነገር የሚሰጠውን መልስ ብቻ ነው የምና
ነበው ( 1 ቆሮ.9፡1-8. 2ቆሮ.12፡11-13) ። ስለራሱ
የሚሰጣቸውን መልሶችና ለአብያተክርስቲያናት መ
መሪያ እንዲሆኑ የደነገጋቸውን ትምህርቶች ለይቶ
ማወቅ አስፈላጊ ነው ።

እንግዲህ ለሐዋርያነት የሚያበቃው ድንቅ ተአ
ምራት ማድረግ ነው ብለን ካልን ሐዋርያት ተብለው
ከተጠቀሱት ስንቶቹ ድንቅ ተአምራት አድርገው ይ
ሆን ? በጥቅሉ በሥራ 5፡12 ላይ በሐዋርያትም
እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝቡ መካከል ይደረግ
ነበር ” የሚል አለ ። ሆኖም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ
ድንቅ ድንቅ ተአምራትን ለማድረግ ተጠቅሰው የም
ናገኛቸው ሐዋርያው ጳውሎስና ጴጥሮስ ብቻ ናቸው።
ይህ ሲባል በሌሎቹ ድንቅና ተአምራት አልተደረገም
ብለን ለመዝጋት አንደፍርም ። ይሁን እንጂ ለሐዋ
ርያነት የሚያበቃ ድንቅና ተአምራት ነው የሚለው
አጥጋቢ ነጥብ አይደለም። እንዲያውም በ1ቆሮ.12 ፡27
-28 ላይ እንደምናየው ሐዋርያትንና ተአምራት ማድ
ረግ ለያይቶነው ያቀረበልን ። ስለዚህ ተአምራትን
ማድረግ ሐዋርያት ባልሆኑትም ስለሚገለጽ ተአም
ራትን የሚያደርጉትን ሐዋርያት ብለን ላንጠራቸው
እንችላለን ።

## 3. <u>ሐዋርያትና አገልግሎታቸው ፤</u>

ሐዋርያትን ሐዋርያት የሚያሰኛቸው የሚኖራቸው አገልግሎትና
የሚኖራቸው ሥልጣን ነው ። በእርግጥ እነዚያን አሥራ ሁለቱን
የበጐ ሐዋርያት የምንላቸውን የእነርሱን ሥልጣን ማንም አይኖ

ረውም ። እነዚህንም ሌሎች ሐዋርያት የምንላቸውን እግዚአብሔር በውስጣቸው የሚያስቀምጠው ኃይል መጠንና አገልግሎታቸው ከፍ ያለ ነው ።

በአጠቃላይ የሐዋርያትን አገልግሎት ብናይ ሁሉን ዓይነት አገል ግሎት አጠቃልሎ የያዘ እንደሆነ እንረዳለን ። እነዚህም ፦

3.1. <u>የወንጌል ሰባኪነት ሥራ ፡</u>

የሐዋርያት ዋናውና ትልቁ አገልግሎት ወንጌልን ላልደረሰው ማዳ ረስ ነው ። ( 1ቆሮ 9፡16፥ 2ጢሞ.4.2) ሐዋርያ የሚለው ትርጉም እንዳየነው የተላከ ማለት ነው ። ይህም መላክ ወንጌልን ይዞ ለጠ ፋው ዓለም ማድረስ ነው ። ( ዮሐ.20፡21

3.2. <u>የነቢያት አገልግሎት አላቸው ፡</u>

ብዙዎች ሐዋርያት ትንቢት እንደተናገሩ እናያለን ፡

— ሐዋርያው ዮሐንስ የራዕይን የትንቢት መጽሐፍ የጻፈ ነው ፡
— ጳውሎስ ስለመጨረሻው ዘመን ስለሚሆኑ ነገሮች ጽፎ አል ፡
— ጴጥሮስ የትንቢት ቃል ጽፎአል ፡
በአጠቃላይ እንደምናየው በአዲስ ኪዳን የተጻፉ የትን ቢት ቃሎች በሐዋርያት የተነገሩ ናቸው ።

3.3 <u>ሐዋርያት አስተማሪዎችና የቤተክርስቲያን የበላይ አስተዳዳርዎ ትም ነበሩ ፡</u>

ሐዋርያት በየአብያተክርስቲያናቱ እየዞሩ ያስተምሩና ደቀመዝሙር ያደርጉ ነበር ። ስለዚህ በአጠቃላይ የአዲስ ኪዳን ትምህርት የተሰ ጠው በሐዋርያት ነው ። ከዚህም ጋር ቤተክርስቲያንን ከበላይ ሆ ነው ሲመሩና ሲያስተዳድሩ የነበሩ ሐዋርያት መሆናቸው ግልጽ ነው። በአሁኑስ ዘመን ሐዋርያት ይኖሩ ይሆን ? ቤተክርስቲያን በዚህ ዓለም እስካለች ይኖራሉ ። የቤተክርስቲያን ሥራ ያለቀ አይደ ለም ። ቤተክርስቲያን ራሷም ተሠርታ አላለቀችም ። እግዚአብ ሔር ለቤተክርስቲያን ያለውን ዓላማ አልጨረሰም ስለዚህ ሐዋር ያት የማይኖሩበት ምንም ምክንያት የለም ።

ሆኖም በዚህ ዘመን ያሉት አብያተክርስቲያናት ብዙው አሠራራቸው ዘመናዊ መልክ ያለው አሠራር ስለሆነ ቢኖሩም ለማወቅ ያስቸግራል ።



ለ· <u>ነቢያት ፡</u>

1. ትርጉም ፡

ነብይ በእብራይስጥ ቋንቋ “ ናቢ ” ይባላል ። ትርጉሙም አዋጅ ነጋሪ ወይም መልዕክት አስተላላፊ ማለት ነው ። ትንቢት የሚለው ቃል ደግሞ “ ናባ ” ሲሆን ትርጉሙም “መፍለቅለቅ” ማለት ነው። በግሪክ ቋንቋ ነቢይ ማለት ደግሞ “ ፕሮፌተስ ” ሲሆን ። ትርጉ ሙም “ በሌላው ቦታ ሆኖ መናገር ” ማለት ነው ። ስለዚህ በእብራ ይስጥም ይሁን በግሪክ ቋንቋ ትርጉሙ የተራራቀ አይደለም ።

2. ነቢያት በብሉይ ኪዳን ብዙ መጠሪያ ስሞች አሏቸው ፡

2.1. የእግዚአብሔር ሰው ፡ ( ዘዳ. 33 ፡ 1 )
ይህም ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ለማለት ነው ።

2.2. የእግዚአብሔር መልዕክተኛ ( ሐጌ 1 ፡ 13 )
ለሕዝቡ የሚያስተላልፈው መልዕክት የማን እንደሆነ ያስገነዝባል ።

2.3. ባለ ራዕይ ፡ 1ሣሙ. 9፡9 11፡18 ፡ 1 ዜና 21 ፡ 9 )
ከእግዚአብሔር የሆነውን ነገር የሚያይ ለማለት ነው።

2.4. የእግዚአብሔር ባሪያ ፡ ( ኢያ. 1፡1፥ ኢሳ. 20 ፡ 3)

ለእግዚአብሔር ፍጹም ታዛዥነቱንና አገልጋይነቱን ለመግለጽ ነው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት በአጠቃላይ አገልግሎታቸው ከእግዚአብሔር ሆነው ወደ ሕዝቡ የሚናገሩ ናቸው ።

3. የአዲስ ኪዳን ነቢያት ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ልዩ የሚያደርጋቸው ተጨማሪ የክህነት አገልግሎትም አላቸው ።ምክንያቱም ክርስቲያን ሁሉ የክህነት አገልግሎት ስላለው ነቢያትም ይህ አገልግሎት ይኖ ራቸዋል ። (1ጴጥ.2፡9 ፡ ራዕ. 5 ፡10 ) ካህን ማለት “ አገልጋይ ” ማለት ነው ። አገልግሎቱም በእግዚአብሔርና በሰው መሐከል ሆኖ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ማገናኘት ነው ። ስለዚህ በአዲስ ኪዳን ያሉ ቅዱሳን ሁሉ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር በክርስቶስ ስለሚያ ቀርቡ ይህ አገልግሎት አላቸው ። ( 2 ቆሮ.5፡18 ፡ ሮሜ 15 ፡ 15 )

4. የአዲስ ኪዳን ነቢያት በደረጃ ከሐዋርያት ቀጥሎ ይጠቀሳሉ ። ( 1 ቆሮ.12፡28 ፡ ኤፌ.፡3፡5. 4፡11 ፡ ራዕ. 18፡20 ) ነቢያት እንደ ሐዋር ያትና እንደ ወንጌላውያን እየተዟዟረ የሚያገለግሉ እንጂ በአንድ

አጥቢያ ቤተክርስቲያን እንደ እረኞች የሚቀመጡ አይደሉም ። ከሐዋርያትና ከወንጌላውያን ልዩ የሚያደርጋቸው ፣ ነቢያት አገልግሎታቸው ብዙውን ጊዜ ወንጌልን ላልደረሳቸው ማዳረስ ሳይሆን ከአጥቢያ አብያተክርስቲያናት ወደ አጥቢያ አብያተክርስቲያናት በመዟዟር ያመኑትን ማገልገል ፣ ማነቃቃት ነው ። ( ሥራ 11፥28.13፥1 21፥10 )

5. ነቢያት ዋና አገልግሎሎታቸው ትንቢት መናገር ነው ። ሆኖም ትንቢት የሚናገሩ ሁሉ ደግሞ ነቢያት ናቸው ማለት አይደለም ። ትንቢት መናገር የፀጋ ስጦታዎች ከምንለው ውስጥ አንዱ ነው።ስለዚህ ብዙዎች ትንቢት ሊናገሩ ይችላሉ ። (1 ቆሮ.12፥4-8 ፣ ሮሜ 12 ፥ 6-8፣ ሥራ 2፥17-18) ሆኖም ብዙዎች እንደእምነታቸው ልክ ትንቢት ቢናገሩም ( ሮሜ 12፥6 ) በነቢያት ያለው ትንቢት አገልግሎት ስፋት አለው ።

6. ነቢያትን በተጨማሪ ልዩ የሚያደርጋቸውን ያለምንም ዝግጅት ለረጅም ጊዜ መልዕክት ማቅረብ መቻላቸው ነው ። መልዕክታቸው ያልተወሳሰቡ በጣም ግልፅ የሆነ ነው ። እንደ ምንጭ ሲፍለቀለቁ አይጠገቡም ፣ አይሰለቹም ። የእግዚአብሔር ቃል ከአፋቸው እንደ ውኃ ይፈልቃል ። መልዕክት በሚያቀርቡበት ጊዜ የንግግር ችሎታቸው ከወትሮው የንግግር ችሎታቸው ከፍ ያለ ነው ።

6.1 ነቢያት በሚሰብኩበት ጊዜ ጉባኤው ሁሉ ይመራመራል እሳት እንደሚቀጣጠል ይቀጣጠላል ፣ ካፋቸው የሚፈሰው ቃል በልባቸው ከሚፈስው ከእግዚአብሔር ሐሳብ ነው ። ስለ ዚህ ጉባኤው ሁሉ ይታነጻል ።

6.2 በጉባኤ መሐል የተደበቁ እርም ቢኖር ይገለጣል ።
6.3 ማንም ሳይካነው ለንስሐ ይጮሃል ።
6.4 በተለያየ ጥያቄ ተሞልተው የመጡ መልስ ያገኛሉ ፣ እግዚአብሔርን ለማመስገን ይጮሃሉ ።

6.5 የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ የተሳናቸውና ግራ የተጋቡ መልስ ያገኛሉ ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለግላቸው ወደማወቅና ወደ መረዳት ደረጃ ይመጣሉ ።

— በአጠቃላይ ቤተክርስቲያን ትታነጻለች ፣ ታላቅ መነቃቃት ይሆናል !

— በቤተክርስቲያን ውስጥ የመታነጽና የመንጻት አገልግሎት በነቢያት ይካሄዳል ።



7. በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የነበሩ ነቢያት ከፍተኛ ችግር ገጥሟቸው ነበር ። ለምን ቢባል ፦

7.1 በመጀመሪያው ስደት ለመከራና ለሞት የተጋለጡ ሆኑ።

7.2 አንዳንድ ነቢያት አገልግሎታቸውን ለኑሮ ማትረፊያ አድረጉት ። ( ቲቶ 1፣ 12 )

7.3 አንዳንዶቹ ውሸተኞች ሆነው የስህተት ትምህርት ማስተማር ጀመሩ። (1 ዮሐ. 3 ፥ 19-27 ፣ 4 ፥ 1-3 ፣ 2ኛ ዮሐ.7.10 ፣ ቲቶ1 ፥10-11)

7.4. አብያተክርስቲያናት እየተደራጁ ሲመጡ የነቢያት የአገልግሎት በር እየጠበበ መጣ ።

7.5. የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ቀስ በቀስ እየተዘነጋ መጣ / ከታሪክ እንደምንረዳው።/ የነብያት አገልግሎት ድምቀትና ተቀባይነት የሚኖረው ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ባለበት ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው ።

በአሁኑ ዘመን ያሉ ነቢያት ካለፈው ትምህርት መውሰድ አለባቸው ነቢያት በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን፣ አሁንም ብዙ አጀብ አላቸው ። ተቀባይነታቸው በአማኞች ዘንድ ከፍ ያለ ነው ። በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ያሉት ነቢያት ለቤተ ክርስቲያን አይገዙም ነበር ። የቤተ ክርስቲያንን እረኞች ይንቁ ነበር ። ምዕመናንም ያጅቧቸው ነበርና ። ቤተ ክርስቲያናት በአስተዳደራቸው ጠንካራ እየሆኑ ሲመጡ ነቢያት ያገልግሎት በር እየጠበበባቸው መጣ ።

አብያተ ክርስቲያናት ወደፊት የሚገጥማቸው ትልቅ ችግር የሐሰተኞች ነቢያት መነሳት ነው።(ማቴ. 24፥41,23) እነዚህ ሐሰተኞች ነቢያት የሚነሱት ደግሞ ከቤተክርስቲያን ውስጥ ነው እንጂ ከውጭ አይደለም ። በቤተክርስቲያን ውስጥ ደግሞ የነቢያት አገልግሎት መኖር እጅግ ጠቃሚ ነው ። ስለዚህ በአሁኑ ዘመን ያሉት አብያተክርስቲያናት የነቢያትን አገልግሎት አውቀው ጠንካራ ትምህርት መውሰድ አለባቸው ። ትምህርት የማትወስድ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ መሰናክል ይጠብቃታል ። እውነትን ከሐሰተኞች መለየት አስቸጋሪ እንደሚሆን ጌታ አስጠንቅቋል ( ማቴ.24፥24 ) ከእነርሱም የተነሣ ከእርስ በርስ መሰነካከ ያይሆናል ። ማቴ.24፥10 ) እውነተኞቹንም ማውገዝ ይመጣ ይሆናል ። ሐሰተኞችን መለየት ካልተቻለ ተቀባይነት ያገኙ ይሆናል ። አሁንም በጥቂቱ

እንዳየነው ይህ ዓይነቱ ተፈሚጽል ። ለዚህ የሚጠቅመው የእግዚአብሔርን ቃል እንደክትባት አስቀድሞ መውሰድ ነው።

## ሐ. ወንጌላውያን ፡

1. ወንጌላዊ የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ "" ኢቫንጀልስተስ " ከሚል ቃል የተወሰደ ነው ። ትርጉሙም መልካሙን የምሥራች አብሣሪ ማለት ነው ። መልካሙ የምሥራች የሚሰበከው ደግሞ የምሥራች ቃል ላልደረሳቸው ነው።ይህ የምሥራች ቃል ክርስቶስ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ሲል መሞቱን ነው ። ክርስቶስ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ቢሞትም የሚድኑት ቃሉን ሰምተው የተቀበሉት ብቻ ናቸው ። ስለዚህ ይህን የምሥራች ቃል የሚያሰሙ " ኢቫንጀሊስትስ " ተባሉ ።

2. ወንጌላውያን እንደ ሐዋርያት እየተዘዋወሩ ወንጌል ላልደረሳቸው የሚያደርሱና የሚሰብኩ ናቸው እንጂ እረኞች በቤተ ክርስቲያን ተቀምጠው የዳኑትን የሚያሠማሩ አይደሉም ።ቢሆንም ስለወንጌላውያን ከአዲስ ኪዳን ሆነ ከመጽሀፍ እየጠቀሱ ብዙ መናገር ያስቸግራል ።

3. ወንጌላዊ የሚለው ስም ሁለት ቦታ ብቻ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን ። ( ሥራ 21:8፥ ኤፌ.4:11 ) ወንጌላዊ ተብሎ የተጠቀሰው አንድ ሰው ብቻ ነው ። እርሱም ፊልጶስ ነው ። ( ሥራ 21 ፡ 8 )

ለምን ብዙዎች ወንጌላውያን ተብለው አልተጠቀሱም ቢባል ፥ የወንጌል ስብከት ሥራ የሐዋርያት ዋና የአገልግሎት ክፍል ስለሆነ ( ጢሞ. 4:5 ፥1 ቆሮ 9 ፥16 ) ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ወንጌልን በሚያደርሱ ወንጌላውያን ከመባል ይልቅ ሐዋርያት መባል መርጠው ይሆናል ። ወንጌልን በትክክል እስከሰበኩ ድረስ ሐዋርያ ተብሎ ለመጠራት እንደ አሁኑ ዘመን እምብዛምም ጫና ያለበት አይመስልም ።

4 በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ አገሮች ወንጌላውያን የሚሏቸው ሙሉ ጊዜያቸውን የሰጡ አዳዲስ ጀማሪ ሰባኪዎችን ነው ። ለወንጌል ሥራ ብዙ ከሮጡና ልምዶችን ካገኙ በኋላ የቤተ ክርስቲያን እረኞች ይሆናሉ ።

በአንዳንድ አገሮች ደግሞ እረኞች ሆነው ከቆዩ በኋላ ወንጌላውያን ይሆናሉ ። ሆኖም ከአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ወን



ጌላውያን ሆነው ከቆዩ በኋላ እረኞች እንደሚሆኑ ወይም እረኞች ሆነው ከቆዩ በኋላ ወንጌላውያን መሆን እንደሚችሉ የምንረዳው ነገር የለም ።

5. አቀማመጣቸውን በኤፌ.4 ፡ 11 ላይ ብንመለከት " አንዳንዶቹ ሐዋርያት ሌሎችም ነቢያት " ብሎ ወንጌል ሰባኪዎችን በሶስተኛ ደረጃ ያስቀምጣቸዋል ። በ1 ቆሮ.12፡28 ላይ ስናይ ደግሞ " እግዚአብሔርን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን ሁለተኛም ነቢያትን ብሎ በሶስተኛ ደረጃ አስተማሪዎችን ..." አድርጓል ይላል ። ወንጌል ሰባኪዎችን አይጠቅስም ። ምናልባት "ሶስተኛ አስተማሪዎችን ፥ ቀጥሎ ተአምራት ማድረግን . . . " ብሎ በአራተኛ ደረጃ ያስቀመጣቸው ወንጌላውያንን ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በአዲስ ኪዳን እስከመጨረሻው በወንጌላዊነት የታወቀው የፊልጶስ አገልግሎት እንደምሳሌ አድርገን ወስደን ብናይ የፊልጶስ አገልግሎት በታላቅ ተአምራት የተሞላ እንደሆነ እናያለን ። ( ሥራ 8 ፡ 6, 13 ) እርሱ የተለመደውን ተአምራት በሐዋርያት እንኳን አልታየም ። ( ሥራ 8 ፡ 39 - 40 )

ያም ሆነ ይህ አስፈላጊው የደረጃ አቀማመጥ አይደለም ። ዋናውቁም ነገር ሁሉም በተጠሩበትና ባለበት ቦታ እጅግ አስፈላጊ መሆናቸውን መረዳትና አገልግሎታቸውን በታማኝነትና በትጋት መወጣት ነው ። (ሮሜ 12 ፡58) ወንጌላዊ ካልሰበኩ ፥ እረኛ የሚጠብቀው የለውም ። ወንጌላዊ ብቻ ቢሰብክ እረኛ ከሌለ መንጋው ይበተናል ። የተዘራው የማይሰበሰብ ከሆነ ትርፉ ድካም ብቻ ነው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ እኔ ተከልኩ ፥ አጵሎስ አጠጣ ይላል ። (1 ቆሮ. 3 ፡6) ደግሞም እንደብልሃተኛ የአናጢ አለቃ መሰረትን መሰረትሁ ፥ ሌላው በላይ ይገነባል ይላል ። (1 ቆሮ. 3 ፡10) እራሱን እንደወንጌል አገልጋይ በመቁጠር ። ስለዚህ በወንጌል ስብከት መስክ በይበልጥ ወንጌል ሰባኪው አስፈላጊ ነው ። ለእርሱ ተሰጥቶታልና !

የዳኑትን ለማሳደግና ለማሠማራት ደግሞ እረኛው በይበልጥ አስፈላጊ ነው ። ለዚህ ተጠርቷልና ። ይህን መገንዘብ እጅግ ታላቅ ነገር ነው ። ይህ ሲሆን ቤተክርስቲያን ወደሚጠበቅባትና ወደታቀደላት ግብ ለመድረስ ትችላለች ። እግዚአብሔር እነዚህን አገልጋዮች ለቤተክርስቲያን የሚሰጠው ሁሉም አንድ ዓይነት ሥራ እንዲሠሩ አለመሆኑን መገንዘብ ይጠቅማል ። (ሮሜ 12 ፡ 4—5)

## መ. እረኞች ፥ አስተማሪዎችና ሽማግሌዎች ፤

በአሁኑ ጊዜ እረኞች ፥ አስተማሪዎች ፤ ሽማግሌዎች የሚባሉትን ከመጀመሪያ ክፍለ ዘመን ካሉት ጋር አገናዝቦና ተንትኖ ለማስቀመጥ በጣም አስቸጋሪ ነው።ስለዚህ እረኞችን አስተማሪዎችንና ሽማግሌዎችን በሚመለከት ሶስት የተለያዩ አቋሞች አሉ ።

ሽማግሌዎችና እረኞች የስም ልዩነት እንጂ አገልግሎቱ አንድ ነው ፥ ማለትም ለአንድ አገልጋይ የተሰጠ ስም ነው ። አስተማሪዎች ግን ልዩ ናቸው የሚል ነው ። (ቲቶ 1 ፥5,7 ፥ ሥራ 20 ፥17,28 ፥ 1 ጢሞ.3፥1 ) እነዚህን ሁለቱን በመጀመሪያ ለይተን በግሪክ ቋንቋ ምን ተብለው እንደሚጠሩ ከነትርጉማቸው ብናይ ጥሩ ግንዛቤ ይሰጠናል ።

ሽማግሌ የሚለው ቃል "ፕርስቡተሮስ" ሲሆን ትርጉሙም ሽማግሌ ማለት ነው ። ይህ ቃል በቤተክርስቲያን ውስጥ ላለው የአገልግሎት ሹመት የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን በዕድሜ ላረጁም የሚሰጥ ስም ነው ።

እረኛ የሚለው ቃል ደግሞ "ፓይመን" ሲሆን ትርጉሙም እረኛ ወይም ጠባቂ ማለት ነው ። (በቲቶ 1 ፥ 5 ፥ በሥራ 20 ፥ 17 ላይ ሽማግሌዎች የሚላቸውን መልሶ "ኤጲስቆጶስ" ይላቸዋል ። (ሥራ 20 ፥ 28 ፥ ቲቶ 1 ፥ 7) በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ጳጳስ የሚለው ቃልና ኤጲስ ቆጶስ የሚለው" ኤጲስኮፕ" ከሚል ከአንድ ቃል የወጣ ነው። ትርጉሙም የበላይ ተመልካች ወይም የበላይ ጠባቂ ማለት ነው ። እነዚህኑ ሽማግሌዎች ወይም ኤጲስቆጶስ ያላቸውን ተግባራቸውን ወይም ኃላፊነታቸውን ሲያመለክት"የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ..."ይላል ስለዚህ ሽማግሌዎች ሲል ሹመታቸውን ለማመልከት ሲሆን እረኞች ወይም ኤጴስቆጶስ ሲል ደግሞ አገልግሎታቸውን ለማመልከት ይሆናል ።

ሁለተኛው አቋም እረኞችና አስተማሪዎች ለአንድ አገልጋይ የተሰጡ ስሞች ናቸው ። ሽማግሌዎችን ልዩ ናቸው የሚል ነው ። ምክንያቱም ሐዋርያው ጳውሎስ እረኞችና አስተማሪዎች የሚለውን አንዱን የአገልግሎት ክፍል ለማመልከት እንደሆነ የተጠቀመው አንድ የተወሰነ መስተአምር ነው ። ሁለት የአገልግሎት ክፍል የሚመለከት ቢሆን ኖሮ ሁለት መስተአምሮችን መጠቀም ነበረበት ። በተጨማሪም የእረኞቹ ሥራ ሕዝቡን የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ ስለሆነ በ1 ጢሞ 3 ፥2 ላይ ደግሞ ለኤጲስ ቆጶስነት የሚያበቃ ማስተማር መቻል እንደሆነ ተጠቅሷል ።

ስለዚህ እረኛና አስተማሪ ለአንድ አገልጋይ የተሰጡ ስሞች እንደሆኑ እናያለን ። እረኞችና አስተማሪዎች የሚለው አባባል በ1 ጴጥ.2 ፥25 ላይ "ወደነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል" የሚል አባባል ክርስቶስን ሲያመለክት ነው እንጂ እረኛ ሌላ ጠባቂ ደግሞ ሌላ እንደሆነ ለማ



መልከት አይደለም ። በተመሳሳይ ሁኔታ "እረኞችና አስተማሪዎች" ሲል አንዱን የቤተክርስቲያን መጋቢ ለማመልከት እንጂ እረኞችና አስተማሪዎች ልዩ እንደሆኑ ለማመልከት አይደለም በማለት ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች ይስማማሉ ።

ሶስተኛው አቋም ደግሞ ሽማግሌዎችን በሁለት በመመደብ ነው ።

1ኛ. የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ፥

2ኛ. የሚያስተምሩ ሽማግሌዎች በማለት በሁለት ይመድቢቸውና ማስተማር የሚችሉ እረኞች ናቸው ይላሉ ፥ በ1 ጢሞ. 5 ፥17 ላይ ስንመለከት "መልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት እጥፍ ክብር ይገባቸዋል" ሲል የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ፥ ነገር ግን የማይሰብኩና የማያስተምሩ እንዳሉ ይመስላል ። ስለዚህ የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች ሁሉ አስተማሪዎች አይደሉም ማለት ነው ይላሉ ። ይሁን እንጂ እነዚህን መስበክና ማስተማር የሚችሉም ሽማግሌዎች ተብለዋል ።

### መ.1 የሽማግሌዎች አመጣጥ ፤

የሽማግሌዎች አመጣጥ በእሥራኤላውያን በብሉይ ኪዳን ጊዜ ነው ። (ዘፀ. 3፥ 16, 11 ፥21 ፥ ኢያ.23 ፥2፥ መሳ.21 ፥ 16 ፥ 1 ነገ.21 ፥8) በጌታም ጊዜ ነበሩ ። (ማቴ. 15 ፥2, 21 ፥23 ፥ 26, 57) ከካህናት ፥ ከሽማግሌዎችና ከጸፎች የተውጣጡ "ሸንጎ" ተብለው የተሰየሙ ነበሩ ። (ማር.15 ፥1) ጌታ በነዚህ ሸንጎ ፊት ቀርቦ ነበር ። (ማቴ.56 ፥59) ሐዋርያትም በሸንጎ ፊት ቀርበው ነበር ። (ሥራ 5 ፥21 6 ፥ 12, 22 ፥ 30)

ከታሪክ እንደምንረዳው የዚህ የሸንጎ አባል መሆን የሚችል ዕድሜው ከ30 ዓመት በላይ የሆነና ያገባ መሆን አለበት ። የዚህ የሸንጎ ቁጥር 70 ወይም 72 ይሆናል ።

እንግዲህ ክርስትና የጀመረው ከአይሁድ ስለነበር ቤተክርስቲያንም ስትቋቋም የአስተዳደርን ሁኔታ የወሰደችው ከአይሁድ መሆኑ ነው ። (ሥራ 11 ፥30 ፥11 ፥23 ፥15 ፥2 ፥1 ጢሞ. 5 ፥ 17 ፥ ቲቶ1 ፥5 ፥ ያዕ. 5፥14 ) ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የሚያበቃ በ1 ጢሞ. 3 ፥ 1—7 ፥ በቲቶ 1 ፥ 5—9 የተዘረዘሩ ስለሆነ ከዚህ መመልከት ይቻላል ። የሚገርመው በሰማያዊም አገር ሽማግሌዎች መኖራቸው ነው ። (ኢሳ.23 ፥24 ፥ ራዕ. 4 ፥4 11 ፥ 8, 16)

## መ.2 የእረኞች ወይም የሽማግሌዎች አገልግሎት

እረኞች ወይም ሽማግሌዎች እንደ ሐዋርያት ፣ እንደ ወንጌላውያንና እንደ ነቢያት እየተዟዟሩ ሳይሆን ፣ በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ተቀምጠው የዳኑትን ነፍሳት የሚያገለግሉ ናቸው ።

ዋና ዋና ተግባራቸውም ፤

1. ከመንጋው መሐል የጠፉትን መፈለግ ፣
2. የባዘኑትን መመለስ ፣
3. በሕይወታቸው የተሰበሩትን መጠገን ፣
4. በሕይወታቸው የደከሙትን ማጽናት ፣
5. ባሉበት ሔደው መጐብኘት ፣
6. ለመንጋዎቻቸው በሕይወታቸው ምሳሌ ሆኖ መታየት ፣
7. በወቅቱ አስፈላጊውን መንፈሳዊ ምግብ መስጠት ፣
8. አጥፊዎችን ተገቢውን ምክርና ተግሳጽ መስጠት ሲሆን ፣

በአጠቃላይ መንጋውን መጠበቅ ነው ። (ሕዝ.34 ፥1—16 ፣1ጴጥ. 5 ፥2—3 ፣ ማቴ. 24 ፥45 ፣1ተሰ.5 ፥12 ፣2ጢሞ. 4 ፥2 ፣ ሥራ 20 ፥ 31)

## መ.3 እውነተኛ እረኞች የጌታን ፈለግ መከተል አለባቸው ፤

እውነተኛ የበጐች እረኛና የእረኞችም አለቃ እርሱ ነውና።(1 ጴጥ. 5፥4 ዮሐ. 10 ፥ 11)

1. እርሱ በጐቹን ሁሉ ያውቃል ። (ዮሐ.10.14-15)

2. እርሱ በጐቹን ሁሉ ይወዳል ። (ዮሐ. 10 ፥11 ፣ 1ዮሐ.3 ፥16) መንጋውን የማይወድ እረኛ በጐቹን ለጉዳት ይሰጣል ። (ዮሐ.10 ፥ 12 — 13) መንጋዎቹም ይበተናሉ ። (ኤር. 10 ፥21, 23 ፥1)

ስለዚህ ከእረኞች የሚጠበቀው ኃላፊነት እጅግ ከባድ ነው ። ከመንጋው አንዲት ነፍስ ብትጠፋ እግዚአብሔር ያቺን ነፍስ ከእረኛው እጅ ይፈልጋል ። (ሕዝ.34 ፥9—10) መተካት ስለማይቻል በግዴለሽነት የሚመላለሰውን መጋቢ ከሁለት እንደሚሰነጥቀውና ዕድሉም ከግብዞች ጋር እንደሚያደርገው ጌታ አስጠንቅቋል ። (ማቴ.24 ፥ 48) ይህን ለማስፈራራት አላለም ። ጌታ ለሰው ፊት አያዳላም ። ያለውን ይፈጽማል ። ሆኖም ጌታ የሾማቸው ልባምና ታማኝ መጋቢዎች መንጋውን ሲንከባከቡና ሲመሩ ጌታ ሲያገኛቸው ባለው ሁሉ ላይ ይሾማቸዋል ። የክብርም አክሊል ይሰጣቸዋል ። (ማቴ.24 ፥45—47 ፣1ጴጥ. 5 ፥4)



## መ.4 ከመንጋው ምን ይጠበቃል ?

ሽማግሌዎች ወይም እረኞች የምንላቸው ለመንጋው ታላቅ ኃላፊነት እንዳላቸው ሁሉ መንጋውም ለእረኞቻቸው ማድረግ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች አሉ ።

1. እረኞቻቸውን ማወቅና መታዘዝ አለባቸው ። (1ተሰ. 5 ፥ 12) ለእረኞች የማይታዘዙና የማይገዙ መንጋዎችን መጠበቅና መንከባከብ በጣም ያስቸግራል ። እረኛውን የማያውቅና የማይታዘዝ አደጋ ይደርስበታል ።

2. አክብሮት መስጠት አለባቸው። (1ጢሞ. 5 ፥17) ይህ በፍቅርና በውዴታ የሚሆን ነው ። ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን አክብሮት ማሳየት የሚጀምረው በዚህ ነው ።

3. በኑሮአቸው መደገፍ አለባቸው ። (1ጢሞ. 5 ፥ 18) መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በቤተክርስቲያን ያሉ ሽማግሌዎች ወይም እረኞች የምንላቸው እነርሱ የሚያሰላስሉት ሌላ ነገር ሳይሆን መንጋውን እንደሆነ ነው ። (ዕብ.13 ፥ 17) ጊዜያቸውና አእምሮአቸውን የያዘ የቤተክርስቲያን ጉዳይ የመንጋውን ሕይወት ማሰብ ስለሆነ መንጋው ደግሞ መታዘዝና አክብሮት መስጠት ብቻ ሳይሆን በኑሮአቸው እንክብካቤ ማድረግ አለባቸው ። ይህ ሲሆን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ትታነጻለች ፣ ወደሚጠበቅባትም ግብ ትደርሳለች ።

## ሠ. ዲያቆናት ፤

ዲያቆናት አወጣጣቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ ከሽማግሌዎች ይልቅ ቀደም ብሎ ነው ። (ሥራ 6 ፥1—6) በእርግጥ የሽማግሌዎችን ሥራ ሐዋርያት ይሠሩ እንደነበር እንጂ ከሽማግሌዎች ይልቅ ዲያቆናት መቅደም ስላለባቸው ነው ለማለት አይደለም ።

ዲያቆን የሚለው ቃል "ዲያኩኖስ" ከሚል ከግሪክ የተወሰደ ቃል ነው ። ትርጉሙም "አገልጋይ" ወይም "ረዳት" ማለት ነው ። ይህ ስም በቤተክርስቲያን ውስጥ በድቁና እንዲያገለግሉ ለተሾሙ የተሰጠ ስም ብቻ ሳይሆን ለሁሉ ይሆናል ። (2ቆሮ.6 ፥4) መሰረተ ሐሳቡ ራስን ዝቅ አድርጐ ማገልገል ማለት ነው ። (ሉቃ.22 ፥24)

### የዲያቆናት አገልግሎት ፤

ዲያቆናት በመጀመሪያ በኢየሩሳሌም ባለች ቤተክርስቲያን ሲመረጡ ሕዝቡን በምግብና ዕደላ እንዲያገለግሉ ነበር ። ኋላ ግን እንደሽማግ

ሌዎች መመዘኛ ወጥቶ በቤተክርስቲያን ይሾሙ ጀመር ። ተጨማሪ አገልግሎታቸውን ግን ብዙ አናውቅም ። በአሁኑ ጊዜ ግን ዲያቆናት በአንዳንድ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ሽማግሌዎች ሆነው አስተዳደርነክ በሆነ ጉዳይ አገልግሎት ይሰጣሉ ። በአጠቃላይ የዲያቆናት አገልግሎት የሚከተለውን ይመስላል ።

— የጌታ እራት ሕብሥቱንና ጽዋውን ያዘጋጃሉ ፥ ለየ ዕመናን ሕብስትና ጽዋውን ያድላሉ ።

— የውኃ ጥምቀት ሲሰጥ አስፈላጊውን ዝግጅት ያደርጋሉ ።

— ምጽዋትና እሥራትን ፥ እንዲሁም ስጦታዎችን ሰብስበው ወደ ሽማግሌዎች ያመጣሉ ።

— ከቤት ወደ ቤት በመሄድ ችግረኞችን በመጐብኘትም ሽማግሌዎችን ያግዛሉ ።

— በአጠቃላይ ዲያቆናት የሽማግሌዎች የቅርብ ረዳቶች ሆነው በቤተክርስቲያን ውስጥ ጌታን ያገለግላሉ ። ይህንንም የዲያቆናት አገልግሎት በሮሜ 12:7-8 በመንፈስ ቅዱስ የሚሰጥ የጸጋ ስጦታ እንደሆነም እናያለን ።

በዚህ ውስጥ "አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ" ሲል ሌላውን አገልግሎት ሳይሆን የዲያቆናት አገልግሎት ማለቱ ነው ። ስለዲያቆናት ብቃት በ1 ጢሞ. 3 ፥8—10 ላይ ስንመለከት ለሽማግሌነት ከተሰጠው ብቃት ከአንድ ነገር በስተቀር ሁሉም ነጥብ ይመለከታቸዋል ። እርሱም ማስተማር መቻል የሚለው ነው ። ስለዚህ ኃላፊነታቸውም ያንኑ ያህል በቤተክርስቲያን ውስጥ እጅግ ከፍ ያለ እንደሆነ እናያለን ።



# ምዕራፍ ሰባት

# አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ማደራጀት

"ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ" ቲቶ 1 ፥ 5

ወንጌልን ከማዳረስ ጐን አብሮ ሊታሰብበት የሚገባ ነገር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን የማደራጀቱ ሁኔታ ነው ። ይህ ካልሆነ በቀር ዘር በማሳ ዘርቶ እንደ መተው ነው ። አንድ ገበሬ እርሻ አርሶ ከዘራ በኋላ ዝም ብሎ አይተውም ። እርሻውን በሚገባ ይጠብቃል ። የመከር ጊዜ ሲደርስ አዝመራውን ይሰበስባል ። በዚሁ ረገድ አንዲት ቤተክርስቲያን የወንጌል ቃል ከዘራች በኋላ ቃሉን የተቀበሉትን እየተንከባከበች በማሳደግና በማደራጀት ራሳቸውን ማስቻል አለባት ።

ስለቤተክርስቲያን አደረጃጀት ወይም አመሠራረት ስናስብ ወደ መጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን ሁኔታ ሄደን ማየት አለብን ። የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን አሁንም ወደፊትም ሊመሠረቱ ካላቸው አጥቢያ ቤተክርስቲያናት እንደ ሞዴል (አርአያ) መታየት አለባት ። ስለዚህ በዚህ ክፍል ውስጥ በቅድሚያ ስለመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን መስፋፋትና ሌሎች አጥቢያዎችን እንዴት ታደራጅ እንደነበር እናያለን ።

## ክፍል 1. የመጀመሪያይቱ ኤክሌሽያ መስፋፋት

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ እንዳየነው ኤክሌሽያ በጰንጠቆስጤ ዕለት (በበዓለ ሃምሳ ቀን) ተወለደች ። ከዚያም በኋላ ደቀመዛሙርቱ ጌታ እንዳዘዛቸው ወንጌልን በአካባቢያቸው መስበክ ጀመሩ ። ይህ ሲሆን የአገልግሎታቸው ሁኔታ ሶስት መልክ ነበረው ። አንደኛው በቤተመቅደስና ከቤት ወደ ቤት በመሄድ መስበክና መመስከር ሲሆን ( ሥራ5 ፥ 42)፥ ሁለተኛ ደግሞ ከየአገሩ ወደ እነርሱ የሚመጡትን በመቀበል ለበሽተኞች በመፀለይ ስለጌታ መመስከር ነበር (ሥራ 5 ፥16) ፥ ሶስተኛው ደግሞ ያመኑትን በማስተማር ፥ ደቀመዝሙር ማድረግ ነው ። ሥራ2 ፥ 42 ።

በዚህ ሁኔታ አማኞች በየዕለቱ እየጨመሩ ይበዙ ነበር፥ሥራ 2 ፥ 47

ሀ/ ለመጀመሪያይቱ ኤክሌሽያ ቶሎ ማደግ ምክንያት የሆኑት ነገሮች ፥—

1. የመሪዎች ቃሉን ማስተማርና በጸሎት መትጋት ። (ሥራ 2 ፥ 42 ፥ 6 ፥2) በዚያን ጊዜ የነበሩ መሪዎች በየጥቃቅኑ ነገሮች እየገቡ አይባክኑም ነበር ። ሥራ 6 ፥2 ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማርና ለጸሎት በቂ ጊዜ ነበራቸው ። በዚህ ምክንያት የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወቷ ጠንካራ ነበርና የሚድኑት ዕለት በዕለት ይጨመሩ ነበር ።

2. ይደረጉ የነበረ ምልክቶችና ድንቆች ፥ ሥራ 4 ፥ 16 ፥ 5 ፥ 16 የወንጌል ስብከት ከድንቆችና ከምልክቶች ጋር ሲሆን ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋትና ማደግ ታላቅ ድርሻ አለው ። ሰዎች ድንቅና ተአምራትን ሲያዩ ልባቸው ለወንጌል ቃል ይከፈታል ። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተቀበሉ አገልጋዮች ወንጌል ሲሰበክ ድንቅና ተአምራት ደግሞ ይሆናል ። "የታወቀ ምልክት በእነርሱ እጅ እንደተደረገ በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሁሉ ተገልጦ አልና ፥ እንሸሽገውም ዘንድ ለንችልም" ሥራ 4 ፥16 ይህንን ያሉት ተቃዋሚዎቻቸው ነበሩ ። የእግዚአብሔርን ሥራ ሊሸሽጉትና ሊያስተባብሉ ቢፈልጉም እንኳን እንደማይቻላቸው ተገነዘቡ ።

3. የደቀመዛሙርት ፍጹም አንድነት ፥ ሥራ 2 ፥ 46 ፥ 4 ፥ 32 አስቀድሞ እርስበርሳቸው ይከራከሩና ይጣሉ ነበር (ሉቃ.9 ፥46 ፥ ማር. 10 ፥ 41) መንፈስ ቅዱሳን ከተቀበሉ በኋላ አንድ አካል ሆኑ ፥ (1ቆሮ.12 ፥ 13) "ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበራቸው" ሥራ 4 ፥ 32

ስለዚህም በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው (ሥራ 4 ፥33) ጌታም በሕዝቡ ሁሉ ፊት ሞገሥን ሰጣቸው ። ስብከታቸው ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውና ኑሮአቸው የብዙ ሰዎችን ሕይወት ይማርክና ይስብ ነበር ።

ለ. ሌሎችን አጥቢያ ኤክሌሽያን በየቦታው መመሥረትና ማስፋፋት ።

ጌታ ባረገበት ዕለት ለደቀመዛሙርቱ ኃይልን በመንፈስ ቅዱስ ከተቀበሉ በኋላ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ወንጌልን መስበክ እንዳለባቸው አስገንዝቧቸው ነበር ። (ሥራ. 1፥8) እነርሱ ግን ከኢየሩሳሌም አካባቢ አልፈው በዓለም ሁሉ ወንጌልን ለማዳረስ ሲያቅዱ አናይም። ነገር ግን ስደት በተነሳባቸው ጊዜ ሐዋርያት ብቻ በኢየሩሳሌም ሲቀሩ ሌሎች ደቀመዛሙርት ወደ የአገሩ ሁሉ ተበተኑ ። ሥራ.8 ፥1



ይህን ደግሞ እግዚአብሔር ለመልካም አደረገው ። ሁሉም በየሄዱበት አገር ወንጌልን ይሰብኩ ነበር ። (ሥራ 8 ፥4) ደግሞ ወንጌል ወደተሰበከባቸው አገሮች ሌሎች አገልጋዮችን ከኢየሩሳሌም ይልኩ ነበር ። ሥራ 11 ፥ 19—22 ራሳቸውም በመሔድ ላመኑ ሰዎች እጅ በመጫን ለመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ለፈውስ ይጸልዩላቸው ነበር ። ሥራ 8 ፥ 14 ፥ 9 ፥ 32 ፥ ይሁን እንጂ ለየአጥቢያ ቤተክርስቲያን መሪዎችን ከመሀላቸው ሲሾሙላቸው አናይም ምናልባት ከነዚህ አዳዲስ ክርስቲያኖች ለመሪነት የሚበቃ አይኖርም ብለው አስበው ይሆናል ። የመሪነትን ደግሞ ወይምቦታ መያዝ የሚገባቸው አይሁዶች ብቻ መሆን አለባቸው የሚል ሀሳብ ይኖራቸው ይሆናል ። ስለ አሕዛብ መዳን እንኳን ገና ያልተቀበሉና ያልገባቸው ነበሩና ። ሥራ 11 ፥ 1—215 ፥ ፥1—2

በኋላ ግን መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስንና በርናባስን በተለየ መንገድ ጠራቸው ። (ሥራ 13 ፥2) እነርሱም በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ወንጌልን ለአሕዛብ መስበክ ጀመሩ ፥ ሥራ 13 ፥ 4—5 46—48 ፥ 14 ፥ 1—6 ። ወንጌልን ወደሰበኩባቸው ከተማዎች ተመልሰው የሚመሯቸውን ሽማግሌዎች በጾም በጸሎት ሆነው ሾሙላቸው ። ሥራ 14 ፥22—23 ። ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለሽማግሌዎችና ስለዲያቆናት ሹመት አሰጣጥ ለሌሎች አገልጋዮች ኃላፊነትና አመራርን ሲሰጣቸው እናያለን ። ቲቶ 1 ፥ 5—9 ፥ 1ጢሞ.3 ፥ 1—13

ሆኖም እነዚህ መሪዎች የዕለት በዕለት ተግባራቸው ምን መሆን እንዳለበት በዝርዝር አልተገለጸም ። የተጠቀሰ ነገር ቢኖር መሪዎች ማስፈለጋቸውና ማሟላት የሚገባቸው ብቃት ነው ። በዚህም ምክንያት ይሆናል በአሁኑ ዘመን ያሉ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንድ ወጥ የሆነ የአስተዳደር ሁኔታ የሌለው ።

## ክፍል 2 <u>በዚህ ዘመን አጥቢያ ቤተክርስቲያንን ማደራጀት</u> ።

"ኃጢአተኞች ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው"። 1 ጢሞ.1፥15 በሌላ ሥፍራ ደግሞ ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ ? ይላል ሮሜ 10፥14 ። ታዲያ የምሥራቹን ቃል ለሰው ሁሉ ለማሰማት አመቺ ሁኔታን መፈለግ ያስፈልጋል ። ለዚህ ደግሞ በየአካባቢው አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ማቋቋም ለአካባቢው ሕዝብ በቀላሉ ወንጌል ለማዳረስ ከሁሉም የተሻለ መንገድ ነው ።

1ኛ/ በአካባቢያቸው (በቅርባቸው) ቤተክርስቲያን ካለ ያካባቢው ሕዝብ ሄደው የወንጌል ቃል ለመስማት ያመቻቸዋል ።

2ኛ/ ከሩቅ ሥፍራ ወደ ቤተክርስቲያን ለመምጣት አቅመ - ደካማ የሆኑትን አባላትን በአካባቢያቸው ለመያዝ አመቺ ነው ።

3ኛ/ የተጠሩ አገልጋዮች የአገልግሎት ሥፍራ ይኖራቸዋል ። አገልጋዮች አንድ ቦታ ከተከማቹ ሰፊ የአገልግሎት በር አይኖራቸውም። ኃላፊነቱን ሥፍራ የሚይዙት ጥቂቶች ይሆናሉ ። አገልጋዮች ኃላፊነት ካልተሰጣቸው ትጋት አይኖራቸውም ። ኃላፊነት እንዲሰማቸው በኃላፊነት ቦታ ማስቀመጥ ያስፈልጋል ። ስለዚህ የመከሩን ጌታ አገልጋዮችን እንዲያስነሳ መጸለዩ ብቻ በቂ አይደለም ። የአገልግሎትን መስክ ማመቻቸት ያስፈልጋል ። አገልጋዮች ሲበዙ በዚያኑ ልክ አዝመራው ይሰበሰባል ።

ሀ/ የደረጀች ቤተክርስቲያን ሌሎች አጥቢያዎችን ለመመሥረት ስታስብ ልትወስደው የሚገባ እርምጃ ፤

አንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአካባቢዋ ወንጌልን በማዳረስ ሌሎች አጥቢያዎችን ለማስፋፋት ስታቅድ የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን ፈለግ መከተል ያስፈልጋታል ።

1ኛ/ በጾምና በጸሎት መትጋት ። ሥራ 13፡1-4

በእርግጥ ጾምና ጸሎት ወንጌልን ለማዳረስ ሲታሰብ ብቻ የሚደረግ አይደለም ። እንዲያውም በጾምና በጸሎት የማትተጋ ቤተ ክርስቲያን መንፈሣዊ ልምምድ ሊጐድላት ይችላል ። መንፈሣዊ ልምምድ የሚጐድላት ከሆነ ደግሞ መንፈሣዊውን ሥራ እንደሚገባ መሥራት አትችልም ።

2ኛ/ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት መቀበል ሥራ 1፡8

ወንጌል ኃይል የሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲሰበክ ነው ። ሥራ 4፡31፣13፡9። የወንጌልን መልእክት በኃይልና በሥልጣን ለመስበክ የምትፈልግ ቤተክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መቀበል አለባት ። ሥራ 1፡8

3ኛ/ በቃሉ ሙላት ማደግ ቆላ.3፡15

"በእናንተ ስላለው ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቃችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁሉ " ይላልና ። 1ጴጥ.3፡15 በሌላ ሥፍራ ደግሞ "ከጊዜው የተነሣ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕጸንነት ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደገና ያስፈልጋችኋልና ..." ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ "ይላል ። ዕብ.5፡12፡6፡1። ስለዚህ ማኅበረ-ምዕመናን መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት በመማር ብቻ ተወስነው መቅረት የለባቸውም ። ሥርዓት ባለው ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል ደረጃ በደረጃ ማስተማርና ማሳደግ ያስፈልጋል ። ያን ጊዜ ሁሉም የሕይወትን ቃል ለዓለም በማቅረብ እንደ ብርሃን ይታያሉ ። ፊል.2፡15-16

4ኛ/ አባላትን ሁሉ ለወንጌል ሥርጭት ማንቀሳቀስ ።

የወንጌል አገልግሎት ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ብቻ የሚተው አይደለም ፤ ያመነ ሁሉ ሊመሰክር ተጠርቷል ። 1ጴጥ.2፡9። በተለይ ሌሎች አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ለመመሥረት ሲታቀድ አባላትን በሁለት አቅጣጫ መጠቀም ይቻላል ።

አንደኛ መንገድ ከአባላት መካከል ከፍተኛ ቅንዓት ያላቸውን በቡድን በቡድን ማሰባሰብ ፤ ከዚያም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የጸሎት ፕሮግራም ከቤተ ክርስቲያን ራቅ ብሎ በሚኖር አባላት ቤት መጀመር ። እነዚህ ለአካባቢ ነዋሪዎች እየመሰከሩ ወደ ፕሮግራማቸው እንዲጋብዙ ዘወትር ማነሳሳት ። ከዚያም ያመኑትን በማደራጀትና በማሳደግ ቀስ በቀስ ወደ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ደረጃ ማድረስ ይቻላል ።

ሁለተኛ መንገድ የደረጀች ቤተክርስቲያን በእናትነት ሌላ አጥቢያ ቤተክርስቲያንን እንድትወልድ የማድረግ ዘዴ ነው ። ይህ የሚሆነው ከርቀት የሚመጡትን አባላትን በአካባቢያቸው በማሰባሰብ ፤ አገልጋዮችን በማሠልጠን አጥቢያ ቤተክርስቲያን እንዲሆኑ ማድረግ ነው ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እንደ ልጅ የሆነች ቤተክርስቲያን ሌሎች አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን ወደ መውለድ ትደርሳለች ማለት ነው ። በዚህ ሁኔታ አጥቢያ ቤተክርስቲያናትን በየአካባቢው በመመሥረት ወንጌል ለሰው ሁሉ በቀላሉ ማዳረስ ይቻላል ።

ለ/ <u>አዲስ የተቋረቋረችን ቤተክርስቲያን ቶሎ ራሷን የማስቻል አስፈላጊነት</u> ፤

አዲስ የተቋረቋረች አጥቢያን ቶሎ ራሷን ማስቻል በጣም አስፈላጊ ነው ። ለረጅም ጊዜ በጥገኝነት የምትተዳደር ቤተክርስቲያን ልታድግና ልትስፋፋ አትችልም ። ማኅበረ-ምዕመኑ የሌላ ቤተክርስቲያን ተቀጥያ

አድርገው ራሳቸውን ስለሚቆጥሩ የራሳቸውን ሕልውና ዝቅ አድርጎ የማ
የት ሁኔታ ይፈጠርባቸዋል ። ከዚህም ሌላ በአካባቢያቸው ወንጌል ለማ
ዳረስ ብዙዎቹ ኃላፊነት ሊሰማቸው አይችልም ።

በሌላ መልኩ ደግሞ ማኅበረ- ምዕመኑ እያደገ ከሄደ ራስን በራስ
የመቻልና የማስተዳደር ፍላጐት ሊያድርባቸው ይችላል ።

ሁልጊዜ የሌላውን ውሳኔ መጠበቅ ይሰለቻቸው ይሆናል ። በተለይም
ከሌላ ቦታ ውሳኔ በመጠበቅ ሥራቸውን ሲያጓትትባቸው ካዩ ቶሎ ራስን
የመቻል ፍላጐት ስለሚያድርባቸው ያልታሰበ ችግር ሊፈጠር ይችላል ።
ስለዚህ አዲስ የተቆረቆረችን አጥቢያ ቶሎ ራሷን ማስቻል አስፈላጊ ነው።

አዲስ የተቆረቆረች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ራሷን ለማስቻል ሲታ
ሰብ መታየት ያለባቸው ነገሮች አሉ ።

1/ <u>በአስተዳደር ራሷን ማስቻል ፣</u>

አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአንድ አካባቢ ለመመሥረት ሲታቀድ ወዲ
ያውኑ የአስተዳደር ጉዳይ አብሮ ሊታሰብበት ይገባል ። ሐዋርያት
ወንጌል ከሰበኩ በኋላ ብዙ ሳይቆዩ ብቃት ያላቸውን ዓይተው ጾመው
ጸልየው ሽማግሌዎች አድርገው ሾሙላቸው ። ሥራ 14፡23 እነዚህኑ
አጥቢያዎች በሌላ ጊዜ ሐዋርያት ሲጐበኙአቸው ፣ በእምነታቸው
ጠንክረው በቁጥር በዝተው እንዳገኙአቸው እናነባለን።ሥራ 16፡1-5
በአሁኑም ዘመኑ አዲስ የተቆረቆረችን ቤተክርስቲያን መሪ ሊሆኑ
የተጠሩትን ከመሀከላቸው በመምረጥ ተከታታይ ሥልጠናዎችን
በመስጠት ችሎታቸውን ማዳደግና ኃላፊነት እንዲኖራቸው ማድረግ
አስፈላጊ ነው ። በመጀመሪያ ግን "የእግዚአብሔርን ቃልና የእግ
ዚአብሔርን መንፈስ የተቀበለ ሕዝብ ራሱን ይችላል " በማለት
እምነት ሊጣልባቸው ይገባል ።

2. <u>በወንጌል ሥርጭት ራስን ማስቻል ።</u>

አንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን አቅሟ በሚፈቅድላት መጠን ወን
ጌልን በአካባቢዋ የማዳረስ ኃላፊነት አለባት ። ወንጌልን መስበክ
የጌታ ትዕዛዝ ስለሆነ ምንጊዜም ቢሆን ወንጌል መስበክ የቤተክር
ስቲያን ዓላማ መሆን አለበት ። ማር. 16፡15 ወንጌልን የማትሰብክ
ቤተክርስቲያን ድሃና አቅመ - ቢስ ትሆናለች ። የኋላ ኋላም በዓለም
ልትዋጥና ሕልውናዋን ልታጣ ትችላለች ። የቤተክርስቲያን ሕል
ውና በወንጌል ነውና ወንጌልን የምትሰብክ ቤተክርስቲያን ግን ለሕ
ውናዋ ዋስትና አላት ። ጌታም ወንጌልን ለምትሰብክ ቤተክርስቲያን



አብሯት እንደሚሠራ ተናግሯል ። ማቴ.28፡18-20፣ማር. 16፡20
አንዲት ቤተክርስቲያን ችግር የሚገጥማት ወንጌልን መስበክ ስት
ተው እንደ ሆነ ደጋግሞ ማስገንዘብ ያስፈልጋል ።

ታዲያ ማኅበረ- ምዕመናንን ለወንጌል ሥራ ለማነሳሳት የመሪዎች
መንፈሣዊ ሕይወት ወሣኝነት አለው ። መሪዎች በመንፈስ ቅዱስ
ካልተነቃቁ ማኅበረ- ምዕመናን ለማነቃቃት አይችሉም ። መሪ
ዎች ወዳልደረሱበት መንፈሣዊ ሕይወት አባሎቻቸውን ማድረስ
አይችሉምና ። ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ አካባቢውን በወንጌል
መልእክት ለማድረስ ልምድ እንዲያደርግ ከተፈለገ ከመሪዎች ጀምሮ
ማኅበረ- ምዕመናንን ሁሉ ማነቃቃትና ክትትል ማድረግ ተገቢ
ነው ። ያን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ሲያነቃቃቸው ለእግዚአ
ብሔር ሥራ ታጥቀው ይነሳሉ ። ሐጌ 1፡13 -15 አለበለዚያ በሰው
ችሎታና ዘዴ የሚደረግ እንቅስቃሴ ውጤት አይኖረውም ።እግዚ
አብሔርም ከብዙ ዘመናት በፊት ይህንኑ አስገንዝቧል ። ዘካ.4፡16
ስለዚህ አማኞች ለሁሉም ነገር በእግዚአብሔር መንፈስ እንዲታ
መኑ ዘወትር ማነሳሳት ያስፈልጋል ።

3. በገንዘብና በቁሳቁስ ራስን ማስቻል ።

ገንዘብ በዚህ ዓለም ለማናቸውም ሥራ አስፈላጊ ነው ። ቤተክርስቲ
ያን የገንዘብ እጥረት ከገጠማት ከጥገኝነት ልትላቀቅ አትችልም ።
ይሁን እንጂ በገንዘብ ራስን ለመቻል ተብሎ የወንጌል ስብከት ገን
ዘብ መሰብሰቢያ መንገድ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። በሌላ
በኩል ደግሞ የቤተክርስቲያን የገቢ ምንጭ እንደ እግዚአብሔር ቃል
አባላት በሚሰጡት አሥራትና ምፅዋት መሆኑ የታወቀ ነው ።ሚል
3፡10-12 ይህ ሲሆን አባላት በደስታ መስጠት እንዳለባቸው ማስተ
ማር ያስፈልጋል ።2ቆሮ. 9፡6-7 በአንዳንድ ቤተክርስቲያን መሪዎች
ገንዘብ ወዳድ እንዳይባሉ ማኅበረ - ምዕመኑን ስለገንዘብ አሰጣጥ
አያስተምሩም ። ሆኖም የእግዚአብሔር ቃል ስለሚያዝ በግልጽ
ማስተማር ያስፈልጋል ።

በደስታ ለሚሰጡ እግዚአብሔር በሠማያዊ አገር በዚህ ዓለምም አብ
ዝቶ እንደሚባርካቸው በቃሉ ተናግሯል ። ሚል 3፡10፣ሉቃ.6፡38፣12፡33

ለዚህ የመጀመሪያይቱን ቤተክርስቲያን ልምምድ ማስታወስ ያስፈ
ልጋል ። አባላት ያላቸውን ሁሉ በደስታ ይሰጡ ነበር ። ታዲያ ከመሀከላ
ቸው አንድም ችግረኛ አልነበረም ። ሥራ 4፡32-34

በዚህ ዘመን ያሉ አማኞችም ሕይወታቸውና ኑሮአቸው በበረከት
የተሞላ እንዲሆን ከተፈለገ በደስታ መስጠትን ከጅምሩ መማር አለባቸው

የእያንዳንዱ አማኝ መበልፀግ የቤተክርስቲያን መበልፀግ ይሆናል ፡፡ በዚህ ሪገድ ከተሄደ እንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን በሌላዋ ላይ ጥገኛ የምት ሆንበት መንገድ አይኖርም ፡፡

ሐ/ <u>መሥራች ቤተክርስቲያን አዲስ ለተመሠረተች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ያለባት ኃላፊነት</u>

መሥራች የሆነች ቤተክርስቲያን አዲስ የተቆረቆረችን ቤተክርስቲያን እስከትደረጅ ድረስ መከታተል ያስፈልጋታል ፡፡ አለበለዚያ ችግሮች አብረው ሊመሠረቱ ይችላሉ ፡፡ ስለዚህ የሚከተሉትን መሠረታዊ ነገሮች ማስያዝ አለባት ፡፡

1. አዲስ ለተመሠረተች ቤተክርስቲያን የመሪዎችን ድርሻና የማኅበረ ምዕመናንን ድርሻ ለይቶ ማስረዳት ፤

መሪዎች ማኅበረ ምዕመናኑን መንከባከብና መምራት የሚችሉት ማኅበረ ምዕመኑ በፈቃዳቸው መሪዎቻቸውን መከተል ሲችሉ ነው ፡፡ ተሰ 5፡12 ዕብ. 13፡17 ማህበረ ምዕመናን መሪዎቻቸውን መከተል የሚችሉት ደግሞ መሪዎች ሊመሯቸው እስከቻሉ ድረስ ነው ስለዚህ መሪዎች በየጥቃቅኑ ነገር እየገቡ ሥልጣናቸውን ማስገንዘብ ያስፈልጋል (ሥራ 6፡2)

2. አገር አቀፍ የሆነችው (ዲኖሚኔሽን) ቤተክርስቲያን የምትመራበትን የእምነት አንቀጽና መተዳደሪያ ደንብ በትክክል ማስረዳት ፣ አለበለዚያ የቤተክርስቲያንን ማዕከላዊ አሠራር ሊያፋልስ የሚችል ነገር ሊፈጠር ይችላል ፡፡

3. መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ደረጃ በደረጃ ማስተማር ፣
በመሠረቱ ለክርስቲያኖች ሁሉ መመሪያቸው መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም ብዙዎች በክርስትና ስም የሚጠሩ መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው እያሉ ፣ ነገር ግን የስህተት ትምህርት የሚከተሉና የሚያስፋፉ አልታጡም ፡፡ ስለዚህ አዲስ ለተመሠረተች ቤተክርስቲያን "መመሪያችን መጽሐፍ ቅዱስ ነው" ማለቱ ብቻ በቂ አይደለም ፡፡ መሠረታዊ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ሥርዓት ባለው ሁኔታ ማስተማር ያስፈልጋል ፡፡

4. ከሌሎች መሰል አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ሊኖር የሚገባውን ጤናማ ግንኙነትና ኅብረት ምን መምሰል እንዳለበት ማስረዳት ፤

በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መሀከል ያለው ልዩነት የስም ልዩነት ብቻ ከሆነ ሁሉንም እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ማየት አስፈላጊ ነው ፡፡ እኔ የዚህ ነኝ ፣ እኔ የዚያ ነኝ ማለቱ የቆሮንቶስን ቤተክርስቲያንም እንዳስነቀፈ ማየት ይቻላል ፡፡ (1ቆሮ.1፡12-15) ይሁን



እንጂ ሁሉም ያለበትን አጥቢያ ቤተክርስቲያን የመንፈስ አንድነት መጠበቅ አስፈላጊ እንደሆነ ማሳሰብ ተገቢ ነው ፡፡ ኤፌ.4፡3

5. ቤተክርስቲያን ከመንግሥት አካላት ጋር ሊኖራት የሚገባውን አቋም በግልጽ ማስረዳት ፣

ምናልባት አገር አቀፍ የሆነችዋ (ዲኖሚኔሽን) ቤተክርስቲያን በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ይህን በሚመለከት የተጠቀሰ አንቀጽ ሊኖር ስለሚችል ይህንኑ ገልጾ ማስረዳት በቂ ሊሆን ይችላል ፡፡

6. የቤተክርስቲያን መብዓ እና አሥራት አሰባሰብ የሚከተሉትን መመሪያ መስጠት ፣

6.1 መብዓ እና አሥራት የመሰብሰብ ፣ የመቁጠር ሥራ ቢያንስ በሁለት የቤተ ክርስቲያንቱ ዲያቆናት መካሄድ አለበት ፡፡

6.2 የገባውን ገንዘብ ልክ የሚገልጽ ትክክለኛ ሠነድ ተመዝግቦ የቆጠሩ ሰዎች ከሠነዱ ሥር ፊርማቸውን ማኖር አለባቸው ፡፡

6.3 ከቤተክርስቲያን ሽማግሌ አንዱ የቤተክርስቲያንን ገንዘብ በጥንቃቄ እንዲይዝ መሾም ፡፡

6.4 የገንዘብ ወጪና ገቢ የመቆጣጠር ሥራ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ኃላፊነት መሆኑን ማስገንዘብ ፡፡

7. የቤተክርስቲያን መሪ የሆኑትን የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድ አወጣጥና በጀት አሠራር በቂ ትምህርት መስጠት ፤

በጀት ሲሠራ ከዚህ የሚከተሉትን ጉዳዮች ቅድሚያ እንዲሰጡ ማስረዳት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ፡፡

7.1 የቤተክርስቲያን የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ቀለብ ሚል .3፡10፣ "እንግዲህ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጓል " ይላልና 1ቆሮ.9፡14፤ ሉቃ.10፡7 ፡፡ ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ቀለብ ለመመደብ የአካባቢውን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ መካከለኛ መነሻ አድርጐ መውሰድ ይቻላል ፡፡ ሆኖም የቤተክርስቲያኒቱ የገቢ አቅም ወሳኝነት እንዳለው ማስገንዘብ ያስፈልጋል ፡፡

7.2 ለወንጌል ሥርጭት ፤

ለአካባቢው ሕዝብ ወንጌልን ለማዳረስ ፣ አባላትን በቡድን ለመላክ ፤ ወጪያቸውን መቻል ፣ ትራክቶችንና ጽሑፎችን ለማዘጋጀት በሁለተኛ ደረጃ በጀት መመደብ ይቻላል ፡፡

7.3 ለአባላት የመማሪያ መጣሪያዎችን ለማዘጋጀት ፤

አባላት በእግዚአብሔር ቃል ተኮትኩተው እንዲያድጉ የትምህርት መማሪያዎችን ለማዘጋጀት በጀት መመደብ ያስፈልጋል ።

7.4 ለጥገና ሥራዎች ፡

የጸሎት ቤትና የመማሪያ ክፍሎች ፣ ተሽከርካሪ መኪኖች ፣ መቀመጫዎች ፣ እንዲሁም በቤተክርስቲያን ውስጥ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁስ መጠገኛ በጀት መመደብ አለባቸው ። የቤተክርስቲያን መገልገያ ዕቃዎች በወቅቱ ዕድሳት ካልተደረገላቸው ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሊሰጡ ሲችሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ባክነው ሊቀሩ ይችላሉ ።2 ነገሥት 12፡5-17 ከዚህ በኋላ እንደ የሁኔታውና እንደ የአስፈላጊነቱ ጥናቶችን በማድረግ በጀት ማዘጋጀት ይቻላል ።

8. የስብሰባ ሥርዓቶች ማስተማር ፤

እንዴት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ሁለት ዓይነት የስብሰባ ሁኔታ ሊኖራት ይችላል ።

8.1 የሽማግሌዎች ጉባኤ ስብሰባ ፤

ይህ ስብሰባ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የቤተክርስቲያኒቱን መንፈሣዊና አስተዳደራዊ ሥራ ላይ ለመመካከር የሚኖራቸው የስብሰባ ጊዜ ነው ። ዕብ.3፡15 በዚህ የስብሰባ ወቅት የሚከተሉትን ሥርዓቶች መከተል አስፈላጊ ነው ።

8.1.1 የሽማግሌዎች ጉባዔ ሰብሳቢ ተሰጥኦ ያለውን ከመሃከላቸው እንዲመራ መምረጥ ፤

8.1.2 ከሽማግሌዎች አንዱ የፀሐፊነት ተሰጥኦ ያለው ቃለ ጉባዔና ውሣኔዎችን የሚይዝ መምረጥ ፤

8.1.3 በስብሰባ ወቅት መወያያ አጀንዳ ማዘጋጀት የሰብሳቢው ኃላፊነት እንደሆነ ማስገንዘብ ፤

8.1.4 አባላት አስፈላጊ ከሆነ በአጀንዳው ላይ መጨመር እንደሚችሉ ማስረዳት ፡

8.1.5 በውይይት ወቅት በተቻለ መጠን የሐሳብ አንድነት እንዲኖር ማስረዳት ፣ ሆኖም አስተዳደራዊ በሆነ ጉዳይ አንዳንድ ጊዜ የተለያዩ አመለካከቶች መኖራቸው የማይቀር ነው ።ይህ ደግሞ መንፈሣዊነት በማጣት ወይም በክፋት ምክንያት ላይ



ሆን ይችላል ። ስለዚህ በድምጽ ብልጫ መወሰኑ አስፈላጊ ነው ። አለበለዚያ ብዙ ሥራዎች ሊጓተቱ ይችላሉ ፣ማናቸውም ጉዳይ በጊዜ ውሳኔ ካላገኘ መበላሸቱ አይቀርም ። በድምፅ ብልጫ ከተወሰነ በኋላ ግን ሁሉም በተሰጠው ውሣኔ በአንድ ልብ መስማማት አለባቸው።ፊል.4፡1-4።

8.2 የቤተክርስቲያን የአባላት የሥራ ስብሰባ ፤

ይህ ስብሰባ የቤተክርስቲያኒቱን አባላት ብቻ የሚመለከት ስብሰባ ነው ። በዚህ ስብሰባ ወቅት አባላት ስለ ቤተክርስቲያን ጠቅላላ እንቅስቃሴ የሚሰሙበት ጊዜ ስለሆነ እጅግ አስፈላጊ ነው ። ስለዚህ ቢያንስ በዓመት ሦስት ጊዜ መደረግ አለበት ። በዚህ ስብሰባ ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች መሠረት ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል ።

8.2.1 በቤተክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች የሚቀርበውን የዓመት የሥራ ዕቅድና በጀት በማዳመጥ አባላት ጠቃሚ አስተያየቶችን መስጠት ፤

8.2.2 በሽማግሌዎች የሚቀርብ የሥራና የገንዘብ ነክ ሪፖርት መስማትና አስተያየት መስጠት ሊሆን ይችላል ። እነዚህን ልማዶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ማዳበር እጅግ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ማኅበረ- ምዕመናን በመሪዎቻቸው ላይ ሙሉ እምነት እንዲኖራቸው ያደርጋል ። ስለዚህም በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚኖረው ነገር ሁሉ ኃላፊነት ስለሚሰማቸው ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ ያስችላቸዋል ።

9. የሥነ ሥርዓት (ዲሲፕሊን) አስፈላጊነት ማስተማር ፡

ለቤተክርስቲያን መሪዎች ብዙ የሚገጥማቸው ችግር ቢኖርም ከሁሉ አስቸጋሪው ቅጣትን መስጠት ነው ። ሆኖም የማይቀር ጉዳይ ነውና የሚከተሉትን ምክሮች መከተል ጠቃሚ ነው ።

9.1 ምን ጊዜም ቢሆን ቅጣት መስጠት ዓላማው ላጠፋው አባልና ለቤተክርስቲያን ጥንቃቄ ለማድረግ ታስቦ መሆን አለበት ። 2ቆሮ. 2፡6-7

9.2 ቅጣት ከመሰጠቱ በፊት በቂ ማስረጃ ማግኘት አስፈላጊ ነው። ጢሞ 5፡19፡ማቴ 18፡16

9.3 ቅጣት መስጠት መሪዎች ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የቤተክርስቲያን ኃላፊነት ጭምር ነው ። ማቴ.18፡15-17 ፤1ቆሮ. 5፡6-13

9.4 ጥፋት ሁሉ እኩል አይደለም ። ስለዚህ የቅጣቱ ደረጃ የጥፋቱ ዓይነት ይወስነዋል ። ተግሣጽና ምክር በመስጠት ብቻ የሚታከፍ ጥፋት ሊኖር ይችላል ።1ጢሞ.5፡20

ጨርሶ ከአባልነት ሊያሠርዝ የሚያስችል የጥፋት ዓይነት ደግሞ ሊኖር ይችላል ። 1ቆሮ.5፡9፡13

እነዚህን ልምዶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ማዳበር በሥርዓት መታነጽንና መንፈሳዊ ብስለትን ይፈጥራል ። ታዲያ እነዚህን መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን አዲስ ለተቆረቆረች ቤተክርስቲያን የማስጨበጡ ጉዳይ መሥራች የሆነች ቤተክርስቲያን ኃላፊነት ነው ። መዘንጋት የለበትም ።



# ምዕራፍ ስምንት

# የኤክሌሽያ አገልግሎት

ኤክሌሽያ በዚህ ዓለም ስትኖር ትልቅ ኃላፊነት ነላት ። እግዚአብሔር በቀጥታ ነብሯት እየሠራ ያለችና እሱም እየሠራች ያለች ምድራዊ የእግዚአብሔር ድርጅት ቤተክርስቲያን ናት ።

ስለዚህ ቤተክርስቲያን በዚህ ዓለም ስትኖር ያላትን አገልግሎት በሁለት አቅጣጫ መድበን እናያለን ።

## ክፍል 1. የኤክሌሽያ የውስጥ አገልግሎት

የኤክሌሽያ የውስጥ አገልግሎት የምንለው በአማኞች መሐል የሚካሄድ መንፈሳዊ አገልግሎት ነው ። ይህም በክርስቶስም እምነት ወደሚገኘው አንድነት ለመድረስ ቅዱሳን ሁሉ እግዚአብሔርን ለማገልገል እንዲችሉ ማዘጋጀትና በመጨረሻም ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙላት ለመድረስ የሚያግዝ ነው ።(ኤፌ.4፡11-13) ስለዚህ ወደ እነዚህ ዓላማዎች ለመድረስ የሚከተሉት የአገልግሎት ዓይነቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ይከናወናሉ ።

### ሀ. አምልኮ

አምልኮ ምንድነው? አምልኮ መስገድ ወይም መገዛት ማለት ሲሆን ይህም በተለያየ ሁኔታ ይገለጻል ።

እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ሁሉ አምልኮ ይፈልጋል (መዝ.148፡1-14 ) ፡ፍጥረትም ሁሉ ፈጣሪውን ያመልካል ፥ ያመሰግናል ። ስለዚህ እግዚአብሔር ሰዎችን እንዲያመልኩት ለእራሱ ክብር ፈጥሯቸዋል ።

የእሥራኤል ሕዝብ እግዚአብሔር በሰጣቸው ሥርዓት እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር ። የሚያካሂዱትም አምልኮ ሥጋዊ ሥርዓቶች ነበሩ (ዕብ.9፡10) ቤተ መቅደሱም በሰው እጅ የተሠራ ሕንጻ ነበር። በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚካሄደው አምልኮ ግን ለየት ያለ ነው። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በልጁ በክርስቶስ የተዋጁ ክርስቲያኖች ናቸው /1ኛ ቆሮ. 3፡16/። ለእግዚአብሔር የሚቀርበው መስዋዕት መንፈሳዊ ነው /1ኛ ጴጥ.2፡4-5/። እርሱም ጾምና ጸሎት (ሥራ 13፡2/ ። እንጀራ አብሮ መቁረስ (ሥራ 2፡42/። ዝማሬ (ኤፌ.5፡19) ምሥጋና(ዕብ.13፡15) የመሳሰሉ ናቸው ። እነዚህን ለመፈጸም በመጀመሪያ ራስን ሕያው መስዋዕት አድርጐ ለእግዚአብሔር መስጠት ይቀድማል (ሮሜ 12፡1-2)።

እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ የሚሰግዱለትም በመንፈስ እንደ ሆነ ጌታ ተናግሮአል ። (ዮሐ.4፥24) ። ስለዚህ በሥጋ ያሉ ምንም ዓይነት ሥርዓቶችን ተጠንቅቀው እንኳን ቢፈጽሙ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይችሉም (ሮሜ 8፥8) ።

በሚልክያስ 3፥1-4 እንደምንመለከተው ትንቢታዊ ቃል አለ። ይህም የትንቢት ቃል ጌታ እንደ አንጥረኛ እሳትና እንደ አጣቢ ሳሙና ሆኖ እንደ ሚገለጥና ብዙዎችን እንደ ብርና እንደ ወርቅ ካጠራቸው በኋላ እነርሱም ለእግዚአብሔር በጽድቅ ማለትም ያለ ለበጣና ያለ ግብዝነት ሆነው ለእግዚአብሔር ምሥጋናን እንደሚያቀርቡ የሚገልጽ ነው ።

ስለዚህ ዮሐንስ መጥምቁ በመጣ ጊዜ ስለ ጌታ ሲናገር እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት እንደሚያጠምቅ ተናገረ (ማቴ.3፥11ዮሐ. 1፥26/። ጌታም ለደቀ መዛሙርቱ ይህንኑ እንደሚያደርግ ገልጾላቸዋል (ሥራ1፥5)። ይህም ለመጀመሪያ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት በበዓለ ሃምሣ ቀን ተጠመቁ ። ይህ ደግሞ በእነርሱ ብቻ የሚያቆም እንዳይደለ ጴጥሮስ ሲገልጽ የተሰፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችን ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው” (ሥራ 2፥39)

ስለዚህ አሁንም ቢሆን ማናቸውም አገልግሎትና አምልኮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መካሄድ ያለበት በመንፈስ ቅዱስ መሆን እንዳለበት እንረዳለን ። (ዮሐ.4፥24)።

ለ. <u>የመታነፅ አገልግሎት</u>

መታነፅ በግሪክ ቋንቋ “አይኮዶም” ይባላል ። ትርጉሙም “መገንባት” ማለት ነው ።

ይህ ቃል በድንጋይ ለሚገነባ ቤትም ሆነ (ማቴ.7፥24፥23፥29 ሥራ 7፥47/ መንፈሳዊ ቤት ለማመልከት የሚጠቀስ ቃል ነው ። (ማቴ. 16፥18፥1ኛ ጴጥ.2፥5.1ኛ ቆሮ.3፥12)

እንደገናም ደግሞ በውስጥ ሰውነት ስላለው መታነፅ ለማመልከትም የተጠቀሰ ይኸው “አይኮዶም” የሚለው ቃል ነው (ሮሜ 15፥2 1ኛ ቆሮ.14፥3 ሥራ 9፥31 1ኛ ተሰ.5፥11፥ሮሜ 14፥19።

አሁን በዚህ ክፍል ማየት የምንፈልገው መታነፅ በውስጥ ሰውነታችን ደስ ስለመሰኘት ያለውን መታነፅ ነው ። ይህ የውስጥ ሰውነት መታነጽ የሚገኘው አማኞች በአንድ ላይ በመሆን እግዚአብ



ሔርን ሲያመልኩ ፣ በመዝሙር ፣ በእግዚአብሔር ቃል ፣ በትንቢት፣ በልሣን መናገር ፣ በልሣን የተነገረውን መተርጐምና በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚካሄደው መንፈሣዊ ፕሮግራም ሁሉ ነው ። ‘1ኛ ቆሮ.14፥26-27/’

ለአማኞች የተለያዩ የፀጋ ስጦታዎችም የሚሰጠው ለየግላቸው ጥቅም ተብሎ ሳይሆን ለጋራ ጥቅም ማለትም በጋራ በአንድነት ለመታነፅ ነው (1ኛቆሮ. 12፥4-7) በኤፌ. 4፥11 ላይ የተጠቀሱት የእግዚአብሔር መጋቢዎች ለቤተክርስቲያን የተሰጡበት አንዱ ምክንያት ቤተክርስቲያን እንድትታነፅ እንደሆነ እናያለን ። (2ኛ ቆሮ. 10፥8-13፥10)

ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በሰጠን ልዩ ልዩ የፀጋ ስጦታ እርስ በርሳችን መተናነፅ ይጠበቅብናል ። (ሮሜ 15፥2)

ሐ. <u>መንፃት ፣</u>

በብሉይ ኪዳን የመንፃት ሥርዓት በተለያየ ሁኔታ ይካሄድ ነበር ። ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለዕቃዎችም የተለያየ የመንፃት ሥርዓት ይደረግላቸው ነበር ። (ዕብ.9፥22) ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች ንፁህ ሆነው መቅረብ አለባቸው ። ለዚህ የዘጸአትን መጽሐፍ ምዕራፍ 25-39 መመልከት ጠቃሚ ነው ። መንጻት የቅድስና መለስተኛ ትርጉም ነው ።

መቀደስ ማለት መለየት ማለት ነው ። ማለትም ለእግዚአብሔር ሆኖ መገኘት ማለት ነው ። መንፃት ማለት ግን ያለነቀፋ ሆኖ መገኘት ወይም ያለስህተት ሆኖ መጠበቅ ነው ።

በብሉይ ኪዳን ሰውም ሆነ ዕቃ ከነፃ በኋላ ለእግዚአብሔር ሆኖ ይቀደሳል ማለትም ይለያል ። ለእግዚአብሔር ሆኖ ከተቀደሰ በኋላ ለሌላ መገልገያ ሆኖ መቅረብ አይችልም ።

ሆኖም የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን የመንፃትና የመቀደስ ሥርዓትና ደረጃ የተለየ ነው ። የአዲስ ኪዳን መንፃትና መቀደስ የውስጥ ሕይወት መንጻትና መቀደስ ነው ። የብሉይ ኪዳን ግን ውጫዊ ወይም ሥጋዊ የሆነ መንፃት ነው ። ዕብ.9፥ 10.13

ጌታ ቤተክርስቲያን ያለነውርና ያለነቀፋ ሆና እንድትገኝ በደሙ ፣ በቃሉ ፣ በመንፈሱ ያነፃታል ፣ ይቀድሳታል ። ( ሚል3፥1-4 ኤፌ.5 ፥26 - 27 ፥2ኛ ቆሮ. 11፥1-2 ፥9፥14 ፥ ዮሐ. 15፥3. 6፥63፥

ቲቶ 3፥4 / ይህ የመንጻት ሁኔታ በቤተክርስቲያን የውስጥ አገልግሎት የሚቀጥል ነው ። ( ዕብ.10፥22 )

መ. <u>ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ፡</u>

በኤፌ. 4፥11-13 ላይ እንደምናየው ለቤተክርስቲያን የተሰጡ አገልጋዮች ከተሰጡበት ምክንያት አንዱ ምዕመናንን ለቅዱስ አገልግሎት እንዲያዘጋጁ ማድረግ ነው ።

ምዕመናን ለአገልግሎት ማዘጋጀት የሚቻለው ደቀመዝሙር በማድረግ ማለትም በማስተማር ነው ።

እንደ እግዚአብሔር ቃል ካየን ቅዱሳን ሁሉ ለአገልግሎት ተጠርተዋል ። ( 1ኛ ጴጥ. 2፥9፥ ሮሜ 12 ፥ 4-8 )

ቅዱሳን በተሰጣቸው ፀጋ እንዲያገለግሉ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል ፡ ጌታ በቤተክርስቲያን ውስጥ አስተማሪዎችን ያስቀመጠው ለዚህ ዓላማ ነው ። ( ኤፌ. 4፥11 ) ደግሞም ያመኑትን ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ብሏል ( ማቴ.28፥20 )

<u>ከደቀመዛሙርት ምን ይጠበቃል</u>

1. መታዘዝ ( ማቴ.11፥1)
2. ታማኝነት ( 1ኛ ተሰ.2፥4 )
3. መስቀሉን ተሸክሞ መጓዝ ( ሉቃ.14፥25፥ ፊል 1.፥29 ) ነው ።

ይህ ሥልጠና አገልጋዮችን በመደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በማስተማር የሚያበቃ አይደለም ። በቤተክርስቲያን ውስጥ ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ለሚያገለግሉ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መግባት ያስፈልጋቸው ይሆናል ። ሆኖም እግዚአብሔርን ለማገልገል ሙሉ ጊዜያቸውን በስጡት ብቻ የሚወሰን ስላይደለ ከቃሉ እንዳየነውና እንደተረዳነው ማኅበረ - ምዕመናን ሁሉ በተሰጣቸው ልዩ ልዩ የፀጋ ስጦታ እግዚአብሔርን ያገለግላሉ ። (1ኛ ጴጥ 4፥10 ) ስለዚህ በተሰጣቸው የፀጋ ስጦታ እንዲያገለግሉ የማዘጋጀቱ ሥራ በቤተክርስቲያን የውስጥ አገልግሎት የሚካሄድ ነው ።

ሠ/ <u>የኤክሌሽያ ሥርዓቶች ፡</u>

ቤተክርስቲያን እንደ ብሉይ ኪዳን ሕዝብ በልዩ ልዩ የአምልኮ ሥርዓት የተያዘችና የተሞላች አይደለችም ። ምክንያቱም የአ



ዲስ ኪዳን ሕዝብ እያንዳንዱ ከአምላኩ ጋር በመንፈስ ቅዱስ ቀጥተኛ ኅብረት ማድረግ ስለሚችል ነው ። ነገር ግን በጌታ የተሰጡ ሁለት ሥርዓቶች ብቻ አሉ ። እነርሱም ፦ የውኃ ጥምቀትና የጌታ ራት ናቸው ። ሆኖም አንዳንድ አብያተክርስቲያናት እግር መተጣጠብም ይጨምራል እነዚህ ሁለቱን ብቻ በተናጠል በመጠኑ እናያለን ።

1/ <u>የውኃ ጥምቀት</u> ፡

1.1. የቃሉ ትርጉም — በግሪክ ቋንቋ " ባፕቲዝማ " ይባላል፥ትርጉሙም " ወደታች ማስመጥ " ማለት ነው ።

1.2. ምሳሌነቱ ፦

1.2.1 ወደ ውኃ መስመጥ ፡ ለአሮጌው ሰው መሞት ፡ ከክርስቶስ ጋር እንደ መቀበር መቁጠር ፡ ( ቆላ.2 ፥12)

1.2.2 ከውኃ መውጣት ፡ ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሳ በአዲስ ሕይወት አብሮ እንደመነሳት መቁጠር፥(ቆላ. 2፥12 ሮሜ 6፥3-4 )

1.3. ለውኃ ጥምቀት የሚበቃ ፦

1.3.1 ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በፍጹም ልቡ አምኖ የተቀበለ ነው ። ( ሥራ 8፥36 )

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወደ ውኃ አጠገብ ሲደርሱ ፊልጶስን የጠየቀውና ፊልጶስም የሰጠው መልስ በጣም ግልፅ ነው ። ጃንደረባው እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድነው ባለው ጊዜ ፊልጶስም " በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶልሃል " አለው ። በሌላ መልክ ብናየው በፍጹም ልብህ ካላመንህ አይፈቀድልህም ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው ። ይህ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ብቻ ላይ የሚሠራ አይደለም ፡ የእግዚአብሔር ቃል እንደየሁኔታው የምንቀያይረው አይደለም ። ስለዚህ ዛሬም ለመጠመቅ የሚያበቃ ነጥብ ቢኖር ጃንደረባው እንደመለሰው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ ማለት የሚችል መሆን አለበት ። ( ሥራ 8 ፥ 37 )

1.3.2 የልብ መነሳሳትና የግል ዝግጅት ( ሥራ 8፥36 ) ፡ ለውኃ ጥምቀት የግል መነሳትና የልብ ዝግጅት አስፈ

ላጊ ነው ። በሌላ ሰው ግፊትና አነሳሽነት መሆን የለበትም ። ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባና ከፊልጶስ ሁኔታ እንደምንረዳው ፣ ፊልጶስ ያደረገው ነገር ቢኖር ቃሉን ማስረዳት ነበር እንጂ እንዲጠመቅ አልጋበዘውም ፣ አልገፋፋውም ። ምክንያቱም የግል ውሣኔ ነውና ። ለመጠመቅ ጥያቄ ያቀረበው ጃንደረባው ነው ። ስለዚህ በውኃ ጥምቀት የግል መነሳሳትና ውሣኔ አስፈላጊ ነው ።

## 2/ <u>የጌታ እራት ፣</u>

የጌታ እራት የተደነገገው የፋሲካ ዕለት ነበር ። ( ሉቃ.22፡7-23) ፋሲካ ማለት የማለፍ በዓል ማለት ነው ። የግብፃውያን የበኩር ልጆች በመቅሰፍት ሲሞቱ እሥራኤላውያን ግን በቤታቸው መቃንና ጉበን ላይ የጠቦት በግ ደም በመቀባት ከመቅሰፍት ታልፈዋል ። ( ዘፀ. 12፡1-1 | )

ከቅኝ ገዥነት ነፃ የወጡበትን ቀን አንዳንድ አገሮች በየዓመቱ እንደሚያከብሩ ሁሉ እሥራኤላውያንም እግዚአብሔር በደነገገላቸው ሕግ መሠረት ከግብፅ ባርነት ነፃ የወጡበትን ቀን በየዓመቱ “ ፋሲካ ” በማለት ያከብሩ ነበር ። ( ዘፀ.13፡3-10 ) በዚህ በፋሲካ ምሽት ጌታ የፋሲካን በዓል ካከበረ በኋላ የጌታ እራት የምንለውን ደነገገ ። ( ሉቃ.22፡14-20 )

ስለ ጌታ እራት ስናስብ ማወቅ ያለብን ነገሮች ፡—

2.1. መታሰቢያነቱን ( ሉቃ.22፡14-20 1ቆሮ.11፡23-26. ማቴ. 26፡26-27 )

ከእነዚህ ጥቅሶች እንደምንረዳው መታሰብ ያለበት ነገር ምንድነው ? ቢባል ፡—

2.1.1 ሞቱን
2.1.2 ትንሣኤውን
2.1.3 ዳግም ምፅአቱን
2.1.4 በደሙ የተደረገ አዲስ ኪዳን ነው ።

2.2 ምሳሌነቱ ፡—

2.2.1 ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ፣

ኅብሥቱ በመስቀል ላይ የቆሰለውን ሥጋውን ሲመስል ፣ ፅዋው ደግሞ በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ ይመሰላል ።



ጽዋ በመካፈል ክርስቶስ በእኛ እንዳለ እኛ በክርስቶስ እንዳለን የሚመስልልን ነው ። ( 1ቆሮ.11፡16. ዮሐ.6፡56) ስለኅብሥቱና ስለ ጽዋው በአብያተ ክርስቲያናት መሐከል አጉል ክርክሮች ተደርገዋል ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ነው ፣ ደሜ እውነተኛ መጠጥ ነው የሚለው አባባል ዮሐ.6፡55.ሉቃ.22፡19 ) አንዳንዶች ኅብሥቱና ፅዋው ቃል በቃል ወደ ሥጋና ወደ ደሙ ይለወጣል ብለው ያስተምራሉ ክርስቶስ ራሱን በብዙ ነገሮች መስሏል። “ እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ ” ( ዮሐ.15፡1) “ እኔ የበጐች በር ነኝ” ( ዩሐ.10፡7 ) “ እኔ መንገድ ነኝ “ / ዮሐ.14፡6 ) ” የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ) “ ዮሐ. 6፡35.4148.51.58) ብሏል እነዚህን ራሱን የመሰለባቸውን ቃል በቃል እንደማንወስዳቸው ሁሉ እንጀራንም ቆርሶ ይህ ሥጋዬ ነው ብሎ ሲሰጣቸው ቃል በቃል ሥጋውን አድርገን አንወስደውም ማለት ነው ።

ደግሞም ይህንን ያለው ገና ሥጋው በመስቀል ላይ ሳይውልና ደሙም ሳይፈስ ነበር ። ሆኖም ኅብሥቱን በሥጋው መስሎ ጽዋውን በደሙ መስሎ አቅርባል ።
እራሱን በወይን ግንድ ፣ በበጐች በር መመሰሉ ትርጉም እንደሚሰጠን ሁሉ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም ፣ በእኔ የሚያምን ከቶ አይጠማም ፣ በማለት ራሱን በሕይወት እንጀራና ሕይወት ውኃ መመሰሉ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ በነፍሳቸው ከቶውን እንደማይራቡና እንደማይጠሙ ለመግለጽ ነው ዮሐ.6፡35

2.2.2 ከቅዱሳን ጋር ኅብረት ፣

በክርስቶስ ሥጋ የተመሰለውን አንዱን ኅብሥት ብዙዎች ሆነን መካፈላችን በክርስቶስ አንድ አካል መሆናችንን ያስገነዝበናል ። ( 1ቆሮ.10፡17 )

2.3 የጌታን እራት ለመካፈል የሚያበቃ ምንድነው ?
በመጀመሪያ የጌታን እራት መካፈል የ ሚችል ሰው ጌታን የግል መድኃኒቱ አድርጐ የተቀበለ መሆን አለበት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትኛው እንደሚቀድም ባይገለጽም የውኃ ጥምቀት ከወሰደ በኋላ ቢሆን ጥሩ ነው ። ሆኖም አንዱ ለሌላው ሥርዓት አያቀርብም ፣ አያበቃምም ፣ ሁለቱም ራሳቸ

ውን ችለው የሚቆሙ ሥር ዓቶች ናቸው ። ቢሆንም አንድ አማኝ የጌታን እራት ከመቀበሉ በፊት ራሱን መመርመር አለበት ። ( 1ቆሮ. 11፥28)

በ1ቆሮ.11፥27 ላይ " ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላይ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት " ማለቱ ምንድነው ? በመሠረቱ ማንም ሰው ቢሆን " ብቁ ሆኖ " መቅረብ የሚችል የለም ። ጌታ በመስቀል ላይ የዋለው ለጻድቃን ሳይሆን ለኃጢአተኞች መሆኑ ግልጽ ነው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ እዚህ ላይ መግለጽ የሚፈልገው አንድ ሰው በልማድ እንደሚበላ እንጀራ በመቁጠር በግዴለሽነት መካፈል የለበትም ለማለት ነው ። ይህ ከሆነ በማይገባው ሁኔታ ወሰደ ማለት ነው ።

በቁጥር 27 " ሳይገባው " የሚለው ቃልና በቁጥር 29 "ሳይገባው " የሚለው ቃል ሁለቱ ልዩ ትርጉም ነው ያላቸው ። ይኸውም በቁጥር 27 ላይ በማይገባው ሁኔታ ለማለት ሲሆን ፥ በቁጥር 29 ላይ ደግሞ ላላ አድርገን ብናነበው የሚሰጠን ትርጉም " ሳይረዳ " የሚል ይሆናል ። ስለዚህ አንድ አማኝ የጌታ ሥጋና ደም እንደሆነ ሳይረዳ መካፈል አይገባውም ማለት ነው ።

## ክፍል 2. የኤክሌሺያ የውጭ አገልግሎት

የቤተክርስቲያን የውጭ አገልግሎት የምንለው ወንጌልን ላልደረሳቸው የማዳረስ አገልግሎት ነው ።

ሀ/ ለዚህ አገልግሎቱ መሠረት የሚሆኑ ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ፡

1. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ ተልዕኮ ( ማቴ.28፥18-20) አንድን ተልዕኮ ወይንም ትዕዛዝ ተፈጻሚ የሚያደርገው የትዕዛዝ ሰጪው ሥልጣን ነው ።ጌታችን ደግሞ በሰማይ በምድርም ሥልጣን ተሰጥቶታል ። ስለዚህ የጌታን ሥልጣንና ክብር የተረዳ ሁሉ ለታላቁ ተልዕኮ ይታዘዛል ።
2. የጌታ ፍቅር (2 ቆሮ.5፥ 13-14 ፥ ዮሐ. 14፥21 ) ጌታ ፍቅር ነው ። ፍቅሩንም ነፍሱን በመስጠት ገልጿል ። ( ዮሐ 15፥13) ስለዚህ ይህ የጌታ ፍቅር እንድንታዘዝ ግድ ይለናል ። (2ቆሮ. 5፥13-14) ፍቅሩ የገባው ታላቁን ተልዕኮ ይፈጽማል ።

ለ/ ወንጌል ላልደረሳቸው ማዳረስ ፥

ወንጌልን ለማዳረስ ብዙ መንገዶች ቢኖሩም ሁለት ዋና ዋና መንገዶችን እንጠቅሳለን ።



1. አባላትን በሙሉ ማሳተፍ ፥

እግዚአብሔር ከጨለማ ወደ ብርሃን የጠራቸው የእርሱን የማዳን ሥራ እንዲናገሩ ነው ። ( 1ጴጥ.2፥9 ) ከቃሉ እንደምንረዳው በጌታ ማመን ብቻ ሳይሆን ስለእርሱ መመስከር አስፈላጊ ነው ። ( ሮሜ 10፥9-10 ፥ ዮሐ. 12፥42)

ስለዚህ ማኅበረ - ምዕመናን በየግል ክርስቶስን ይመሰክሩ ዘንድ ያስፈልጋቸዋል ።

2. የወንጌል ሰባኪዎችን መጠቀም ፥

ይህ እንደተራራው ስብከት ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ወንጌልን መስበክ ነው ። በየትኛውም መንገድ ይቅረብ ከቤተ ክርስቲያን የሚጠበቅ ነገር ታላቅ ተልዕኮ ወንጌልን ለዓለም መስበክ ነው ። የወንጌል ስብከት ሥራ እስከ ጌታችን ዳግም

ምፅአት የሚቀጥል ነው ። ታዲያ ቤተክርስቲያን የወንጌል ስብከት ማቀድ የምትተወው ስታረጅ ነው ። ወንጌልን መስበክ የምትተው አጥቢያ ቤተክርስቲያን ወደ ሞት ትቃረባለች አጥቢያ ቤተክርስቲያን የምትኖረውና የምታድገው ወንጌል ስትሰብክ ብቻ ነው ።

ሐ/ የኤክሌሽያ የውጭ አገልግሎት ምሳሌ ሆነው የቀረቡ ሁለት ነገሮች አሉ ።

1) በጨው የተመሰለ አገልግሎት ፥

ጨው ነገሮች ሳይበላሹ ለብዙ ጊዜ እንዲቆይ የሚረዳ ሲሆን፥ ለምግብ ጣዕም ይሰጣል ፥ በተመሳሳይ ሁኔታ ቤተክርስቲያን ለእውነት እስከ መጨረሻው በመቆም በመልካም ሥራ ውስጥ በመታየት እግዚአብሔር እንዲከበርና እንዲመሰገን ታደርጋለች ( 1ጴጥ.2፥12 ሮሜ 12፥20 ) ።

2) በመብራት የተመሰለ አገልግሎት ፥

በመብራት የተመሰለው የእግዚአብሔር ቃል ነው ( መዝ.119 105) ። ስለዚህ ቤተክርስቲያን ይህን የሕይወት ቃል ለዓለም በማቅረብ እንደ ብርሃን ትታያለች ፥ ( ፊል.2፥14 ) ይህ የሕይወት ቃል የተባለው ለሰዎች ሁሉ ሕይወት የሚሰጥ የወንጌል መልዕክት ነው ። ስለዚህ ቤተክርስቲያን በዚህ ዓለም መኖር እንደ ጨውና እንደ ብርሃን ሆና ታገለግላለች ። ቤተ

ክርስቲያን በዚች ዓለም ባትኖር ግን ዓለም ጣዕም ታጣለች ፣ ጨለማም ይውጣታል ። ይህ የማይካድ እውነት ነው ።

መ/ ከአማኞች ሌላ በወንጌል ሥራ ማን ድርሻ አለው ?

በመሠረቱ የወንጌል አገልግሎት ሥራ ለሰው ልጆች ብቻ የተሰጠ አይደለም ። ወይም ወንጌል ያመኑና የተቀበሉ ሰዎች ወንጌልን የማዳረስን ሥራ እራሳቸው እንዲወጡት የተተወላቸው አይደለም ።

1. በወንጌል አገልግሎት የአብ ድርሻ ፣

የወንጌል አገልግሎት ሰዎችን የማዳን ሥራ ነው ። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ከራሱ ጋር የሚያስታርቀው በክርስቶስ ነው ። (2ቆሮ 5፥18 ) ለዚህ ሥራ ተጓዳኝ ሠራተኞች በክርስቶስ አምነው የዳኑ ሰዎች ናቸው ። ( 2ቆሮ.5፥18-19 ) እግዚአብሔር ለእነርሱ ፦

1ኛ. የማስታረቅን አገልግሎት ይሰጣቸዋል ፣
2ኛ. የማስታረቅንም ቃል ማለትም የጥበብን ቃል ይሰጣቸዋል ፣
3ኛ. ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለው ባለመሰልቸት ሰዎችን ሁሉ የሚማልዱበትን ፀጋ ይሰጣቸዋል ።

እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደሚሠራ ማስረጃው የመሰከርንላቸው ሰዎች የእኛን የምስክርነትን ቃል ሲቀበሉ መዳናቸው ነው ። ደግሞም ከእግዚአብሔር ጋር ተጓዳኝ ሠራተኞች መሆናችንን ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ "እኔ ተከልኩ ፣ አጵሎስ አጠጣ" ይልና " ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር " ካለ በኋላ " እኛ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ ነን " ይላል ። (1ኛ ቆሮ.3፥6.9

ይህም ማለት ሰዎች በግላቸው ቃሉን አንብበውም ቢሆን ያለ እኛ ጣልቃ ገቢነት አይድኑም ማለት አይደለም ። ነገር ግን ማለት የተፈለገው በወንጌል ማዳረስ ሥራ ውስጥ እግዚአብሔር ከአማኞች ጋር ይሠራል ለማለት ነው ።

2. በወንጌል አገልግሎት የጌታ ድርሻ ፣

ጌታ ታላቁን ተልዕኮ ከሰጠ በኋላ " እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ " ብሏል (ማቴ.28፥20፣) በማር 16፥20 ላይ እንደምናነበው ደግሞ " ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር ፣ በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያፀና ነበር" ይላል ። ታዲያ ከሐዋርያቱ ጋር እንጂ ከእኛ ጋር መሆኑን በምን እናውቃለን? ብንል "እስከ ዓለም ፍጻሜ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ " የሚለው ቃል አሁንም ወደፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ወንጌል ከሚሰብኩት ጋር መሆኑን



ያረጋግጣል ። ሐዋርያት በዓይናቸው እያዩት ፣ በጆሮአቸው እየሰሙት ይናገር እንጂ እርሱ ግን በዘመናት ሁሉ ውስጥ ያሉትን ታማኝ ባሪያዎች እያየ ነበር የተናገረው ። ስለዚህ ዛሬም ስሙ ሲጠራ ድንቅ ተአምራት የሚሆነው ፣ ጌታ ከሚያምኑት ጋር እንደቃሉ አብሮ በመሥራቱ ነው ።

የወንጌል አገልጋዮች የጌታ አምባሣደሮች ተብለዋል ፣ በ2ኛ ቆሮ. 5፥20 ላይ " ስለክርስቶስ መልዕክተኞች ነን " የሚለው ቃል የክርስቶስ አምባሣደሮች " የሚል ትርጉም ነው ያለው ። አምባሣደር ማለት የተላከ ማለት ነው ፣ ወይም ባለሙሉ ሥልጣን ሆኖ የተወከለ ማለት ነው ። ስለዚህ ጌታ " አብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ " አለ ፣ ( ዮሐ. 20 ፥ 21 ) ስለዚህ " እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል ፣ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል " ብሏል ። ( ማቴ.10፥40 )

ለዚህ የሚበቃ ማነው ? ማንም የለም ። ነገር ግን የአማኞች ሁሉ ብቃት ጌታ ነው ። ( 2ቆሮ.13፥5፣ 1ቆሮ.1፥26-30 ) ስለዚህ ስለ ስሙ ከምትመሰክር ቤተክርስቲያን ጋር ጌታ ሁልጊዜ አብሮ ተጓዳኝ ሆኖ ይሠራል ። ( ማቴ.28፥20 )

3. በወንጌል አገልግሎት የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ ፣

ስለ ጌታ በመመስከር ትልቁን ድርሻ የያዘ መንፈስ ቅዱስ ነው። ( ዮሐ.15፥26. ሥራ 5፥32 ዮሐ 16፥8 ) ክርስቶስ በግልጽ " ስለ እኔ ይመሰክራል " ያለው ስማያዊ አካል የሆነ መንፈስ ቅዱስን ነው ። ሆኖም መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስን የሚመሰክረው እንዴት ነው ? ሐዋርያው ጳውሎስ በ1 ቆሮ 12፥1-4 ላይ እንደተጠቀሰው ያለ መንፈስ ቅዱስ ማንም ሰው ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ሊገነዘብ አይችልም ይላል ። እንደገናም በዮሐ. 16፥14 "እርሱ ያከብረኛል" ይላል ስለዚህ የወንጌልን ቃል ለሚሰሙ የጌታን ማንነት የሚገልጽና የሚመሰክረው መንፈስ ቅዱስ ነው ።

የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በሁለት አቅጣጫ ማየት እንችላለን ። በአንድ በኩል ስለ ጌታ የሚመሰክሩትን ኃይል ( ሥራ 1፥8) የሚናገሩበትን ቃልና ጥበብ (ሉቃ.12፥11 21፥15 ሥራ 6፥20 ) ይሰጣቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ቃሉን የሚሰሙትን በኃጢአታቸው እንዲፀፀቱ እና ንስሐ እንዲገቡ ይወቅሳቸዋል ። ያነሳሳቸዋል። (ዮሐ. 16 ፥ 8 )

ሆኖም የሚመሠክርላቸው ሰዎች ልባቸውን ? ደንድነው ሊቃወሙ ይችላሉ ( ሥራ 7፥51.24፥24-25 ) ። ነገር ግን ያለ መንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ማንም ሰው ኢየሱስን ጌታና አዳኝ አድርጎ ሊረዳና

ሊቀበል አይችልም ። በአእምሮ ብቻ የሚደገፍ ሰው የክርስቶስን ነገር ሞኝነት አድርጎ ስለሚቆጥር ሊቀበለው አይችልም ። 1 ቆሮ 3፥14 )

4. የቅዱሳን መላዕክቶች ድርሻ ፥
በወንጌል አገልግሎት ውስጥ ቅዱሳን መላዕክትም ታላቅ ድርሻ አላቸው

4.1 በመጀመሪያ የጌታን መፀነስ ያበሠረ መላእክ ነው ። ( ሉቃ.1፥ 26-35 )

4.2 መወለድን አብሥረዋል ። ( ሉቃ. 2፥8-14 )
4.3 መነሣቱን አብሥረዋል ። ( ሉቃ.24፥1-4 )
4.4 ዕርገቱን አብሥረዋል ። ( ሥራ 1፥10 )
4.5 ዳግም ምፅአቱን አብሥረዋል ። ( ሥራ 1፥10 )

እሁንም ቢሆን ቅዱሳን መላዕክት በወንጌል አገልግሎት ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት እንችላለን ። ዕብ 1.14

ሐዋርያው ዮሐንስ ከጌታ ዘንድ ተልኮ በራዕይ ላሣየው መልአክ ሊሰግድለት በእግሩ ፊት ሲደፋ መልአኩ ለእርሱ መስገድ እንደሌለበት ካስጠነቀቀው በኋላ ስለራሱ ሲመሰክር “ ከአንተ ጋር የኢየሱስ ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ” አለው ። ( ራዕ.19፥ 10፥22፥8-9 ) ስለዚህ ወንጌልን ከሚሰብኩት ጋር መላእክት ተጓዳኝ ሆነው ይሠራሉ ማለት ነው ። በዕብ.1፥14 ላይ እንደምንመለከተው ደግሞ መላእክት መዳንን ይወርሱ ዘንድ ለሚገባቸው ለማገዝ የሚላኩ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደሆኑ እንረዳለን ።

በሐዋርያው ሥራ ውስጥ የሆነውን ብናይ በአንድ ወቅት መቶ አለቃው ቆርኔሊዮስ ሲፀልይ መልአክ ተገልጾለት ጴጥሮስን አስጠርቶ የወንጌል ቃል ከእርሱ እንዲሰማ ሲያግዘው እናያለን ። ( ሥራ 10፥1-6 )

በሌላ በኩል ደግሞ ለፊሊጶስ ተገልጦለት ወደ ጋዛ ምድረ በዳ ሄዶ በመንገድ ላይ ላለው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ እንዲመሰክርለት ሲያግዘው እናያለን ። ( ሥራ 8 ፥ 26 - 32 )

ይሁን እንጂ መላእክት ክርስቶስ ያድናል ብለው ለሰዎች ሲመሰክሩ አናይም ። ይህ ለምን ይሆን ?



ይህ የሚያሳየው መላዕክት ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር የማስታረቅ አገልግሎት እንዳልተሰጣቸው ነው ። አለበለዚያ የሁለት ቀን መንገድ፡ ልኮ ጴጥሮስን ከማስጠራት ስለክርስቶስ ማዳን ወዲያው በነገረውና ቆርኔሊዮስ ጌታን በተቀበለ ነበር። እንደገናም ፊልጶስን ወደ ምድረ በዳ ከሚልክና ከሚያደክም ይልቅ ለጃንደረባው ተገልጦለት ጌታን እንዲቀበል በረዳው ነበር።ምክንያቱም ወደ ጋዛ ምድረበዳ መሄድ ከፊልጶስ ይልቅ ለመልአኩ ይቀልለው ነበርና ! ስለዚህ መማለድና ማስታረቅ ለሰዎች እንጂ ለመላዕክት አልተሰጣቸውም ። (2 ቆሮ. 5፥18 )

ከዚህ ጋር ደግሞ መላዕክት ለወንጌል አገልግሎት የተላኩትን ከአደጋ የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳላቸው እናያለን ።

በአንድ ወቅት ሐዋርያትን አይሁዶች ወደ ወህኒ አስገብተዋቸው ነበር ። የጌታ መልአክ ግን የወህኒውን ደጅ ከፍቶ ካወጣቸው በኋላ የወንጌል አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ እንደ ነገራቸው እናያለን ( ሥራ 5 ፥ 18 - 20 ) ።

በሌላ ጉዞ ደግሞ ጴጥሮስን ከታሠረበት ወህኒ ቤት ፈትቶ እንዳወጣው እናነባለን ( ሥራ 12 ፥ 7 - 10 ) ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ከሌሎች እሥረኞች ጋር በወንጌል ምክንያት ታሥሮ ወደ ሮም በመርከብ ሲጓዝ የሚያስጨንቅ አደጋ በደረሰባቸው ጊዜ የጌታ መልአክ በአጠገቡ ቆሞ እንዳበረታታው እንረዳለን ። ( ሥራ 27 ፥ 23-24 ) ።

ጌታም ዘወትር የሚጠብቁን መላዕክቶች እንዳሉና የሚንቁንንና የሚጠሉንን ለመበቀል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማግኘት ፊቱን እንደሚያዩ ተናግሯል ( ማቴ. 18፥10 )

እንግዲህ ስለ ወንጌል አገልግሎት ስንመለከት የሰማይ አካላት ሁሉ ከቤተክርስቲያን ጋር አብረው ተጓዳኝ ሆነው እንደሚሠሩ ተረድተናል ። ስለዚህም ነው ቤተክርስቲያንን የገሐነም ደጆች ሁሉ ሊቋቋሟት የማይችሉት ። በየዘመናቱ ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት ዲያብሎስ በተለያየ መንገድ ሲያስነሳቸው የነበሩት ሁሉ ሲጠፉ ቤተክርስቲያን ግን አለች ። ወደ

ፊትም በሰማያዊ ሥፍራ ከበጉ ክርስቶስ ጋር ለዘለዓለም ትኖራለች ። ይህ ታላቅ ተስፋ በክርስቶስ ዳግም ምፅአት ይፈጸማል ።

" እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱ እንደሥራው እከፍለው ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አሉ ። "

" መንፈሱና ሙሽራውም ና ይላሉ የሚሰማማም ና ይላል፣ የተጠማም ይምጣ የወደደም የሀይወትን ውኃ እንዲያው ይወሰድ "

" ይህን የሚመሰክር ፡— አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል አሜን ጌታ እየሱስ ሆይና " ራዕ 22፡12.17.20

አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ጌታ ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ክብርና ምስጋና ይሁን ።



# ምስጋና

" ኤክሌሽያ " ን ሳዘጋጅ ብዙ ወገኖች በጸሎትና ረቂቁን በማንበብ ረድተውኛል ። ጌታ ይባርካቸው ። በተለይም ታይፕ በማድረግ ሀሳብ በመስጠት ረግድ ሳትሰለች ትርፍ ጊዜዋን መስዋዕት እያደረገች በፍጹም ቅንነት የረዳችኝ በጌታ ልጇ የሆነችውን ወ/ሮ ፋንታዬ ተረፈ ጌታ ይባርካት እላለሁ ።

ከሁሉ በላይ ግን በመንፈሱ ላበረታኝ ፣ ጸጋውን ለሰጠኝ ጌታ ክብርና ምሥጋና አቀርባለሁ ። አ ሜ ን ።

ሰለሞን ወ/አምላክ

ሚያዝያ 1985

Church Business
An Independent - study Text book
By Joseph W;Kipatrick
BiBilology - Ecclesiology
An Independent - study Textbook
by Suwandoko Koslim
Lectures in Systematic Theology
By Henry C.Thiessen
A systematic Theology of the Christian Religion
By James Oliver Buswell, Jr. PH..D
The Indigenous Church
By Melvin L. Hodges
Knowing The Doctrines of the BIBLE
By MYER PEARLMAN

ይህቺ መፅሐፍ ለቤተክርስቲያን መሪዎችና በቤተክርስቲያን ውስጥ በተለያየ የአገልግሎት ደረጃ ላይ ላሉ ሁሉ አገልግሎታቸውን በብቃትና በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን እንዲችሉ ትልቅ እገዛ እንደምታደርግ አምናለሁ ።

## ለማ ምስጋና

ኑፋቄት በብዛት እየፈለሱ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በሚጨመሩበት በአሁኑ ወቅት ለብር ሊታሰብበት የሚገባ ነገር ቢኖር የማደራጀት ጉዳይ መሆን አለበት ስለዚህ ይህቺ ሊክሊሽያ የተሰኘች ጽሑፍ በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ደረጃ ለተደራጁ ና የመደራጀት አዝማሚያ ለሚያሳዩ ለማኞች ሁሉ ብቃት ያለው ትምህርትና ምክር እንዲሁም መመሪያ ትሰጣለች ብዬ አምናለሁ ።

## ፓስተር መርጅ ለማ

ለቶ ሰሎሞን በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በአማርኛ መጽሐፍ ለማዘጋጀት መሞከራቸው ከበሬታ የሚያሰጥ ነው።ይህ ጽሁፍ ርዕሱን በሚመለከት ብዙ ጠቃሚ ሃሳቦችን ያዘለ ሊክሊሽያ የሚለውን ሃሳብ በጥሩ ሁኔታ ያብራራ ነው። የቤተክርስቲያን አገልጋዮችና መሪዎች አስተውለው ቢያነቡት ያተርፉበታል ።

## ሰለሞን ከበደ

ቤተክርስቲያንና አስተዳደሯን በተመለከተ ወገናዊ እንጂ መጽሐፍ ቀዳሚ የሆኑ የአማርኛ መጽሐፍት በበቂ አንዝ የሉንም ስለቤተክርስቲያን አዲስ ካዳናዊ ግንዛቤ ለማግኘት የሊክሊሽያ መጽሐፍ አይነተኛ ምሳሌና አበረታች ጅማሬ ናት ። እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መሪ ሊያነባትና ሊኖርባት ይገባል ፡

## እንዳለ ገ/መስቀል